የአንድ ጠገራ ብር ቱሩፋት ገጽ 13



ሲስፋፉ የሚገባቸው የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

82ኛ ዓመት ቁጥር 063 ኅዳር 3 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# በሽሬ ዲስትሪክት ስር የነበሩ ሰባት የንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ስራ ጀመሩ



**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ሽሬ ዲስትሪክት ስር የነበሩት የማይካድራ፣ ሁመራ፣ ቃፍታ ፣ አውሮራ፣ ዳንሻ፣ አዲ ረሚጥ እና ከተማ ንጉስ ቅርንጫፎች ስራ መጀመራቸውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስታወቀ። በማይጸብሪ፣ በአይካል እና በአዲሄርዲ የነበሩ ቅርንጫፎችም በቅርቡ ስራ እንደሚጀምሩ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኮርፖሬት ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አልሰን አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሽሬ ዲስትሪክት ስር ተጠቃሚ የነበረው ማህበረሰብ እንዳይቸገር ሲባል ለጊዜው በጎንደር ዲስትሪክት ስር ታቅፈው አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉን ገልጸዋል።

እንደ አቶ አልሰን ገለፃ፤ የሽሬ ዲስትሪክት ሁሉም ቅርንጫፎች ሙሉ በሙሉ አገልግሎት እስከሚጀምሩ ድረስ ነው በጎንደር ዲስትሪክት አክሰስ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተከስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት በሽሬና መቀሌ ዲስትሪክቶች ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት አቁሞ እንደነበር ያወሱት አቶ አልሰን፤ ባንኩ ቀደም ሲል በጦርነቱ ምክንያት አገልግሎት በተቋረጠባቸው አካባቢዎች ዳግም ስራ ለማስጀመር ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል ብለዋል።

ባንኩ ባደረገው ጥረት ተከዜ፣ አዲ ጎሹ፣ ቆራሪት፣ ማይጋባ፣ ሰቲት እና አደባይ ቅርንጫፎች በቅርቡ ወደስራ

በሽሬ ዲስትሪክት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











# መንግሥት በግማሽ ቢሊየን ብር ወጪ ለትግራይ የሰብዓዊ ድጋፍ እያቀረበ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል መንግሥት በ500 ሚሊዮን ብር ወጪ በትግራይ ክልል የሰብዓዊ ድጋፍ እያቀረበ መሆኑን የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የፌዴራል መንግሥት በትግራይ ክልል ለሚገኙ ዜጎች 500 ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የተለያዩ ድጋፎች እያቀረበ ይገኛል።

በሽራሮ፣ ሽሬ፣ አክሱምና አድዋ አካባቢዎች በጦርነቱ ምክንያት ለችግር ለተጋለጡ ዜጎች የስንዴና የአልሚ ምግብ እየተከፋፈለ መሆኑን ገልጸዋል።



ከደቡብ አፍሪካው የሰላም ስምምነት በኋላ የተሻለ መረጋጋት በታየባቸው ተጨማሪ የትግራይ አካባቢዎች ላይም መንግሥት የሰብዓዊ ድጋፉን ለማከፋፈል ዝግጅት ማድረጉን ጠቁመዋል።

በመጪው ሳምንት መጀመሪያ ላይ መንግሥት ተጨማሪ ድጋፍ ለማቅረብ አርባ ከባድ ተሽከርካሪዎችን ወደትግራይ ያጓጉዛል ያሉት አምባሳደር ሽፈራው፤ በዚህም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የሰብዓዊ ድጋፎች ለህብረተሰቡ እንደሚከፋፈሉ አስታውቀዋል።

በቀጣይነትም ድጋፎቹ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የገለጹት ኮሚሽነሩ፤ በየብስ መስመሮች ከሚደረገው የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት በተጨማሪ በአየር ትራንስፖርት አማራጭ ድጋፎችን ለማቅረብ የሚደረገው ጥረት መቀጠሉንም ተናግረዋል።

በሽሬ፣ አክሱምና መቀሌ አየር ማረፊያዎች ላይ የሚከናወኑ ሥራዎች እንዳለቁ ከመንግስት ባለፈ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅራቢ ድርጅቶችም የአውሮፕላን

መንግሥት በግማሽ ቢሊየን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ወደ ትግራይ ክልል እርዳታ በብዛት እየገባ መሆኑን አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን አስታወቁ

ገጽ 4






## የመንግስት የኮሙኒኬሽን ሥራዎች የሰላም ስምምነቱን ድንጋጌዎች ያከበሩ መሆን እንዳለባቸው አገልግሎቱ አሳሰበ

ገጽ 4

# በ578 ትምህርት ቤቶች የሚተገበር አዲስ የምገባ ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ግሎባል ፓርትነርሺፕ ፎር ኤዱኬሽን ለአንድ ዓመት የሚዘልቅ አዲስ የምገባ ፕሮጀክት ከስድስት ክልሎች በተመረጡ 578 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ እንደሚያስጀምር ይፋ አደረገ።

ግሎባል ፓርትነርሺፕ ፎር ኤጁኬሽን ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከዓለም አቀፍ ሕፃናት አድን ድርጅት እና ከክልል አጋር ተቋማት ጋር ለሁለት ዓመታት ሲያካሂደው የነበረውን ሁሉን አቀፍ ሀገር በቀል እና አካታች የትምህርት ቤት ምገባ መርሐ-ግብር ፕሮጀክት በስኬት ማጠናቀቁን አስመልክቶ የምስጋና መድረክ ተካሂዷል።

ፕሮጀክቱ በሁለት ዓመታት ቆይታው ከ163 ሺህ በላይ ሕፃናትን በትምህርት ቤት ምገባ ለመደገፍ ያቀደ ቢሆንም በኢትዮጵያ በሚገኙ 648 ትምህርት ቤቶች ለ223 ሺህ 301 ተማሪዎች ድጋፍ ማድረጉ ተገልጿል።

ከዚህም በተጨማሪ የመጸዳጃ ቤት፣ ማብሰያ ክፍሎች ግንባታ እንዲሁም ለመምህራን ሥልጠና መስጠቱ ተጠቁሟል።

ከነበሩ ተሞክሮዎች በመነሣት አዲሱ ፕሮጀክት ከፈረንጆቹ ኅዳር 1 ቀን 2022 ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ 31 ቀን 2023 እንደሚቆይ ተገልጿል።



ግሎባል ፓርትነርሺፕ ፎር ኤጁኬሽን በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ89 ሀገራት ጋር በቅንጅት እንደሚሠራ የተናገሩት በኢትዮጵያ የተቋሙ ኃላፊ ዶር ስፓታህ ዳር፤ ተቋማቸው ለ20 ዓመታት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በትምህርቱ ዘርፍ እንደሠራ ጠቅሰው፤ በቀጣይም አጋርነቱ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር ፈንታ ማንደፍሮ በበኩላቸው፣ ግሎባል ፓርትነርሺፕ ፎር ኤዱኬሽን እና ዓለም አቀፍ ሕፃናት አድን ድርጅት ፕሮጀክቱ በተሳካ መልኩ እንዲጠናቀቅ ላደረጉት ድጋፍ ማመስገናቸውን ኢቢሲ ዘግቧል።



ወይዘሮ ትግስት በዳዳ

# አዲስ አበባን ከትምባሆ ጭስ ነፃ የማድረግ ንቅናቄ በቅርቡ ይካሄዳል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባን ከትምባሆ ጭስ ነፃ የማድረግ ንቅናቄ በህዳር ወር አጋማሽ በአዲስ አበባ ደረጃ እንደሚካሄድ የአዲስ አበባ ምግብና መድሃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ የምግብና መድሃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ትግስት በዳዳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አዲስ አበባን ከትምባሆ ጭስ ነፃ የማድረግ ንቅናቄ በህዳር ወር አጋማሽ ይጀመራል።

በንቅናቄው ህብረተሰቡን ስለትንባሆ ጎጂነት ከማስተማር ባለፈ ጊዜ ያለፈባቸው ምግብና መጠጦች እና ለፀሐይ የተጋለጡ ምርቶችን የሚለዩበትን መንገድ እንደሚያሳይ ተጠቁሟል። ይህም የከተማዋን ነዋሪ ጤና ለመጠበቅ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል።

ንቅናቄው ህብረተሰቡ ምግብና መጠጦችን ከሱቅ፣ ከሱፐር ማርኬትና ከመንገድ ሲገዛ ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች በቀላሉ መለየት የሚችልበትን መንገድ ለመፍጠር ታስቦ የተዘጋጀ ነው ያሉት ወይዘሮ ትግስት፤ ንቅናቄው በትምህርት ቤቶች አካባቢ በስፋት ይካሄዳል፤ ይህንን ለማድረግም ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር በጋራ እየሰራን ነው ብለዋል።

በተለይ ተማሪው ከትምህርቱ ባሻገር ከአደንዛዥ እጽ ጋር እራሱን እንዲጠብቅና እንደዚህ አይነት ተግባር ላይ ያሉትን ተማሪዎች እንዲያስተምር ግንዛቤ ለመፍጠር ሥራ እየተሰራ ነው። ከዚህም ባለፈ በትምህርት ቤት አካባቢዎች ተማሪውን ለአደንዛዥ እጽና ለትንባሆ ተጠቃሚነት የሚጋብዙ ቦታዎችን ባለስልጣኑ እያጠራ እንደሚሄድ ገልጸዋል።

ንቅናቄው በትምህርት ቤቶች ላይ የሚያተኩር ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን ለጤና ችግር የሚዳርጉ ቦታዎች ላይም እንደሚያተኩር የተናገሩት ኃላፊዋ፤ ንቅናቄው የተማሪዎችን፣ የህብረተሰቡንና የንግድ ቤት ባለቤቶችን ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችልና ህብረተሰቡ ራሱን በጤና ለመጠበቅ የሚያስችል አዕምሯዊ ብቃት የሚያላብስ ነው ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ ትግስት ገለፃ፤ በ2013 ዓመተ ምህረት የተጀመረው አዲስ አበባን ከትንባሆ ጭስ ነፃ የማድረግ ተግባር በ2014 ዓመተ ምህረት በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። ይህንኑ ደግሞ በ2015 ዓመተ ምህረት አጠናክሮ ለመቀጠል በህዳር ወር አጋማሽ በአዲስ አበባ ደረጃ ንቅናቄውን ለማድረግ ታቅዷል።

በዚህም ህብረተሰቡን ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ በከተማዋ በሚገኙ 121 ወረዳዎች ላይ የሚደረግ ይሆናል። ቀጥሎም በወረዳዎቹ የተሰራው ሥራ በክፍለ ከተማ ደረጃ ይገመገማል። ይህም እስከ አሁን ሲሰራ ከነበረው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የተሻለ እንደሚሆን ተናግረዋል።

አሁን በከተማዋ ለህብረተሰቡ የጤና ጠንቅ እየሆነ ያለው የማይታወቁ ምርቶች የመጠቀም ሁኔታ ይስተዋላል። ስለዚህ ይህንን ለህብረተሰቡ ለማሳወቅና ራሱን በጤና ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እየሞከረ ነው። ለዚህም ይህንን የማስተማሪያ መድረክ አዘጋጅተናል ብለዋል።



ወይዘሮ አብነት ቢሻው



አቶ ይታገሱ ኃይሌ



አቶ ወንድሙ ገብረእየሱስ

# ጊዜና ወቅት ያልገደበው የበጎ አገልግሎት

**ሳሙኤል ወንድወሰን**

ድህነት ጥላውን ላጠላባቸው ነፍሶች ቤት ከመጠለያም በላይ ነው። ቤት ገመናን ሸፋኝ፣ የዘመናት እንባን አባሽ፣ ሀዘንን መርሻ፣ ዞሮ መግቢያ ነው። የክረምቱን መግባት ተከትሎ በበጎ ፈቃድ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የአረጋውያንን እና የአቅመ ደካሞችን ቤቶች ማደስ አንዱ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብና መድሃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣንም በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎቱ የብዙዎችን ቤት ጎብኝቷል።ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው ዝቅ ብሎ እጃቸው ላጠረባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ቤታቸውን አድሶ ለባለቤቶቹ አስተላልፏል።

ወይዘሮ አብነት ቢሻው ይባላሉ፤ የመኖሪያ ጎጇቸውን በአዲስ አበባ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በተለምዶ አዲሱ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ቀልሰዋል። ቤታቸው ወደ ጎን ያዘመመ፣ለመውደቅ አንድ ሀሙስ የቀረው እርጅና የደቋቆሰው ነበር።

ድህነት ድሩን ያደራባቸው ወይዘሮዋ ኑሯቸው የስቃይ ነበር። ከአሁን አሁን ቤታችን ፈረሰ በሚል ስጋት እንቅልፋቸውም የሰቀቀን ነበር።"ቤታችን በተኛንበት የሚፈርስ ስለሚመስለን በቀን እንኳን ለመተኛት እምነት የምንጥልበት አልነበረም።"ይላሉ

ዝናብ ሲጥል የሚገባውን ውሃ ከጎረቤት ጋር በመተባበር በባልዲ እየቀዱ ያፈስሱ እንደነበር የሚያስታውሱት ወይዘሮ አብነት "የሚገባው ጎርፍ የልጆቼን ደብተር፣የቤት ውስጥ የፍጆታ ዕቃዎቼንና ልብሳችንን አበላሽቶብን ያውቃል" ሲሉም ያሳለፉትን ያስታውሳሉ።

የልብ ህመምተኛ ልጃቸው ለየት ያለ ጠረን ሲሸታት ስለምትታመም ልጃቸውን ከአካባቢው ለማሸሽ ግድ ብሏቸው ነበር። ቤቱ ልጆቻቸው ላይ ወድቆ አደጋ ያደርሳል በሚል ስጋት ብዙ የመከራ ቀናቶችን አሳይቷቸዋል። ለዚሁ ሲሉም ልጃቸውን ከሰው አስጠግተው ለማኖር ተገደውም ያውቃሉ።

ወይዘሮ አብነት "አሁን ቤቴ ስለታደሰልኝ ልጄን አያምብኝም፤ጎርፍ ይገባል፤ቤቱም ይወድቃል የሚል ስጋት የለብኝም፤የተደረገልኝን ለመናገር ቃላት ያንሰኛል" ይላሉ። በእንዲህ አይነት በጎ ሃሳብ በመነሳሳት ደካሞችን የሚደግፉ አካላትንም አመስግነዋል።

አቶ ይታገሱ ኃይሌም የቤት ዕድሳት ዕድል ከገጠማቸው መካከል ሌላኛው ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብና መድሃኒት፣የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ቤታቸውን አድሶላቸዋል። ክረምት በመጣ ቁጥር ወደ ቤታቸው የሚገባው ጎርፍ ኑሯቸውን ጎደሎ፣ህይወታቸውን ምስቅልቅል አድርጎባቸው ያውቃል።ዝናብ በዘነበ ቁጥር ውሃው ቤት ውስጥ ሲገባ በማስታጠቢያ እያወጡ መድፋት ዕለታዊ ስራቸው እንደነበር ያስታውሳሉ።

አቶ ይታገሱ፤ "በጎርፉ ምክንያት የቤቴን መውጫ በር በሌላ በኩል ለማድረግ ስሞክር ዝናቡና ብርዱ በጆሮዬና በአፍንጫዬ ይገባ ነበር።" ይላሉ ትናንታቸውን ሲያወሱ፤ በጓሯቸው ውስጥ የገባው ውሃ ለጤና ችግር ዳርጓቸዋል።አሁን ያ ሁሉ መከራና ስቃይ ታሪክ ሆኖ አልፏል።ለዚህ ቀን ያደረሳቸውን ፈጣሪ ምስጋናቸውን ይቸሩታል።

"የተሰራው ቤት በጣም ቆንጆ ነው። ነገር ግን በፊት ከነበረው ስፋቱ ቀንሷል። የጎርፉ ጉዳይ ክረምት ሲመጣ የሚገባት ሁኔታ አልተቀረፈም። ይህንን ጉዳይ ቤቱን የሰሩልን እንደሚያስቡበት አልጠራጠርም" ሲሉ ተናግረዋል። አሁን የሌለን ማድቤትና መጸዳጃ ቤት ነው። ይህንንም ችግር አሰሪው አካል እንደሚፈታው እርግጠኛ ነኝ ብለዋል።

እድገታቸው አዲሱ ሚካኤል አካባቢ ለሆኑት አቶ ወንድሙ ገብረ እየሱስም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብና መድሃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ቤት አድሶላቸዋል።

"ቤቶቹ በአፄ ኃይለ ስላሴ ዘመን የተሰሩ በመሆናቸው እድሳት ተደርጎላቸው አያውቁም። ለመኖር በጭቃ መጠገን ያስፈልጋል ይላሉ። ከ1998 እስከ 2000ዓ.ም ባለው ጊዜ በልማት ትነሳላችሁ ተብለው በጭቃ እንዳይሰሩ ተደርገው እንደነበር ያወሳሉ። በዚህም ቤቱ ዝናብ በዘነበ ቁጥር የልጆቻቸው ደብተር፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ በጎርፍ በመበላሸቱ የወደሙትን ንብረቶች የመተካት አቅም የለኝም" ይላሉ።

የቤታቸው አሰራር ውሃ ልክ የሌለውና በጭቃ የተሰራ እንዲሁም የቆየ በመሆኑ ከፓስተር አካባቢ የሚመጣው ፍሳሽ ወደ ግቢያቸው ይገባ ነበር። በዚህም ከመፋሰሻ ቱቦው የሚመጣው ሽታ ለጤንነታችን አስጊ ደረጃ ላይ በመድረሱ ለሚመለከተው አካል እንዲሰራ ከሌሎች ጋር በመሆን አመልክተን ነበር። ነገር ግን በጊዜው የነበረው አካል ወደ ቤት የሚገባውን ጎርፍ እያዩ በዝምታ አልፈውን ነበር።

አሁን ያለው የመንግስት አካል ችግራችንን ተረድቶ በአካል በመምጣትና በማየት እያሳለፍን ያለውን ስቃይ ተረድቶ ለሚመለከተው አካል አሳውቀን እንዲሰራላችሁ እናደርጋለን ብለው ቃል ገቡልን። ቃላቸውንም ጠብቀው የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ዣንጥራር አባይ እንዲሰራ የመሰረት ሥራውን አስጀመሩልን። ለዚህ ክቡር ሥራ ፈጣሪ እንደችሎታቸው የሚፈልጉትን ያሳካላቸው ሲሉ መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

# የሠላም ስምምነቱ፡-

## - አፍሪካ ችግሮቿን ለመፍታት የማንም ጣልቃ ገብነት እንደማያሻት ማሳያ ነው
## - የኢትዮጵያን ህዝብ የተለመደ አብሮነት ሊያስቀጥል የሚችል ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በፌዴራል መንግስት እና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሠላም ስምምነት አፍሪካ ችግሮቿን የማንም ጣልቃገብነት ሳያስፈልጋት በራሷ መፍታት እንደምትችል ማሳያ መሆኑን የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን አስታወቀ። ስምምነቱ የኢትዮጵያን ህዝብ የተለመደ አብሮነት ሊያስቀጥል የሚችል እንደሆነም ተመላክቷል።

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አያሌው አህመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረው ግጭት ለአፍሪካውያን ትልቅ ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ ሲሆን፤ አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን ያለምንም ጣልቃገብነት በራሳቸው የመፍታት አቅም እንዳላቸውም ያረጋገጠ ነው።

የሰላም ስምምነቱ የኢትዮጵያን አንድነት የሚያስጠብቅና የህዝቦችን የጋራ የተለመደ አብሮነትን ሊያስቀጥል የሚችል እንደሆነም አቶ አያሌው ተናግረዋል።

አፍሪካ በርካታ ችግሮች ያሉባት አህጉር ብትሆንም፤ የኢትዮጵያ ጉዳይ ወደ ሌሎች አህጉራት ከመሄዱ በፊት ራሴ እፈታዋለሁ በማለት ወደ ራሷ ማምጣቷና በራሷ አቅም ችግርን ለመፍታት የሄደችበት ርቀት የሚያኮራ መሆኑን አቶ አያሌው ተናግረዋል። ይህም የኅብረቱን አቅም ወደ ፊት ሊያጠናክር የሚችልና ትልቅ ትምህርት የሚወሰድበት እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ቀዳዳዎችን ተጠቅመው ለመግባት የሚያስቡ ሌሎች ኢትዮጵያንና ብልጽግናዋን የማይፈልጉ አካላት በር ተዘግቶባቸው ጉዳዩ በአፍሪካውያን መታየቱ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውም ጠቁመዋል።



አቶ አያሌው አህመድ

አፍሪካ ችግሮቿን በራሷ በመፍታት የሌሎች ጣልቃ ገብነት የማይፈለግበትን ሁኔታ አሳይታለች ያሉት አቶ አያሌው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት ለማስቆም እስካሁን የተሄደበት የሰላም ስምምነት ሂደት ለአፍሪካውያንም ትልቅ ትምህርት ሰጥቶ ማለፉንም ነው የገለጹት።

በፌዴራል መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረገው ውይይት ለኢትዮጵያ ህዝብ ጠቀሜታ ያለው፤ የኢትዮጵያን አንድነት የሚያስጠብቅና የህዝቦችን የጋራ የተለመደ አብሮነትን ሊያስቀጥል የሚችል እንደሆነም ነው የተናገሩት።

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን አባል ሠራተኞች በትግራይ ክልል ውስጥ ቢኖሩም ከሁለት ዓመታት በላይ ግንኙነታችን ተቋርጧል ያሉት አቶ አያሌው፤ በአካባቢው ያሉ የልማት ተቋማትም ሆኑ ሠራተኞች ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል። ስምምነቱ ለአገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የልማት ተቋማትም ተጠግነው ወደ ሥራ እንዲመለሱ ያስችላል ብለዋል።

በትግራይ ክልልም ሆነ ጦርነቱ በነበረባቸው አካባቢዎች ሥራ ላይ የነበሩና በግጭቱ ምክንያት ውድመት የደረሰባቸው ተቋማት እንዳሉ የጠቆሙት አቶ አያሌው፤ በጦርነቱ ቀጣና የወደሙ ተቋማት፣ አርሶ አደሩን፣ የኢንዱስትሪ ሠራተኛውንና የመንግስት ሠራተኛውን ነክተዋል፤ ውይይቱ የኢትዮጵያን ህዝብና የኢትዮጵያ ሠራተኞችን ችግር የሚፈታ ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

"ኢትዮጵያ የምትመራው በህግ ነው። ህግ ከተከበረ ጦርነት አይኖርም። ህጉን ሁሉም ወገኖች አክብረው ህገ መንግስቱ ላይ በተቀመጠው መሠረት ተናብበውና በውይይት ሊፈቱ የሚችሉትን ጉዳዮች መፍታት ይኖርባቸዋል" ብለዋል አቶ አያሌው። በቀጣይ ከጦርነት መጥፎነት ትምህርት በመውሰድ ወደ ጦርነት ሊያስገቡ የሚችሉ ነገሮችን መከላከል ይገባል ሲሉም መክረዋል።

ጦርነት በኢኮኖሚውና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን የሚያስከትል ነው ያሉት አቶ አያሌው፣ ደቡብ አፍሪካ ላይ የተደረገው የጋራ ውይይት አስደሳች እንደሆነም ተናግረዋል። ለስምምነቱ ተግባራዊነትም ኢሠማኮ የሚጠበቅበትን ድርሻ የሚወጣ መሆኑን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ በዕድገት ላይ የምትታይ አገር እንጂ ጦርነት ተመልሶ የማይመጣባት እንድትሆን ትብብር ማድረግ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

የሚመለከታቸው ወገኖችና መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ለስምምነቱ ተግባራዊነት፣ የህዝቡን ዘላቂ ሠላምና አንድነት በማስቀደም በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖችና ተቋማት መልሶ ለማቋቋምና ለመገንባት የድርሻቸውን እንዲወጡም አቶ አያሌው ጥሪ አቅርበዋል።

# ለሥራ ውጤታማነት የሠራተኞችን የአዕምሮና ሥነልቦና ደህንነት መጠበቅ ይገባል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ለሥራ ውጤታማነት የሠራተኞችን አዕምሮና ሥነልቦና ደህንነት መጠበቅ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ተጠቆመ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ትናንት "አጠቃላይ የአካልና የአዕምሮ ደህንነት" በሚል ርዕስ ለድርጅቱ አመራሮችና ሰራተኞች ሥልጠና በሰጠበት ወቅት የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የይዘት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ እንደገለጹት፤ ድርጅቱ የጀመራቸውን በርካታ የሪፎም ሥራዎች ዳር ለማድረስ ለሠራተኞቹ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች ተሰጥቷል፤ እየተሰጠም ይገኛል።

አቶ ፍቃዱ፣ የእውቀትና የክህሎት ሥልጠናዎች ጎን ለጎን የሠራተኞቹ የአካል፣ የአዕምሮና የሥነልቦና ደህንነት ወሳኝ ጉዳይ መሆናቸውን በማመን አጠቃላይ የአካልና የአዕምሮ ደህንነት ዙሪያ ለሠራተኞቹ ሥልጠናው መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

ስልጠናውን የሰጡት የዌልነስ ሜዲካል አገልግሎት ኃ/የተ/የግል ማህበር መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ በሥራ ላይም ሆነ በግል ህይወት የተስተካከለ አካላዊና የስነ ልቦናዊ ጤንነት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው አንስተው፤ በአለም ጤና ድርጅት ጥናት መሰረት የአብዛኞቹ የአለማችን ሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት ችግር ላይ መውደቁን አመልክተዋል፡፡

የአካላዊና ሥነልቦናዊ ደህንነት ደረጃ በብዙ ሠራተኞች ዘንድ እምብዛም ትኩረት ያላገኘ ነገር ግን እጅግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ያነሱት ዶ/ር ሰላም፤ ጤናማ አካላዊና ሥነልቦናዊ ቅንጅት ከሌለ አንድ ሰራተኛ በሥራው ውጤታማ እንደማይሆን ተናግረዋል፡፡

በተለይ በሥራ ቦታ በቀላሉ ለጉዳት ተጋላጭ የሚሆኑት እንደ ነርቭ፣ጡንቻና የአከርካሪ አጥንት ላሉ የሰውነት ክፍሎች ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ



እንደሚያስፈልግም መክረዋል፡፡

ዶ/ር ሰላም፣ አጠቃላይ ደህንነትና ጤንነት ሁኔታ አካላዊ ፣የአዕምሮ፣ሥነልቦናዊ ፣የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት እንደሚያጠቃልል አስገንዝበው፤ ስለ አካላችን፣አዕምሯአችንና ሥነልቦናችን ደህንነት ግንዛቤ ካለን "ጤናችን በእጃችን ነው" ብለዋል።

የስፖርት ሳይንስ ባለሙያ የሆኑት አቶ ዮናስ የሺጥላ በበኩላቸው፤ አካላዊ፤ አዕምሯዊ እና ሥነልቦና ደህንነት ለሰው ልጅ ወሳኝ ጉዳይ በመሆናቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ በተለይ የአኗኗር ሥርዓትን ማስተካከል ወሳኝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ከዚህ አንጻር የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ፣ ለጥሩ ተክለቁመና ጥረት ማድረግ፣ በቂ እንቅልፍ መተኛት እና በቂ ውሃ መጠጣት ጤናማ ያደርጋል ያሉት አቶ ዮናስ፤ እነዚህን ነገሮች ደግሞ በቀላሉ ማስተካከል እንደሚቻል ጠቅሰዋል፡፡

እንደ አቶ ዮናስ ማብራሪያ፣ የተክለ ሰውነት መዛነፍ ያጋጠመው ሰራተኛ ቶሎ ቶሎ ስለሚደክም አቅሙን አሟጦ አይጠቀምም፡፡ የምግብ መፈጨትና የአተነፋፈስ ችግር ያጋጥማል፡፡ የሥራ ፍላጎት ይቀንሳል፤ ከዚህም አልፎ ሊታመም ይችላል፡፡ ስለዚህ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ ለአንድ ሰው ጤንነትና ደህንነት ወሳኝ ከመሆን አልፎ በሥራ ውጤታማ እንዲሆን ያግዘዋል፡፡



# በክልሉ ቱሪዝምን ዋነኛ የኢኮኖሚ ምንጭ ለማድረግ እየተሰራ ነው

**ገመቹ ከድር**

ሀረር፡- በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም መስህቦችን ዋነኛ የኢኮኖሚ ምንጭ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ43ኛ ፣ በሀገራችን ለ18ኛ ጊዜ የተከበረው የዓለም የቱሪዝም ቀን በኦሮሚያ ክልል "አዲስ እሳቤ ለቱሪዝም " በሚል በፓናል ውይይት ፣ በጉብኝትና በኪነጥበባት ስራዎች እንዲሁም ቱሪዝምን ለማበረታታት ለተሰሩ ስራዎች ዕውቅና በመስጠት ተከብሯል፡፡

ኦሮሚያ ክልል አፈ ጉባዔ ወይዘሮ ሰዓዳ አብዱራህማን በክብረ በዓሉ ላይ ተገኝተው ንግግር ባደረጉበት ወቅት እንደገለጹት፤ የበዓሉ መከበር ህብረተሰቡ ያለውን ተፋጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶቹን ለዓለም ህብረተሰብ በማስተዋወቅ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን በማጠናከር ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው፡፡

የተጀመሩ ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ዘርፉ በጥናትና በምርምር ተደግፎ የገቢ ምንጭ እንዲሆን ለማድረግ መንግስት በትኩረት እየሰራ መሆኑንም ገልጸዋል።

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ሁሴን ፈይሶ በጉብኝቱ ወቅት እንደገለጹት፤ "ትልቁ ጠላት ድህነት በመሆኑ" ድህነትን ለማስወገድ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ዋነኛ የገቢ ምንጭ በማድረግ ኢኮኖሚን ለማሳደግ ክልሉ እየሰራ ይገኛል፡፡

የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለማጠናከር የተጀመሩ ሥራዎች ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የገለጹት የምስራቅ ሀረርጌ ዞን አስተዳዳሪ ወይዘሮ ሚስኪ መሐመድ በበኩላቸው፤ በዓሉ ህብረተሰቡ ያለውን የቱሪዝም ሀብት በማልማት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ግንዛቤ በመፍጠር የቱሪዝም ሀብቱን እንዲንከባከብ ያደርጋል ብለዋል።

ከአፍሪካ በታንዛንያ ብቻ የሚገኝ የዝሆን ዝርያ በባቢሌ መገኘቱ ህብረተሰቡ የዓለም ትኩረት እንደሚያስገኝለት ጠቅሰው፤ ይህንንም የሀገር ውስጥና የውጪ ጎብኚዎችን በማስጎብኘት የውጪ ምንዛሪ ገቢን ለማሳደግ መንግስት በትኩረት ይሰራል ብለዋል።

ቱሪዝም ማንነትን ከመግለጽ በላይ የኢኮኖሚ ምንጭ ነው ያሉት ወይዘሮ ሚስኪ፣ ለውጡን ተከትሎ በጠቅላይ ሚኒስትሩ መሪነት በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት በተሰራው የአረንጓዴ አሻራ ሥራ ሀረማያን ሀይቅ ወደ ነበረበት መመለስ ችሏል ብለዋል።

ለተገኘው ውጤት ሀረማያ ዩኒቨርሲቲና ህብረተሰቡ ላደረጉት አስተዋጽኦ ምስጋና ያቀረቡት ወይዘሮ ሚስኪ፣ የምንሰራውን ስራ ለትውልድ ተሻጋሪ ለማድረግ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል።

ክብረ በዓሉ በፓናል ውይይት፣ ቱሪዝም መስህብ ቦታዎች በመጎብኘት ሲካሄድ ምሥራቅ ሀረርጌ የሚገኙ ጥንታዊ መንደሮች ፣ ትክል ድንጋይ፣ 1ሺ 416 ዓመት ያስቆጠረ ጥንታዊ መስጅድና በትልቅ ጥረት ወደ ነበረበት ቦታ የተመለሰ የሀረማያ ሀይቅ ተጎብኝተዋል።

ታሪካዊ ቦታዎች፣ ከመቶ በላይ ዱር እንስሳ ዝርያ የሚገኙበት ደን፣ ከሃያ ሰባት በላይ ማዕድናት ሀብት ፣ ከ500 በላይ ዋሻዎችና ሌሎችም የቱሪዝም መስህቦችን በማስተዋወቅና በመንከባከብ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲውሉ ለማድረግ የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል።

ቱሪዝምን ለማበረታታት በዞኑ የሚገኙ ዋሻዎችን በተመለከተ ለጎብኚና ለህብረተሰቡ በቂ መረጃ ተደራሽ ለማድረግ በዋሻ ጥናት ባለሙያ አቶ ናስር አህመድ የተጠና መጽሐፍ በዕለቱ ተዋውቋል፡፡

መጽሐፉ በክልሉ የሚገኙ 321 ዋሻዎች ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ እንድውሉ የሚያደርግ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ናስር፣ ስራው የዋሻውን ነባራዊ ሁኔታ ለህብረተሰቡና ለጎብኚ ግልጽ በማድረግ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ለማዋል የሚደረገውን ጥረት ውጤታማ ለማድረግ ትልቅ ሚና አለው ብለዋል፡፡

ዜና

# የመንግስት የኮሙኒኬሽን ሥራዎች የሰላም ስምምነቱን ድንጋጌዎች ያከበሩ መሆን እንዳለባቸው አገልግሎቱ አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የመንግስት የኮሙኒኬሽን ሥራዎች በፌዴራል መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ድንጋጌዎች ያከበሩ እና የሕዝቦችን ወንድማማችነት እና አብሮነትን በሚያጠናክር መልኩ መከናወን እንዳለባቸው የኢፌዲሪ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አሳሰበ፡፡ አገልግሎቱ ከክልል እና የከተማ መስተዳድር የኮሙኒኬሽን ተቋማት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይቷል፡፡

በአዲስ አበባ የተካሔደውን የውይይት መድረክ የመሩት የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሠ ቱሉ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የሚደረጉ የመንግስት የኮሙኒኬሽን ሥራዎች የሰላም ስምምነቱን ድንጋጌዎች ያከበሩና የሕዝቦች ወንድማማችነትና አብሮነትን በሚያጠናክር አኳኋን መሆን እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡

የውይይቱ ዓላማ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ተቋማት የሠላም ስምምነቱ መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ የተግባቦት ሥራ እንዲሰራ ለማድረግ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በውይይቱ ሕዝቡ ወቅታዊና ትክክለኛ የመንግሥት መረጃዎችን እንዲያገኝ በኮሙኒኬሽን መዋቅሩ መከወን ስለሚገባው ጉዳይ እንዲሁም ግጭት ቀስቃሽና የጥላቻ ንግግር በሚወገድበት ሁኔታ ላይ መወያየት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ተቋማት የተናበቡ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ የመንግሥት መረጃዎችን ለሕዝቡ ተደራሽ በማድረግ የኅብረተሰቡን መረጃ የማግኘት ፍላጎት ማረጋገጥ እንዳለባቸውም ዶክተር ለገሰ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሐመድ እድሪስ በበኩላቸው፤ የኮሙኒኬሽን እና የሚዲያ ተቋማት ተናብበው ከጥላቻና ግጭት ቀስቃሽ የፀዳ መረጃ ለኅብረተሰቡ በማድረስ የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት ተግባራዊነት እንዲያረጋግጡ አስገንዝበዋል፡፡

አያይዘውም የመንግስት የኮሙኒኬሽን ተቋማት የተጀመረውን ሀገራዊ የሰላም ሂደት ኅብረተሰቡ በአግባቡ እንዲረዳው ለማድረግ መስራት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል፡፡



ሕዝቡ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የመንግሥት መረጃዎችን በፍጥነት እንዲያገኝ፣ የሕዝቦች አንድነትና ወንድማማችነት እንዲጎለብት፣ በግጭት ሳቢያ የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ በመገንባት ረገድ ወቅታዊ መረጃዎችን አግኝቶ ተሳትፎ እንዲያደርግ ለማድረግ የተጠናከሩ የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን እንደሚሠሩም ተሳታፊዎቹ አረጋግጠዋል፡፡

በውይይቱ ከሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የተውጣጡ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ተቋማት መሪዎችና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፡፡

# የተፈጥሮ ማዳበሪያ የምርት ጭማሪን በማሳደግ አርሶ አደሩን እየጠቀመ ነው

**አዲሱ ገረመው**

ደቡብ ሜጫ፡- በምዕራብ ጎጃም ዞን ደቡብ ሜጫ ወረዳ ያሉ አርሶ አደሮች ከተፈጥሮ ማዳበሪያ የምርት ጭማሪ በማግኘት ተጠቃሚ መሆናቸው ተገለጸ፡፡

በምዕራብ ጎጃም ዞን የደቡብ ሜጫ ወረዳ ፈለገሀይወት ቀበሌ ግብርና ጽህፈት ቤት ተወካይ አቶ አትንኩት አላምረው፤ የውሃና መሬት ሀብት ማዕከል ጉርፍን ለማስቀረት፣ የተራቆተውን መሬት ለማልማት የተፈጥሮ ሀብትን ከምርምር ጋር በማያያዝ አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን በዘረጋው “የመማሪያ ተፋሰስ” ፕሮጀክት የተፈጥሮ ማዳበሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ዙሪያ ለአርሶ አደሩ ግንዛቤ መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡ አርሶ አደሩ በተሰጠው የግንዛቤ ሥራ ወደ አገር በቀል ሥራ እንዲያዘነብል በመደረጉ የምርት ጭማሪንና የመሬትን ለምነት ከፍ ማድረግ እንደተቻለ አስታውቀዋል፡፡

እንደ አገር ባጋጠመው የማዳበሪያ ግብዓት እጥረትና የዋጋ ንረት ምክንያት የአካባቢው አርሶ አደሮች የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) የማዘጋጀት ሥራ ላይ መሆናቸውን አቶ አትንኩት ጠቅሰዋል፡፡ በቀበሌው 10 ሺህ 75 አባወራና እማወራ ያሉ ሲሆን፤ በተያዘው የምርት ዘመን አንድ አባወራ ቢያንስ 30 ሜትር ኪዩብ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከተለያዩ ተረፈ ምርቶች እንዲያዘጋጅ በተደረገው ንቅናቄ 25 ሺህ 250 ሜትር ኪዩብ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማዘጋጀት ተችሏል ነው ያሉት፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀማቸው ያለ አግባብ የሚወጣውን ወጪ እንደቀነሰ፤ ምርታቸውም እንደጨመረና መሬታቸውም ለም መሆን እንደቻለ ገልጸዋል፡፡ ተሞክሮውን ወደ ሌሎች አካባቢዎች ለማስፋት “የአርሶ አደሮች በዓል” የሚል ሁነት በየጊዜው እየተካሄደ እንዳለና በርካታ አርሶ አደሮች እርስበርስ በመማማር ምርታቸውን እያሳደጉ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ የተፈጥሮ ማዳበሪያ መለመድ አገራዊ ፋይዳው ከፍ ያለ እንደመሆኑ መጠን ተሞክሮው መስፋፋት እንዳለበትም ነው የጠቆሙት፡፡

በደቡብ ሜጫ ወረዳ ፈለገህይወት ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር አንቲገኝ ውበቱ፤ ቀድሞ የሰው ሰራሽ ማዳበሪያን ይጠቀሙ እንደነበር ጥቅሙም ለአንድ ዓመት ብቻ እንደነበርና ወጪውም ከፍያለ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ በዋጋ ንረቱ ምክንያት መሬታቸውን ጦም የሚያሳድሩበት ጊዜ እንደነበር አንስተዋል፡፡ በግብርና ባለሙያዎች ስልጠና የተፈጥሮ ማዳበሪያው የደረቀውን መሬት በማለምለም የተለያዩ አይነት ምርቶችን ለማምረት እንዳስቻላቸውና በመጠንም፣ በጥራትም ውጤታማ እንዳደረጋቸው ተናግረዋል፡፡

በአካባቢው በተሠራው የሰርቶ ማሳያ ልምድ ወስደው የተፈጥሮ ማዳበሪያን ማዘጋጀት እንደቻሉም ገልፀዋል፡፡

የአካባቢው ነዋሪ አርሶ አደር ጥላሁን ገላዬ በበኩላቸው፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም ከጀመሩ አራት ዓመት እንደሆናቸው ገልጸዋል፡፡ መሬታቸው የሰው ሰራሽ ማዳበሪያን በመተው የተፈጥሮ ማዳበሪያን እየለመደ በመሄዱ ለማዳበሪያ ያወጡ የነበረውን ገንዘብ በመቆጠብ ተጠቃሚ መሆናቸውንም ተናግረዋል፡፡ በሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ምርት ሳይታጨድ ከነበረው ቡቃያ ይልቅ በተፈጥሮ ማዳበሪያ የተዘራው የተሻለ ምርት እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡ ይህም ምርቱ ሲታጨድ የተሻለ እንደሆነም ነው የገለጹት፡፡

አርሶ አደሩ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም ከጀመሩ ወዲህ ከሰብል ምርት ባሻገር የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማልማት ለአካባቢው ሞዴል አርሶ አደር መሆን ችለዋል፡፡

የውሃና መሬት ሀብት ማዕከል በሉማማና ደብራያዕቆብ የመማሪያ ተፋሰስ ለአርሶ አደሩ ባደረገው እገዛ አርሶ አደሩ የተፈጥሮ ማዳበሪያን በስፋት እየተጠቀመ እንዳለ ኢፕድ በሥፍራው ተመልክቷል፡፡

በአካባቢው የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከአረንጓዴ ቅጠላቅጠል፣ ከአመድ፣ ከእንስሳት ፍግና ከተለያዩ ብስባሽ ቁሶች የሚዘጋጅ ሲሆን፤ ውህደቱ ራሱን የቻለ ቅደም ተከተላዊ አሰራር ያለውና አርሶ አደሩ በግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያ በታገዘ ሥልጠና የሚያዘጋጀው ነው፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያው የመሬትን የማምረት አቅም ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ሊያሻሽል የሚችል እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

# ወደ ትግራይ ክልል እርዳታ በብዛት እየገባ መሆኑን አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን አስታወቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በመከላከያ ሰራዊት ቁጥጥር ስር ወዳሉ የትግራይ አካባቢዎች ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ እርዳታ በብዛት እየገባ መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ እና የሰላም አማራጭ ዐቢይ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገለጹ።

70 በመቶ የሚሆነው የትግራይ ክልል በመከላከያ ስር እንደሆነና ወደ እነዚህ አካባቢዎች እርዳታ በብዛት እየገባ መሆኑን አምባሳደር ሬድዋን አስታውቀዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪው አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በትዊተር ገጻቸው ላይ ባሰፈሩት መልዕክት እንደገለጹት፤ ሰሞኑን በ35 ተሽከርካሪዎች የተጫነ ምግብ እና ሶስት ተሽከርካሪዎች መድኃኒት ተጭኖ ሽሬ ገብቷል ብለዋል።

አምባሳደር ሬድዋን እንደተናገሩት፤ ወደ ክልሉ በረራ ተፈቅዷል፤ የተቋረጡ አገልግሎቶች እየተመለሱ ነው፤ ለዚህ ደግሞ የሰላም ስምምነቱ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ዕርዳታን በተመለከተ ምንም ዓይነት መሰናክል አይፈጠርም ያሉት አምባሳደር ሬድዋን፤ አንዳንድ አካላት የአፍሪካውያን ጥበብ በፕሪቶሪያ ያመጣውን ስኬት ለማወክ ሲጥሩ ይታያሉ ሲሉም ገልጸዋል።

በትግራይ ክልል ሰብዓዊ ድጋፎችን በተሻለ ሁኔታ ማቅረብን ጨምሮ አገልግሎቶች ዳግም እየጀመሩ መሆናቸውን አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገልጸዋል።

አምባሳደሩ እንደገለጹት፣ በፓን አፍሪካኒዝም መንፈስና ጥበብ የተገኘው የሰላም ስምምነትና ውጤቱ አንዳንድ አካላትን ባያስደስትም በተፈጠረው እድል የአየር በረራዎች መፈቀዳቸውንና የተለያዩ አገልግሎቶችም እየተጀመሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

# መንግሥት ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አማራጮችን መጠቀም የሚችሉበት ዕድል እንደሚኖር ገልጸዋል።

እስከዚያው ግን ለሰሜን ኢትዮጵያ የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት አራት የየብስ መስመሮች ክፍት መሆናቸውን ኮሚሽነሩ አስታውቀዋል።

ዓለም አቀፍ ተቋማት ለሰሜን ኢትዮጵያ የሰብዓዊ ዕርዳታ ለማቅረብ በተገቢው የዕርዳታ አቅርቦት ስነምግባር ታግዘው ያለገደብ አራቱን የየብስ መስመሮች መጠቀም እንደሚችሉም ገልጸዋል።

አምባሳደር ሽፈራው እንዳስታወቁት፤ ከአራቱ የሰብዓዊ ድጋፍ ማቅረቢያ የየብስ መስመሮች መካከል አንዱ የጎንደር - ሁመራ- ሽራሮ- ሽሬ- አድዋ መስመር ነው። የደባርቅ -አዳርቃይ- ማይጸምሪ- ሽሬ መስመር ሌላኛው ክፍት የሆነ የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት አማራጭ በመሆኑ ለተሽከርካሪዎች ክፍት ሆኗል።

የወልዲያ - ቆቦ አላማጣ - ኮረም መስመር በተጨማሪነት ለአሽከርካሪ ክፍት መሆኑን የገለጹት ኮሚሽነሩ፤ የሰመራ አብዓላ የየብስ መንገድ ለሰብዓዊ ዕርዳታው አቅርቦት ክፍት የሆነ ሌላኛው የየብስ አማራጭ መሆኑን አስታውቀዋል።

የሰብዓዊ ድጋፉን የሚያቀርቡ አካላት በመስመራቸው የሚገኙ የአማራና አፋር ክልሎች ላይም አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያቀርቡ አምባሳደር ሽፈራው አሳስበዋል።

ከዚህ ባለፈ ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ ዕርዳታ ተቋማት በሰሜን ኢትዮጵያ የሚያቀርቡት ድጋፍ ለተገቢው ሰው ደርሷል የሚለው በየጊዜው እየተገመገመ እንደሚሰራ ኮሚሽነሩ ገልጸዋል።

ዕርዳታው ከመሰጠቱ በፊትም ሆነ ከተከፋፈለ በኋላ ስለትክክለኛነቱና ለተገቢው አካል ስለመድረሱ ድርጅቶቹና የፌዴራል መንግሥት የጋራ ክትትል የሚያደርጉበት አሰራር እንዲኖር መግባባት ላይ መደረሱን አስታውቀዋል።

# በሽሬ ዲስትሪክት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የሚገቡ መሆናቸውንም አቶ አልሰን ጠቁመዋል።

አቶ አልሰን እንደጠቆሙት፤ በክልሉ የሚገኙ አንዳንዶቹ የባንኩ ቅርንጫፎች ከአንድ ዓመት በላይ ተዘግተው የከረሙ፣ ለመክፈትም የኦዲት ሪፖርት የሚሹና መልሶ ለማቋቋም ጊዜ የሚፈጁ በመሆናቸው ስራው ጊዜ ሊወስድ ችሏል። ከኦዲት በኋላ ግን መቶ በመቶ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምሩ ገልጸዋል።

በጦርነቱ ምክንያት የባንኮቹ ኮምፒውተሮች፣ የኤቲኤም ማሽኖች፣ ገንዘብ ማስቀመጫዎች እንዲሁም ሌሎች የቢሮ እቃዎች ውድመት ቢደርስባቸውም ባንኩ ከተለያዩ ቅርንጫፎቹ እና ከዋናው መስሪያ ቤት በማጓጓዝ አቀናንሶ እንዲሰራ በማድረግ አገልግሎት የመስጠት ስራ ማከናወኑንም አቶ አልሰን ገልጸዋል።

በአካባቢው ላይ ያለው የሰው ሀይል እጥረት እንዲሁም የኤሌክትሪክ ሀይል መቆራረጥ፣ የኔት ወርክ ችግር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስራዎች ላይ ተግዳሮት መፍጠራቸውንም ነው አቶ አልሰን የገለጹት።

በተመሳሳይም በወልዲያ ዲስትሪክት ካሉት 36 ቅርንጫፎች መካከል በጦርነቱ ምክንያት ስምንቱ ተዘግተው መቆየታቸውን አቶ አልሰን ጠቁመው፤ ከነዚህ ውስጥ ሰባቱ መከፈታቸውንና የቀረው አንዱም በቅርቡ ስራ እንደሚጀመር ተናግረዋል።

በመቀሌ ዲስትሪክት ስር ካሉት 61 ቅርጫፎች ውስጥ ከኮረም እስከ ዋጃ ጥሙጋ ያሉት ሰባት ቅርንጫፎች ማለትም ኮረም፣ ሃሸንጊ፣ አላማጣ፣ ራያ፣ አንሳር፣ ጁሃን፣ ዋጃና ጥሙጋ በወልዲያ ዲስትሪክት ስር ታቅፈው ስራ እንዲጀምሩ የኦዲት ስራና ቅድመ ዝግጅት ስራ እየተደረገባቸው ነው፡፡

30 ዲስትሪክትና 1841 ቅርንጫፎች ያሉት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግጭት አካባቢዎች ተቋርጦ የከረመውን የባንክ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በፍጥነት ለማስቀጠል በከፍተኛ ርብርብ በመስራት ላይ እንደሚገኝም የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የቀያሚ መጽሄት

# አገልግል

ተጠያቂነት እንዲኖር እንተዋቸው

ገጽ 11





ሲስፋፉ የሚገባቸው የመስኖ ቴክኖሎጂዎች

ገጽ 14

የአንድ ጠገራ ብር ቱሩፋት

ገጽ 13

ያሳሰፈ ችግር

ገጽ 17

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች የግንባታ አፈፃፀም የደረሰበት ደረጃ ሲፈተሽ



**የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ የደረሰበት ደረጃ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማዋ የሚስተዋለውን የኅብረተሰቡን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ለመፍታትና የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከዘረጋቸው ሜጋ የልማት ፕሮጀክቶች አንዱ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በተለያዩ ፕሮግራሞች አካቶ በመሥራት በዘላቂነት የመኖሪያ ቤት ችግርን መቅረፍ አንዱና ዋነኛው ተግባሩ ነው። አስተዳደሩም የኅብረተሰቡን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ እውን ለማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽንን በአዋጅ በማቋቋም ሲንቀሳቀስ ቆይቷል።

ኮርፖሬሽኑም በከተማዋ ያለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍ ከ18 ያላነሱ ቅርንጫፍ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቶችን በተለያዩ ሳይቶች ላይ በማደራጀት ባለፉት ሁለት አስርት አመታት ገደማ የተለያዩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ፕሮግራሞችን በመንደፍ ቤቶቹን ለቤት እድለኞች ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም ኮርፖሬሽኑ ለመምህራን የተሰጠውን አምስት ሺ ቤቶችን ጨምሮ በ20/80 ፣ በ10/90 እና በ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች መርሐ-ግብር እስካሁን በጥቅሉ ከ256 ሺ 251 ቤቶች በላይ ሠርቶ በማጠናቀቅ ለባለ እድለኞቹ በማስረከብ ከአንድ ሚሊዮን 281 ሺ በላይ እማወራዎችን እና አባወራዎችን በአገራቸው ላይ ‹‹የኔ››የሚሉት መኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው አስችሏል። ከዚህ ባሻገር በድምሩ 143 ሺ 295 ቤቶች ግንባታን በነባርና በአዲስ የቤት ልማት ፕሮግራም በማካሄድ ላይ ይገኛል።

ይሁን እንጂ ከተማ አስተዳደሩ ሥር የሰደደውን የመዲናዋ ነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት እና ከቤት ፈላጊው ቁጥር አንፃር ገና ብዙ ሥራዎችን መሥራት እንዳለበት የተገነዘበ በመሆኑ ሌሎች የቤት አማራጮችን በጥናት ላይ ተንተርሶ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለውን የመፍትሔ አቅጣጫዎች ለማስቀመጥ በሒደት ላይ ይገኛል። ከነዚህም መካከል ከተማ አስተዳደሩ የመኖሪያ ቤት ችግሩን ለመፍታት ነዋሪዎች በማህበር ተደራጅተው የሚሠሩበት ሁኔታን እንደ አንድ አማራጭ ሊከተለው እንደሚችል በተለያዩ ጊዜ ሲገልጽ ተደምጧል።

ሌላው ደግሞ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቤት ግንባታን ተግባራዊ በማድረግ በአጭር ጊዜና በተመጣጣኝ ዋጋ ግንባታቸው የሚከናወን ተገጣጣሚ ቤቶችን ገንብቶ ለቤት ፈላጊዎች ለማስረከብ በግንባታ ላይ ይገኛል። ከነዚህ መካከል የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ አንዱ ነው። ከሰሞኑ የፕሮጀክቱ አፈፃፀም የደረሰበት ደረጃ ተጎብኝቷል። በጉብኝቱ የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ቶማስ ደበሌ እና የኮርፖሬት ፋይናንስ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ስለሺ አጥናፌ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢኮሥኮ) የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የቤቶች ልማት ማዕከል ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ ሙሉጌታ ፈይሳ በጉብኝቱ ወቅት እንዳሉት፤ ግንባታው በተቀመጠለት መርሐ-ግብር መሠረት እንዳይከናወን በዋናነት እንቅፋት የሆኑት የግንባታ ግብዓት በተለይ የሲሚንቶ አቅርቦት ፣ የወሰን ማስከበር ፣ የክፍያ ጥያቄ ቶሎ አለመመለስ እና የገበያ ዋጋ ንረት ናቸው።

የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ቶማስ ደበሌ በበኩላቸው፤ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት በሚያስችል መልኩ በቤቶች ልማት በኩል ዝግጅት መደረጉን ገልፀው፤ በቀጣይ ፕሮጀክቱንም በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የቅርንጫፍ 10 ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት በዋናነት የሚከታተለው ይሆናል። በዚህም ሙያዊ እና ከግብዓት አቅርቦት ጋር ተያይዞ ያሉ ጉዳዮችን የሚከታተሉ ሁለት ቡድኖች ተቋቁመዋል። በተጨማሪም ፕሮጀክቱ በታቀደለት የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ ጊዜን በአግባቡ መምራት እና ተግባብቶ መሥራት ትልቁን ድርሻ ይወስዳልም ብለዋል።

የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የኮርፖሬት ፋይናንስ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ስለሺ አጥናፌ በበኩላቸው፤ ከግብዓት አቅርቦት እጥረት ጋር ያለውን ችግር ለመፍታት ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጠንካራ ድጋፍ እንደሚያደርግ በመግለፅ፤ "የሚደረገውን ድጋፍ በፍጥነት እና በቅልጥፍና መስመር ማስያዝ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ነው" ሲሉ አስገንዝበዋል። የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ፕሮጀክት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቤት ግንባታን ተግባራዊ በማድረግ በፈጣን የቤት አቅርቦት የከተማችንን ነዋሪ የቤት ፍላጎት ለማሟላት የታለመ ፕሮጀክት እንደሆነ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ፕሮጀክት ዴቨሎፕመንት ማኔጅመንት ማዕከል ሥራ አስፈፃሚ አቶ ወገን ሰለሞን በበኩላቸው፤ እየተገነቡ ካሉ የባለ ሁለት ወለል (G+2) እና የባለ አራት ወለል (G+4) ህንፃዎች በተጨማሪ የባለ ዘጠኝ ወለል (G+9) ተገጣጣሚ ቤቶችን ለመገንባት የሚያስችል አዲስ ቴክኖሎጂ ከሰርቢያ ተሞክሮ በመውሰድ ተግባራዊ ለማድረግ ጫፍ መድረሱን ገልፀው፤ ፕሮጀክቱም ዕውን እንዲሆን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ልዩ ድጋፍ እንዲደረግ አሳስበዋል።

## ነፃ ሃሳብ

# ሰላም ተናፋቂዋ ጉዳያችን!

**ደዋይዋ ጓደኛዬ የትግራይ ክልል ተወላጅ ናት። የቤተሰቧን በተለይ የወንድም የእህቷን ወሬ ከሰማች ሁለት ዓመት ሲሞላት ምንም አልቀራትም። ያስለቀሳት፣ የደስታ ሲቃ ያስያዛት፣ ተስፋም የሰጣት ከዚህ በላይም የሆነ ምክንያቷ ምን እንደሆነ አስታወስኩ**



በፍሬሕይወት ተሰማ

የአገራችን መንግሥትና የሕወሓት እርቅ በደቡብ አፍሪካ ተፈራረሙ ተብሎ ሲነገርና ጉዳዩ ዓለም አቀፍ ዜና ሲሆን እንደብዙ ኢትዮጵያውያን ግራ ተጋባሁ።ምን እንደሆነ የማላውቀውም ስሜት ተሰማኝ። ምክንያቱም ከሁለት ሶስት ቀናት በፊት ከምዕራባውያን ማስፈራሪያና ፍራቻን የሚያጭሩ የሚመስሉ አስተያየቶች ሲሰጡ ስለተመለከትኩ ነው። እንዴት ሁሉም ጉዳይ እንዲህ በስምምነት አለቀ ብዬም አሰብኩና ተገረምኩ። እናም ልዑሉንና ገናናውን አምላኬን የማይቻለውን ስላስቻለ እንዲሁም በኢትዮጵያ ጉዳይ እንደገናም ጣልቃ ስለገባ ከቤተሰቤ ጋር ተንበርክከን አመሰገንነው አወደስነውም።

ለወትሮው በእንዲህ ያለ ሁኔታ የቅርብ ወዳጆቼ ጋር ደውዬ ደስታዬን የማካፍል ቢሆንም በዚህ ጊዜ ግን ለራሴም ለመረዳትና በጥያቄ የተሞላውን አእምሮዬን ለማሳመን ጊዜ ወሰድኩ። በዚያ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ግን መቆየት ያላስቻላት ጓደኛዬ ደወለችልኝና "ሰማሽ አይደል? ቅዱስ እግዚአብሔር ይመስገን! ልዑሉ አምላካችን ይመስገን!" ከማለቷ የደስታ ሲቃ ሲያንሰቀስቃት ስሰማ ደነገጥኩ።

እውነት ነው ደዋይዋ ጓደኛዬ የትግራይ ክልል ተወላጅ ናት። የቤተሰቧን በተለይ የወንድም የእህቷን ወሬ ከሰማች ሁለት ዓመት ሊሞላት ምንም አልቀራትም። ያስለቀሳት፣ የደስታ ሲቃ ያስያዛት፣ ተስፋም የሰጣት ከዚህ በላይም የሆነ ምክንያቷ ምን እንደሆነ አስታወስኩ። እየተገረምኩ አናግሬያት ስልኩን ከዘጋሁ በኋላ ባለፉት ሁለት ዓመታት ያሳለፈችውን ውጣ ውረድና መከራ አስታውሼ እኔም በሀዘንና በለቅሶ እንዲሁም በአዲስ ምስጋናና ተስፋ ተሞላሁ። ይህቺው ጉደኛዬ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ጦርነቱ እንደተጀመረና መንግሥት መቀሌን እንደተቆጣጠረ እንደማንኛውም ሰው እረፍት ተሰምቷትና ተስፋ አድርጋም ነበር። ነገር ግን የስጋ ነገር ነውና ሁሉም ቤተሰቧ ሰላም መሆኑን ለመስማት በጉጉት ከዚያ የሚመጣ ወሬ ትጠብቅ ነበር። እውነትም ሆኖ ራያ አካባቢ ያሉት ወንድሞቿም ሆኑ ሄዋነ ያለችው እህቷ ሰላም መሆናቸውን መስማታችን እረፍት ሰጠን።

መቀሌ አካባቢ ወንድም እና እህት ቢኖራትም በጊዜው በዚያ አካባቢ ጦርነት ስላልነበረ እጅግም አልሰጋችም ነበር። ከእርሷ ጋር በተለያዩ ጊዜያት በትግራይ የተለያዩ ቦታዎች ዘመዶቿን ተዋውቄ፤ በተለያየ ጊዜ አስተናግደውኝ ስለሸኙኝ እኔም እረፍት አገኘሁ። በተለይ መኾኔ የሚባለው ቦታ ሄደን ከአስር በላይ የሚሆኑ ቤተሰቦቿ ሊያገኟት ከገጠር መጥተው ሲጨዋወቱ፤ እኔ መካከላቸው ካለሁ እኔም ጨዋታቸው እንዲገባኝ ወዲያውኑ ቋንቋቸውን ወደአማርኛ ይቀይሩት እንደነበር አስታውሳለሁ። እንግዳ ተቀባይነታቸው ኢትዮጵያዊ ፍቅራቸው ይማርከኝም ነበር። በወቅቱ አንዳንዶቹ አማርኛ መናገር የማይችሉ መሆናቸውን ስረዳና እንዲጫወቱ ብዬ ከአጠገባቸው ዞር ስል እንደገና በቋንቋቸው ማውራት ይጀምራሉ። እኔም "እባካችሁ በሚመቻችሁ ቋንቋ አውሩ፣ ደሞኮ ትግሪኛን ለመስማት ቀላል ነው፣ አማርኛ ማለት ነው" ስላቸው "ከመቼ ወዲህ ነው ቋንቋውን የማይናገር እንግዳ እያለ እርሱን ቁጭ አድርገን በቋንቋችን የምናወራው?" ይሄ አይደረግም ሲሉ አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ የነገሩኝን በፍጹም አልረሳውም። ከዚህ ደግነትና ፍቅራቸው የተነሳ ደህንነታቸውን መስማቴ እረፍት ሰጠኝ። ድግሜም ልዑል አምላኬን አመሰገንኩ።

ነገር ግን በሳምንቱ አካባቢ መቀሌ ይኖር የነበረ በግል ሥራ የሚተዳደር ወንድሟ በተባራሪ ጥይት ተመትቶ ማረፉን ተረዳች!! ይህ ወንድሟ እንደልጇ ያሳደገችው ሲሆን የግል ድርጅቷን በኃላፊነት የሚመራ ነው። እኔም በተለያየ ጊዜ ትግራይ ስንሄድ ያገኘሁት ሲሆን በተለይ ጓደኛዬ ከዘመዶቿ ጋር ስትጫወት እኔና እርሱ ወጣ ብለን በየከተማው አንዳንድ ቦታዎች ያስጎበኘኝና ታሪክም ያጫውተኝ ስለነበር በብዙ እንቀራረብ ነበር፤ ቀልድና ጨዋታ የሚወድ ስለሆነ በተለያዩ ነገሮች ስደናበር ሙድ ይዞ ስቆ ያስቅብኝ ነበር። ጓደኛዬ ሀዘኗ እጅግ ከባድ በመሆኑ የሆነውን ማመን አቃታት!! መቀሌ በተረጋጋችበት ወቅት ከቤቱ ወጥቶ ትልቅ እህቱ ቤት እየሄደ ነው ተኩሱ ከየት እንደሆነ ያልታወቀ ጥይት ነው የመታው።

ከሁሉ የሚገርመው ሀዘንተኞች እርማቸውን ሊያወጡና ሊያጽናኗት ሲመጡና የእልህ ንግግር ሲናገሩ እርሷ "የሞተው አንድ ኢትዮጵያዊ ነው ከዚህም ከዚያም ወንድም ወንድሙን ገድሏል፤ ተቆሳስለናል ተጎዳድተናልም እኔ ብቻ ሳልሆን የኢትዮጵያ እናትና እህት ታልቅስ" ብላ ትመልስላቸው ነበር። የምታዝነው ምክንያት በሌለው፣ በማያስፈልገው ጦርነት እንጂ 'የወንድሜ ገዳይ እከሌ ነው' አትልም ነበር። በርግጥ ከዚህ ማንነቷ የተነሳ በዘመናት ውስጥ ብዙ ወዳጆች በዙሪያዋ ቢኖሩም፤ በዚህ ሁኔታዋ ግን ሰው ሁሉ እጅግ ተደነቀ። እውነቷን ነው እንዴ ብሎ በመጠራጠርም ማመን ያልቻለውም ብዙ ነበር። በዚህም ምክንያት ብዙዎች ለቅሶ ሊደርሱና ከጎኗ መሆናቸውን ሊያሳዩ መጥተው "ልናጽናናሽ መጥተን አጽናንተሽ መለስሽን" ብለዋታል።

> **ሩቅ ሆኖ ለሚያጋግል የጦርነቱ ነበልባል አይፈጀውምና ስቃዩን ሊገነዘበው ፈጽሞ አይችልም። በጦርነቱ ውስጥ ለነበረ ግን ወላፈኑ የማቃጠል ጥግን በደንብ ያውቀዋልና ስለሰላም መሻቱ እጅጉን ግዙፍና የተለየ ነው**

ይህች ጓደኛዬ ጠንካራ የቢዝነስ ሰው ከመሆኗም በላይ አንባቢ፣ አሳቢ፣ ለኅብረተሰብ መልሶ በመስጠት የምታምን፣ ለውጥ የምትናፍቅ፣ ተስፋ የምታደርግ፣ በነገር ሁሉ መልካሙን ማየት የምትመርጥ ናት። ከአጭር ጊዜ ግለሰባዊ ጥቅም ይልቅ የረጅም ጊዜና የኅብረተሰብ ጥቅም የሚያማልላትም ናት። በሀገራችን ለውጥ መጥቶ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ስራ ፈጣሪዎችን ማበረታታት የሚል ሀሣብ ሲያፈልቁ የድርጅቷን ሠራተኞች ሰብስባና ምሳ ጋብዛ አዲስ ተስፋና አዲስ ጅማሬ እንዳለ አብሥራ ከሥራው በተጨማሪ በግል የራሱን ፈጠራ ይዞ የሚመጣን ሠራተኛ በፋይናንስ እንደምታግዝ ቃል ገብታለች። ለቃሏ የተገዛች ስለሆነችም ቃሏን በተግባር አውላለች።

ሀገራዊውን ለውጥ በሙሉ ልቧ ተቀብላና ወደውስጧ አስርጻ ሠራተኛውም በአዲስ ተስፋ በግል ሕይወቱ፣ በሥራው እንዲሁም ለሀገሩ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ላይ እንዲበረታ አሳሰበች። በአስተሳሰብ ላይ በተለይ ወጣቱ ላይ መስራት ይገባል በሚል 'ሀልዮተ ዓምባ' የሚል ስብስብ ፈጥራ ወጣቱ በመነጋገር ችግርን በውይይት መፍታት፣ እንዲሁም ሃገራችን ካለችበት የሞራል ዝቅጠት እንዴት መውጣት ትችላለች በሚል በትምህርት ጥራት፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ እና በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ በየሳምንቱ ተገናኝቶ ሃሣብ የሚያነሳ፣ የሚወያይ፣ የሚከራከርና የሚጽፍ ቡድን መሠረተች።

ይህ ስብስብ ኮሮና መጥቶ እስኪቀዛቀዝ ድረስ ለሁለት ዓመት አካባቢ በስኬት ዘለቀ። ጦርነቱ ለሁለተኛ ዙር በተጀመረ ሰሞን ተጠርጣሪዎች በጥቆማ ይታሠሩ ነበርና እርሷም ከቤቷ ተወሰደች። ማንነቷን የምናውቅ ሰዎች ልባችን ቢደማምና ሁኔታው ለርሷና ለቤተሰቧ አስደንጋጭ ቢሆንም፤ የጠቆመባት ሰው ሀሰተኛና ለውጡን መደገፏና ተስፋ ማድረጓ ያላስደሰተው የድርጅቷ ሠራተኛ መሆኑን ማመን ከብዷት ነበር።

ነገር ግን ከወንጀል ነጻ መሆኗ ተረጋግጦ ከ20 ቀን እስር በኋላ ስትወጣ ሊያጽናኗት የሚመጡ ወዳጅ ዘመዶቿ በመኪናዋ ቁልፍ መያዣ ላይ ያለውንና ሰው በዶ/ር ዐቢይ ፍቅር ሲናውዝ እርሷም የገዛችውን የርሱን ፎቶ አሁንም ይዛ መታየቷን ማመን አልቻሉም። "አሁንም? እንዲህ ትላለች እንዴ እና እርሷንስ ይበላት" ለሚለው አስተያየታቸው የምትሰጠው መልስ መንግሥት ምን አደረገኝ? ይህ ሁሉ ጉዳት አላስፈላጊው ጦርነት ያመጣብን ችግር ነው እንጂ ነበር መልሷ። ሰው ናትና ስትታሰር እንዴት ቂም አትይዝም? እንዴት አትማረርም? እንዴት አይከፋትም? እውነትም ለማመን የሚከብድ ነው። ነገር ግን እርሷ ማሰብና ማመዛዘን የምትችል፣ ላመነችበት የምትቆም፣ ነገርን ከራሷ አንጻር ብቻ የማታይ በሳልና ሩቅ አሳቢ ሰው ናትና የሆነው ይሄው ነው።

ይህም እንዳይበቃ ያው የጠቆመባት ሰው በሥራ ቦታዋ የመንግሥት ተቆጣጣሪዎች እየላከ ይህንና ያንን ማስረጃ እያስጠየቀም ስቅሏን አሳይቷል። በዚህም የተነሳ ከጭንቀትዋ የተነሳ ጤናዋን ማጣት ጀመረች። ዳግም እንዳያሳስራት በመስጋትም በፍርሃት ራደች። ስለሆነም የዛሬ ሰላሳ ዓመት አገሯ ላይ ለመስራት ጓዝዋን ጠቅልላ የመጣች፣ አገሯ ውስጥ ብዙ ደክማ የተሳካላት ሴት፣ ከአገሯ እንደገና ለመሰደድ ተገደደች። ጦርነት ጣጣውና ጉዳቱ ብዙ ነውና ለዚህ ነው ይህ የሰላም ስምምነት ከፖለቲከኞች ፍላጐት በላይ ነው በሚል ይህን ሃሳብ ለማካፈል የፈለግሁት።

በተከሰተው ጦርነት በየጦር ቀጣናው ያሉት ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍል ያሉ ወገኖችም በእጅጉ ውድ ዋጋ ከፍለዋል። ሕይወታቸውን፣ ጤናቸውን፣ ሥራቸውን፣ ቤተሰባቸውን ያጡ ብዙ ናቸው። ለረጅም ዘመን ያፈሩት ጥሪት ከእጃቸው በኖ የጠፋባቸውና ሕይወት እጅግ ፈታኝ የሆነችባቸውንም ቤት ይቁጠረው። ለዚህ ነው ይህ የሰላም ውል ሲፈረም እኔን ጨምሮ ብዙዎች እጅግ የተደነቁትና በእፎይታ ያነቡት።

ለሁለት ዓመት የናፈቁትን ሰላማዊ ታናሽ ወንድማቸው መቃብር ላይ ሄደው እርማቸውን ለማውጣት ከመፈለግ፣ የአዛውንት እህት፣ ወንድም፣ እናት አባትን ትከሻ አቅፎ ለመሳም ከመጓጓት፣ በረሃብና በጦርነት የተጐዱትን ወገኖች ለመደጐም ከመፈለግ የተነሳ። ከዚህም አልፎ ዘመናቸውን በሙሉ የደከሙበትን ሥራ በሰላም ለማስቀጠል ከመፈለግ፣ በወንድማማችነትና በመተማመን እንደወትሮው ከሌላው ሕዝብ ጋር በሰላም ለመኖር፣ ዳግም ውሾን ያነሳ ብሎ ምህረት አድርጐ የሰላም ኑሮን ለመኖር ከመፈለግ የተነሳ።

ሩቅ ሆኖ ለሚያጋግል የጦርነቱ ነበልባል አይፈጀውምና ስቃዩን ሊገነዘበው ፈጽሞ አይችልም። በጦርነቱ ውስጥ ለነበረ ግን ወላፈኑ የማቃጠል ጥግን በደንብ ያውቀዋልና ስለሰላም መሻቱ እጅጉን ግዙፍና የተለየ ነው። ከጦርነት ብዙ ተጎድተናልና ሰላማችንን አታቃሉብን፣ አታወሳስቡብን፣ ለኛ ልዩ ትኩረት የምንሰጠውና አንገብጋቢ ጉዳያችን ነውና!

# ማህደረ ጤና

## "በጦርነት የተጎዳ አእምሮ የምታክሚው በውይይት ነው "

**- ዶክተር ማስተዋል መኮንን -የሥነ ልቦና ባለሙያ**

እፀገነት አክሊሉ

ሁል ጊዜም በጦርነት ቀዳሚ ተጎጂዎቹ ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አቅመ ደካሞች ናቸው። የተለያዩ ጉዳቶች የሚደርሱትም በእነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ነው ። በተለይም ሰዎች በጦር ቀጠና ውስጥ መኖራቸው በራሱ ከባድ የሥነ ልቦና ጫና ከመፍጠሩም ባሻገር በውትድርና ላይ ተሳትፈው መገኘታቸው ደግሞ የማይሽር የሥነ ልቦና ጠባሳ ጥሎባቸው ያልፋል ።

ሰዎች በጦርነት ቀጠና ውስጥ ሲኖሩ ለተለያዩ ሥነ ልቦናዊም ሆነ መሠረታዊ ፍላጎቶችን የማጣት ችግር ይገጥማቸዋል። በተለይ በጦርነት ቀጠና ውስጥ መኖር መሠረታዊ ነገሮች እንደ ምግብ ልብስ መጠለያ እና የጤና አገልግሎት እንዳያገኙ ያደርጋል። ከሚኖሩበት ቦታ ወደ ሌላ ሊያውም ባልተረጋጋ መንፈስ የመፈናቀል ሁኔታ ሲደርስባቸው በስጋት ውስጥ ለመሆን ይገደዳሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከቤተሰብ መነጠል ሌላ አስከፊ የሥነ ልቦና ጫና የሚፈጥር ነገር ነው።

በተጨማሪም በካምፖች ውስጥ በጋራ መኖር ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ተጋላጭ የሚያደርግ ስለሆነ ሰዎች እንዳይረጋጉ የራሱን ድርሻ ይወጣል። በተለይም ሕጻናትን ታዳጊዎች በመማሪያና በመቦረቂያ እድሜያቸውም ከትምህርት ይገለላሉ ከቤተሰብ ጋር ከተነጠሉ ለጭንቀት ይዳረጋሉ። በጦርነቱ ምክንያት የአካል መጉደልና ሕይወት ላይ አደጋ ሊያጋጥማቸው ይችላል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሲደመሩ ደግሞ ለፍርሀትና ሰቆቃ ለጭንቀትና ድብርት ይጋለጣሉ።

ሰዎች በጦርነት ቀጠና ውስጥ መኖራቸው ከሚያስከትለው ሥነ ልቦናዊ ጫና በተጨማሪ ተገደው ወይም ተታለው በወታደርነት፣ በጦር ቀጠና ውስጥ በሰራተኝነት እንዲሁም በሰላይነት እና በመሳሰሉት መልኩ በግዳጅ ያገለግላሉ። ይህም ለከፋ የጤና፣ የሥነ ልቦናዊ እና ማሕበራዊ ችግሮች ይዳርጋቸዋል።

በጦር ሜዳ ውሎ ላይም ቢሆን የሚያሠቅቁ ነገሮችን ማየት፣ ፆታዊ ጥቃት፣ አዕምሮን ለሚጎዱ ነገሮች (ኬሚካሎች) መዳረግ (በተለይም የሚያደፋፍሩ መድሃኒቶች ከተሰጣቸው) በእነዚህ ሰዎች ላይ ስር የሰደደ የሥነ ልቦናዊና ማሕበራዊ ቀውሶች መከሰት በወደፊት ሕይወታቸው ላይ ጥቁር ጠባሳን ያስቀምጣል።

በዋነኛነት የሚታዩ ሥነልቦናዊ እና ማህበራዊ ችግሮች መካከል ድባቴና ጭንቀት፣ ድህረ አደጋ ጭንቀት ፣ የመገለል ችግር፣ ጥላቻ፣ጥቃት አድራሽ መሆን፣ የኀዘን ስሜት ውስጥ መሆን፣ ራስን ዝቅ አድርጎ መሳል፣ ራስን ከሌሎች መነጠል ከብዙ በጥቂቱ ናቸው።

የሥነ ልቦና ባለሙያዋ ዶክተር ማስተዋል መኮንን እንደሚሉት ሥነ ልቦና ወይም ደግሞ የአእምሮ ጤና ብዙ ነገሮችን የያዘና የግለሰቦችን አስተሳሰብ ማህበራዊ መስተጋብር ስሜትን አብሮነትን እንዲሁም ባህሪያትን አጠቃሎ የሚይዝ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ሰዎች የሥነ ልቦና ወይም ደግሞ የአእምሮ ጉዳት ሲደረስባቸው በሕይወታቸው በርካታ የሚያጧቸውም ነገሮች አብረው ይመጣሉ፡፡

የሰዎች ሥነ ልቦና በተለያዩ ምክንያቶች ሊጎዳ አልያም እክል ሊደርስበት ይችላል የሚሉት ዶክተር ማስተዋል በራሱ በግለሰቡ ሁኔታ ሊጎዳ የሚችል ሲሆን ይህም ማለት ራሱ ግለሰቡ ሥነልቦናውን የሚጎዳ ተግባር ሲፈጽም፤ሊጎዳ ይችላል ካሉ በኋላ በተለይም ለሰዎች ቅርብ የሆኑ ብሎም የሚገዙባቸውና ሊተላለፏቸው የማይፈልጉ እንደ እምነት ፤ሃይማኖት እንዲሁም ባህል የመሳሰሉ ነገሮችን የሚቃረኑ ነገሮች ሲያደርጉ ሥነ ልቦናቸው ላይ ጫና ሊፈጠር ይችላል፡፡ በሌላ በኩልም እንደ ማህበረሰብ የተቀመጡ እሴቶችን የሚጎዱ ከሆነ አእምሯቸው ላይ ጫና ሊያድር ይችላል፤ የኑሮ ውድነት አለመመቸት ብሎም ውጣ ውረድ መብዛት የትዳር አለመመቸት የሰውን ሥነ ልቦና ከሚጎዱ ነገሮች መካከል የሚጠቀሱ ስለመሆናቸውም ያብራራሉ፡፡



> "…..እንደ አለመታደል ሆኖ በአእምሮ ጤና ላይ ያለን ግንዛቤ በጣም አናሳ ነው፡፡ ሰዎች ትንሽ አካላቸው ሲታመም ምንነቱን ለማወቅ ከዚያም መፍትሔ ለመፈለግ የሚያርጉትን ጥረት ያህል ለአእምሯቸው መታወክ ትኩረት አይሰጡም፤ ስሜታቸውንም አይገልጹም ፤ ይህ መታፈን ደግሞ ለተባባሰ ችግር የሚዳርግ በመሆኑ ከሁሉም ስራችን ሊቀድም የሚገባው በአእምሮ ጤና አጠባበቅ ላይ የምናደርገው የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር ሊሆን ይገባል "

በተለይም ጦርነት የሰዎችን ሥነ ልቦና ከሚጎዱ ነገሮች መካከል ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛል የሚሉት ዶክተር ማስተዋል ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ጦርነት ማንንም የማይመርጥ ሁሉን የሚያሸብር መሆኑ ነው፡፡ በተለይም የጦርነት ቀጠና ውስጥ ያሉ ሰዎች ህጻናት እንዲሁም ሴቶች ከፍ ላለ መጨነቅ ፤መረበሽ፤ የጦርነቱ ሰለባ መሆን፤ መደፈር ፤መንገላታት መሰደድ ስለሚገጥማቸው ሥነ ልቦናቸው ይጎዳል አንዳንዴም ከፍ ላለ የአእምሮ ጤና እክል ሊዳርጋቸው ይችላል ይላሉ፡፡

የሥነ ልቦና ችግሩ ጦርነት ቀጠናው ላይ ያሉትን ብቻ በመጉዳት አይመለስም የሚሉት ዶክተር ማስተዋል እንኳን በቅርብ ርቀት ያለን ሰው ይቅርና እኛ ከሩቅ ሆነን በተለያዩ መንገዶች በምንሰማቸው ዜናዎች መደናገጥ መረበሽ መስጋት ይፈጠርብናል ፤ ይህ በራሱ አይባባስ እንጂ ከፍ ያለ የሥነ ልቦና ጫና ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

የሥነ ልቦና ችግር ትንሽ (ማይነር) ከሆነ አእምሯዊ ጉዳት እስከ ከፍ ያለ የአእምሮ ጤና መዛባት ድረስ የመድረስ አቅም አለው፤ በተለይም በአሁኑ ወቅት እንደ አገር ሁላችንም የዚህ ሰለባ ሆነናል፤ ነገር ግን በቀጥታ በቦታው ላይ ያሉ ሰዎች ደግሞ የተባባሰ የሥነ ልቦና ጫና ውስጥ እንዳሉ ይሰማኛል፡፡ በመሆኑም ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከፍ ያለ ስራ መስራት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

የሰሜኑን የአገራችን ክፍል ላይ ስራዎች ሰርቻለሁ የሚሉት ዶክተር ማስተዋል በዚህም በጣም ሰፊ የሆነ የሥነ ልቦና ጉዳት ይታያል፡፡ በመሆኑም ከገቡበት ችግር ይወጡ ዘንድ ብሎም ወደተባባሰ የአእምሮ ጤና መዛባት እንዳይገቡ ስራዎች ዛሬ ነገ ሳይባሉ ሊጀመሩ እንደሚገባም ነው የሚገልጹት፡፡

በአገራችን ያለው የሥነ ልቦና ህክምና ያን ያህል የተጠናከረና የባለሙያውም ቁጥር ብዙ ባይሆንም አሁን ባለው ሁኔታና ባሉት ባለሙያዎች ስራዎችን መስራት ግን ይቻላል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ አገር መሰል ችግሮች ሲደርሱ የሃይማኖት አባቶችን ተሰሚነት ያላቸውን ሰዎች ተሳትፎ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ነገር ግን ይላሉ ዶክተር ማስተዋል አሁን ላይ የደረስንበት የሥልጣኔ ደረጃ ሰዎች ለማህበራዊ ሚዲያው የሚሰጡት ትኩረት አኗኗራችን እንዲሁም ሌሎች ገፊ ምክንያቶች በተለይም የሃይማኖት አባቶችና ታዋቂ ሰዎችን ለመስማት ያለው ፍላጎት አናሳ ነው፤ ችግሩንም በእነሱ ብቻ እንቀርፈዋለን ማለትም ከባድ ነው፡፡ በመሆኑም የተከሰተውን ጉዳት ለመቀነስ ቅድሚያ ህብረተሰቡ ስለ አእምሮ ጤናና ሌሎች ጉዳዮች ግንዛቤን እንዲያገኝ በመገናኛ ብዙሃን ተከታታይነት ያለው ስራን መስራት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

"…..እንደ አለመታደል ሆኖ በአእምሮ ጤና ላይ ያለን ግንዛቤ በጣም አናሳ ነው፡፡ ሰዎች ትንሽ አካላቸው ሲታመም ምንነቱን ለማወቅ ከዚያም መፍትሔ ለመፈለግ የሚያርጉትን ጥረት ያህል ለአእምሯቸው መታወክ ትኩረት አይሰጡም፤ ስሜታቸውንም አይገልጹም ፤ ይህ መታፈን ደግሞ ለተባባሰ ችግር የሚዳርግ በመሆኑ ከሁሉም ስራችን ሊቀድም የሚገባው በአእምሮ ጤና አጠባበቅ ላይ የምናደርገው የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር ሊሆን ይገባል" ብለዋል፡፡

አእምሯችን ጥንቃቄ ይሻል በተለይም እንዲህ በጦርነት ውስጥ ማለፋችን ግድ ሲሆን ከማህበራዊ ሚዲያው እንዲሁም ከሌሎች እያየን ወደአእምሯችን የምንልካቸው መልዕክቶች ላይ ከፍ ያለ ትኩረት ማድረግ ይኖርብናል፤ እነዚህ ሲጠረቃቀሙም ጉዳታቸው ከፍ የሚል በመሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

አሁን ካለንበት ሁኔታ አንጻር በጦርነቱ አካባቢዎችና በሌሎችም ቦታዎች ላይ በቡድን፣ በተናጥል፣ እንዲሁም በማህበረሰብ ሊሆን ይችላል የሥነ ልቦናና የማህበራዊ ደህንነት የሚባለውን ህክምና መስጠት ያስፈልጋል፡፡

አሁን እንደ አገር ያሉንን የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች ከሃይማኖት አባቶች ጋር በማቀናጀት ለስራው ማዘጋጀት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር ነው፤ ሌላው የህብረተሰቡ ውይይት ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱ ደግሞ አእምሮን የምታክመው መጀመሪያ በውይይት ውስጡ ያለውን ነገር እንዲያወጣ በማድረግ ነው፤ ቂም በቀል፣ ጥላቻ፣ ዘረኝነት፣ ጎጠኝነቱ ሁሉ አእምሮን የሚያውኩ በሽታዎች በመሆናቸው ህብረተሰቡን እያቀራረቡና እያወያዩ ለአእምሮ ጤና ችግር ከሚፈጥረው እሳቤ ማስወጣት ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ህብረተሰቡ ሳይተዋወቅ በራሱ ጎጥ ውስጥ ተደብቆ አንዱ ለአንዱ ጠላት የሚመስለውን ነገር ትኩረት ሰጥቶ መስራት፤ ማቀራረብ፣ ማወያየት፣ ያስፈልጋል፡፡ የመገናኛ ብዙሃኑም ይህንኑ ላይ ትኩረት አድርገው መስራት እንደሚያስፈልጋቸው አብራርተዋል፡፡

ጦርነት በርካታ አስከፊ ጎኖች ያሉት ነው፡፡ በተለይም ሰዎችን በዚህ መሰሉ የአእምሮ መዛባት ውስጥ በማስገባት በኩል ወደር የለውም ፤ በመሆኑም አሁን ለይ እንደ አገርና ህዝብ ትኩረታችን ሊሆን የሚገባው በጦርነቱ ወቅት ሥነ ልቦናዊ ጫና የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን ከገቡበት ችግር እንዲወጡ በማገዝ ላይ ነው፡፡

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ዕርቀ ሰላም ደም ያድርቅ

### ክፍል ሁለት

"ሰላምን ግዛት እንጂ አትሸጣት!" ይህ አገላለጽ በብዙ ሀገራት ቋንቋ ውስጥ የተለመደ ብሂል ነው:: ዓለማችን በሰላም ውላ እንዳታድር ብዙ የሚያባንኗትን ፈተናዎች እንደተጋፈጠች ዘመኗን በመፍጀት ላይ ትገኛለች:: በብብቷ አቅፋ የያዘቻቸው ልጆቿም የፈተናዋ ተጋሪ መሆናቸው ግድ ስለሆነ ውጤቱን እየተጎነጩ ያለው ከአንድ የጋራ ጽዋ ነው:: ብዙዎች ሰላምን የግል ሀብትና ዕሴት ከማድረግ ይልቅ በተለያዩ ምክንያቶች በደራ የጥፋትና የክፋት ገበያ ላይ ለሽያጭ እያቀረቡ ሲያስማሙ እየተስተዋለ ነው:: የአብዛኞቹ ሀገራት ታሪክና የአምባገነኖች የየዕለቱ ዜና መዋዕል ይህንኑ እውነታ እያሳየን ስለሆነ በዝርዝር ዘልቆ መተንተኑ እጅግም ላያስፈልግ ይችላል::

"ፀረ ሰላምነት የሚጀምረው ከአንድ ግለሰብ ነው" የሚለው ዘወትራዊ አገላለጽ በሁሉም ዘንድ በአሜንታ ተቀባይነት ይኖረዋል ተብሎ ባይገመትም እውነትነት እንዳለው ግን መካድ አይቻልም:: ለሰላም ተጻራሪነት የግለሰብ ድርሻ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ከሆነ ዘንዳ የሰላም ሐዋርያ ለመሆንም የግለሰቦች ሚና ቀላል የሚባል አይደለም:: የአንድ ሰው ሰላማዊነት የሚጀምረው ከራስ ጋር የሚደረግን ጠብና እልህ በራስ ሸምግልና ማረቅ ሲቻል ነው:: ከራሱ ጋር የታረቀ ግለሰብ ደግሞ በቅርቡ ካለው ሰው ጋር ለመታረቅ አይከብደውም::

እርቅ ከራስና ከሌሎች ጋር ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮ ጋርም መታረቅን ግድ ይሏል:: ከራስ ጋር፣ ከሌሎችና ከተፈጥሮ ጋር ለመታረቅ ልቡ ገር የሆነ ሰው ከፈጣሪ ሃሳብ ጋር ለመስማማት አይከብደውም:: ስለዚህም ነው ቅዱስ መጽሐፍ "ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና" በማለት ማረጋገጫውን የሰጠን::

ግለሰብ የሰላም ሐዋርያ ሲሆን በዙሪያው ያሉት የቅርቦቹ ወይንም የእኔ የሚለው ማሕበራዊ ክበብ/ቡድን ፈለጉን መከተላቸው አይቀርም:: አንድ ቡድን ሰላማዊ ሆነ ማለት ማሕበረሰቡ ሰላማዊ ሆነ ማለት ነው:: ማሕበረሰብ የሰላም መገለጫ ከሆነ ደግሞ የሕብረተሰብ የሰላም አድማስ እየሰፋ ይሄዳል:: እንጂማ ሰላም የሚጀምረው ከላይ ወደ ታች ወይንም ከስብስብ ወደ ግለሰብ እንዳልሆነ በብዙ ማሳያዎች ማመላከቱ አይገድም::

በጠራራ ፀሐይ ፋኖስ አብርቶ "የሰው ያለህ!" እያለ በገበያ መካከል የተንከራተተው ዐይነ ሥውሩ አቴናዊው ፈላስፋ ዲዮጋን በድርጊቱ ለማስተላለፍ የፈለገው ቁምነገር "አንድ የሰላም መሪ" ተገኘ ማለት ሕብረተሰብን መፈወስም ሆነ መታደግ ቀላል ነው የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ፈልጎ ይመስላል:: ደግሞም እውነት ነው::

ጆን ጋርድነር የተባሉ እውቅ አሜሪካዊ ደራሲ በውጤታማ የአመራር ዘይቤ ዙሪያ በጻፉት አንድ መጽሐፍ ውስጥ ከላይ የተጠቀሰውን የአንድ ግለሰብ ተጽእኖ ፈጣሪነት የገለጹት እንደሚከተለው ነበር:: "ዛሬ የምናውቃት ታላቋ አሜሪካ ከ200 ዓመታት በፊት በሀገር ደረጃ ስትታወቅ የሕዝቧ ብዛት ሦስት ሚሊዮን ብቻ ነበር:: ከእነዚያ ሦስት ሚሊዮን ሕዝቦቿ መካከል ስድስት ታላላቅ መሪዎች ነበሯት:: እነርሱም ዋሽንግተን፣ አደምስ፣ ጄፈርሰን፣ ፍራንክሊን፣ ማድሰንና ሃሚልተን ነበሩ:: "

"ዛሬ የሕዝቧ ቁጥር ከ240 ሚሊዮን ልቆ ‹ታላቅ ነኝ ብላ ራሷን ስትሸጥ በምትውለው አሜሪካ› ሰማኒያ እጥፍ ዝነኛ የሰላም ደቀመዛሙርት መሪዎች ሊኖሯት ሲገባ ያለመታደል ሆኖ የጥንቶቹን ያህል ስድስት ያህል ተጠቃሽ የሰላም ሐዋርያት መሪዎችን ለማግኘት አልታደልንም:: " በማለት ሀገራቸውን ሞግተዋል:: ደራሲ ጆን ጋርድነር በቁጭት ለማስተላለፍ የሞከሩት መልዕክት የአሜሪካውያን መሻት ብቻ ሳይሆን የብዙ ሀገራትና ሕዝቦችን የጋራ ጉጉት ጭምር ነው::

> በተለይም በጃፓን ከተሞች ላይ በዘነበው የአቶሚክ ቦንብ ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ በሚወለዱ ሕጻናት ላይ ተጽእኖው ጎልቶ እንደሚታይ ተደጋግሞ ይገለጻል

አባባሉን ከራሳችን ሀገር ወቅታዊ ዐውድ ጋር አዛምደን እንየው:: በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል የተለኮሰው የጦርነት እሳት ምን ያህል የንጹሐንን ሕይወት እንዳስገበረ፣ ምን ያህል ሀብት እንዳወደመብንና በማሕበራዊ ተራክቧችን የፈጠራቸው ሳንካዎች ገና በሚገባ ተጠንተው ስላላለቁ ከድምዳሜ ላይ ለመድረስ አልተቻለም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ጠለቅ ብሎ ቢጠና የጥፋት ሃሳቡ ጥንስስ በመጀመሪያ የተብላላው በአንድ ግለሰብ አእምሮ እንጂ የቡድን ጭንቅላት የፈጠረው እንዳልሆነ ለማመን አይከብድም::

የጀግንነት ዋና መለያው "ሰላም ወዳድነት" ነው:: ለሰላም አሜን ብሎ የሚገዛ ጀግና ሁሌም ጦርነትን እንደፈራ ነው:: የፍርሃቱ መንስኤ በጦርነቱ አሸንፋለሁ ብሎ በመስጋት ሳይሆን በአረር ፉጨት መካከል የሚፈጸመው ጥፋትና ውድመት ሰብዓዊነቱን እየፈተነ ስለሚሞግተው ነው:: ሰላም ወዳድ ጀግና የማንም ዜጋ ደም እንዲፈስ ያለመፈለጉ ብቻ ሳይሆን የሰላም ዘብ ጭምር ነው:: አንድ ሰው ሰላም ወዳድ ስለመሆኑ በበርካታ ማሳያዎች ሊገለጽ ይችላል::

ከብዙ መገለጫዎች መካከል ዋነኛው ከራስ ሁኔታ ባሻገር ስለ ሰላም ሲባል ዝቅ ማለትን መድፈር በቀዳሚነት ሊጠቀስ ይችላል:: "በእንዲህና በእንደዚያ መስፈርቶች ሲመዘን እኔ የተሻልኩ ነኝ" ከማለት ይልቅ ራስን ዝቅ አድርጎ "ሰላምን" ከፍ በማድረግ የሰላም ሐዋርያ መሆን ከሁሉም ልቆ የሚውለበለብ የምስክርነት ሰንደቅ ነው:: የሚከተለው የጸሐፊው አንድ የግል ገጠመኝ ከላይ የተዘረዘሩትን እውነታዎች ይበልጥ ሊያጎላ ይችላል::

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ የአሜሪካዋን 50ኛ ግዛት (ስቴት) የሆነችውን ሐዋይን ለመጎብኘት እ.ኤ.አ. በታህሳስ 1996 ዓ.ም ዕድል ገጥሞት ነበር:: ይህቺ ክፍለ ግዛት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ለመስማትም ሆነ ለመተረክ እጅግ የሚዘገንን ጭፍጨፋና እልቂት ተፈጽሞባት እንደ ነበር አይዘነጋም:: ያንን እጅግ አሰቃቂ ታሪክ ለተከታታዮቹ ትውልዶች ትምህርት እንዲሆን በማሰብ ፊልሞቻቸው፣ የጥበብ ሥራዎቻቸውና ሙዚዬሞቻቸው ሳይቀሩ በሚያስደንቅ አደረጃጀት ታሪኩን በመተረክ ላይ ናቸው::

ያንን የከፋ ጥቁር የታሪክ ክስተት እንደሚከተለው እናስታውስ:: የሁለተኛው ዓለም ጦርነት (እ.ኤ.አ ከ1939 - 1945) እንደ ሰደድ እሳት ዓለማችንን እያንገበገበ ባለበት አንድ ዕለት (እሁድ ዲሴምበር 1941) የሐዋይ ሕዝብ እንደተለመደው ወደ ጉዳዩና ወደየቤተ እምነቶቹ ሊሰማራ ዝግጅት ላይ በነበረበት ሰዓት ድንገት ሳይታሰብ ብዛታቸው 353 የሆኑ የጃፓን የጦር አውሮፕላኖች አከታትለው እየበረሩ በመሄድ ያቺን የደሴቶች ስብስብ ክፍለ ግዛት በአውዳሚ ቦንብ እምሽክ አድርገው አነደዷት:: ሰውም እንስሳትም ሆነ የባሕር ኃይል ወታደራዊ ምድቦችና መኖሪያ ቤቶች በአንድ ቅጽበት ወደ አመድነት እንደተለወጡ ታሪኩ በዝርዝር ተጽፏል::

በሐዋይ ክፍለ ግዛት ውስጥ ሞት ዱታ ነኝ ብሎ ነገሠ:: አካላቸው ጎድሎና እንዳልነበሩ የሆኑ ሰለባዎች በጣር ድምጽ እዬዬ እያሉ ቢቃትቱም የሚያደምጣቸውና የሚረዳቸው አለሁ ባይ ሊደርስላቸው ስላልቻለ የስቃያቸው ጩኸትና ሰቆቃ ዋጋ አልነበረውም::

በአጭሩ ሐዋይ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ቁርስ ሆና በግፈኞች መንጋጋ ታኘከች ማለቱ ይቀላል:: "የዕንቁ ወደብ" (Pearl Harbor) በመባል የሚታወቀው የባሕር ኃይል መደብ ከእነ ሠራዊቱ፣ የሠራዊቱ ቤተሰቦችና በመቶዎች የሚቆጠሩ የጦር መርከቦችና አውሮፕላኖች እንዳለ የዶግ አመድ ሆኑ:: በግፍ የተጨፈጨፉት የባህር ኃይሉ አባላትና የሲቪሎች አጠቃላይ ቁጥር 2,335 ሲሆን የቆሰሉት ደግሞ 1,143 ነበሩ::

ይህ ጥቃት ያንገበገባቸው አሜሪካኖቹ ለበቀል የወሰኑት ጊዜ ሲደርስ ከታላላቆቹ የጃፓን ከተሞች ሁለቱን ሄሮሽማንና ናጋሳኪን በዚያው ዓመት ኦገስት 6 እና 9 በሁለት የአቶሚክ ቦንቦች አጋዩአቸው:: በበቀል ድርጊቱ ያለቁት ጃፓናውያን ሲቪሎችና ወታደሮች ቁጥር በሂሮሽማ 140,000 በናጋሳኪ ደግሞ 74,000 ተገምቷል:: ከተሞቹ ወደ ፍርስራሽነት መለወጣቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በመቶ ሺህዎች የሚገመቱት ዜጎችም ቁስለኞችና አካለ ጎዶሎዎች ሆነዋል::

የእነዚህ ሁለት ሀገራት ጠላትነት ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም የቂሙና የጥላቻው ቁርሾ ዛሬም ድረስ ተፈውሶ አብቅቶለታል ለማለት ያዳግታል:: በተለይም በጃፓን ከተሞች ላይ በዘነበው የአቶሚክ ቦንብ ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ በሚወለዱ ሕጻናት ላይ ተጽእኖው ጎልቶ እንደሚታይ ተደጋግሞ ይገለጻል::

ይህንን የታሪክ ዳራ መነሻ በማድረግ እነሆ ይህ ጸሐፊ የግል ገጠመኙን እንደሚከተለው ለአንባቢያን ያጋራል:: ጸሐፊው እ.ኤ.አ በ1996 ሐዋይ ክፍለ ግዛት በተገኘበት ወራት ክፍለ ግዛቷ የቦንቡ መዓት የዘነበባትንና የአስከፊውን ዕልቂት 55ኛ ዓመት በመዘከር ላይ ተጠምዳ ነበር:: ጸሐፊው በዚያ ምድር የተገኘው ከ23 ሀገራት ከተውጣጡ ባለሙያዎች ጋር በአመራር ጥበብ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ለመውሰድ ነበር:: ከሥልጠናው ጎን ለጎንም የተዘጋጀው የጉብኝትና የባህል ልውውጥ እጅግ የተዋጣለት ነበር::

ከአሰልጣኞቻችን መካከል አንዱ ዝነኛና ታዋቂ የነበሩት ፕሮፌሰር ጃፓናዊው አሬጋ ነበሩ:: የፕሮግራሙ መክፈቻ ሊጀመር የታሰበው በሐዋይ የባህል ቡድኖች የመድረክ ላይ ትርዒት ስለነበር የጥበብ ሥራቸውን ሊያቀርቡ የተዘጋጁት ባለሙያዎች በባሕላዊ ልብሳቸውና ጌጣጌጦቻቸው እንደተዋቡ በመድረኩ ላይ ወግ ባለው ሥርዓት ተዘጋጅተው ተቀምጠው ነበር:: ከኦፊሴላዊ ትውውቅ በኋላ የባሕል ትርዒት አቅራቢዎቹ መሪ ከወንበራቸው ከፍ ብለው የሚከተለውን ንግግር ማድረግ ጀመሩ::

"የተከበራችሁ እንግዶች! እንኳን በሰላም ወደ ውቢቷ የሐዋይ ግዛት በሰላም መጣችሁ:: እኔ ስሜ እከሌ ይባላል:: የትርዒት አቅራቢዎቹን ወክዬ እንኳን ወደ ግዛታችን በሰላም መጣችሁ የምለው "አሎሃ! በማለት ነው:: ጥቂት ስለ ራሴ ላስተዋውቃችሁ:: እኔ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የአሜሪካ የአየር ኃይል አባል ሆኜ አገልግያለሁ:: አባል በሆንኩበት የጦር ክፍል ላይ አሰቃቂውን የጃፓኖች ቅጣት ከተቀበሉት አንዱ ነኝ:: እንደምታዩኝ በዘነበብን ቦንብ ምክንያት ከፊል ሰውነቴ ሽባ ሆኖ በሥጋዬ ውስጥ የማይድን ካንሰር ተሸክሜያለሁ:: ሐኪሞች በአጭር ጊዜ እንደምሞት ቢያረጋግጡልኝም በእግዚአብሔር ፍቅርና ቸርነት ዛሬን ደርሻለሁ::

የሞቴ ቀን ሳይደርስ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ከመጡ እናንተን መሰል ዜጎች ጋር በመተዋወቃችን በግሌ ኩራት ይሰማኛል:: እነዚህ የምታዩአቸው ጎልማሶችና ወጣቶችም የእኔን ስሜት እንደሚጋሩ አምናለሁ:: ላስታዋውቃችሁና ትርዒታችንን እንጀምር" ብለው ፊታቸውን ወደ ትርዒት አቅራቢዎቹ ዞር ከማድረጋቸው እኛ ጃፓናዊ ፕሮፌሰር ከተቀመጡበት ወንበር እመር ብለው በመነሳት መድረኩ ላይ ወጥተው በአዛውንቱ እግር ላይ ተደፉ::

እግራቸው ላይ ተጠምጥመውም "ስላፈሰስነው ደም ጃፓንን ማሩ! ንጹሐንን በመጨፍጨፋችን በድለናችኋልና ማሩን! ለፈጸምንባችሁ የግፍ ዓይነት ሁሉ ጃፓንን ማሩ!" እያሉ ለደቂቆች ያህል እየተንሰቀሰቁ እግራቸውን በእምባቸው አበሱ:: እንደምንም እንዲነሱ ከተደረገ በኋላ ከመድረኩ ወርደው ወደ እያንዳንዱ የፕሮግራሙ ተሳታፊ እግር ላይ እየተደፉ ናይጄውያን፣ ኢትዮጵውያን፣ ብራዚላውያን፣ አውስትራሊያውያን ፣ጃፓንን ማሩ! ...እናንተን የበደልነው በኢኮኖሚያችን በመታበይ ነው:: " ዝርዝር ታሪኩ ብዙ ነው:: በአጭሩ አዳራሹ በእንባ ታጠበ ማለቱ ይቀላል::

ከዚህ ገጠመኝ አንባቢው ምን ትምህርት ያገኛል? መልሱ ቀላል ነው:: ከአንድም ሰው ሆነ ከቡድን የሚደመጥ የሰላምና የይቅርታ ቃል በዳይንም ሆነ ተበዳይን በእኩልነት ይፈውሳል:: ደም የሚደርቀው ልብንና መንፈስን ለሰላምና ለይቅርታ በማስገዛት ነው:: እርግጥ ነው በዳይ ተበዳይን መካስ የነበረና ያለ ስለመሆኑ ባሕልም ሆነ ሕግ ግድ ይለናል:: ከካሳውና ከደም ዋጋው በፊት መቅደም የሚኖርበት ግን ይቅርታ ማድረግ ነው::

በኢትዮጵያ ምድርም እየተፈጸመ ያለው ይኸው ነው:: በክፍል አንድ ጽሑፌ በደልን ይቅር ለማለት እንደምን እንደሚከብድ ለማሳየት ሞክሬያለሁ:: መጠቃት ውስጥን እንደ ሻህላ እንደሚያመነዥግ የደረሰበት ሁሉ ያውቀዋል:: የፈሰሰን ደም "በጥቁር ደም" ለመበቀል መሞከር ትርፉ በማይወጡት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ እንደመኖር ይቆጠራል:: በኢትዮጵያ ምድር በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የፈሰሰው ደምና የወደመው ንብረትና ሀብት፣ የደረሰው የሥነ ልቦና ቀውስና መከራ ምናልባትም ሸክሙ በቀላሉ ሊራገፍ እንደማይችል ይገመት ይሆናል::

እውነት ነው! የመንፈስና የስሜት ስብራት በፋሻ ታስሮም ሆነ በጄሶ ታጅሎ እንደሚድነው የአጥንት ስብራት ቀላል ላይሆን ይችላል:: ከልብ ይቅር መባባል ከሰፈነና አሸናፊውና ተሸናፊው እጃቸውን ለሰላም ከዘረጉና ዝቅ ብለው ከተቀባበሉ "ዕርቅ ደም ያደርቃል"፣ ይቅርታም የውስጥ ቁስልን ይፈውሳል:: ከይቅርታ በኋላ የሚፈጸመው ተጨማሪ ሂደት በራሱ የአካሄድ ወንዝ እየፈሰሰ ፈውሱ ፈጥኖ እንዲለመልም ያግዛል::

**ሰላም ይሁን::**

# ተናጋሪው ዶሴ

# አሰቃቂ ወንጀል በቤት ሰራተኛዋ ላይ

**አስመረት ብስራት**



አሁን አሁን የወንጀል አይነቶች እየበረከቱና እየረቀቁ መሆናቸውን ስንሰማ ወደየት እየሄድን ነው ብለን ራሳችንን እንድንጠይቅ ያደርገናል። የወንጀልና ወንጀለኞች መብዛት ለምን ይሆን ብለን እንድናስብ ያደርገናል፤ የፍትህ ውሳኔዎች ክብደትና ቅለትንም እንድንመዝን እንገደዳለን። በከተሞች አካባቢ የቤት ሰራተኞች በአሰሪዎቻቸው ላይ፤ በሚንከባከቡዋቸው ሕጻናት ላይ አሰቃቂ ወንጀሎችን ፈጸሙ የሚል መጥፎ ዜና መስማትም ተደጋግሞ የሚያጋጥም ክስተት ሆኗል። ከዚህ በተቃራኒም የቤት ሰራተኞች በአሰሪዎቻቸው አሰቃቂ ወንጀል ተፈጸመባቸው፣ ተደፈሩ፣ ተገደሉ፣... ሌላም ሌላም ወንጀል ተፈጸመባቸው የሚሉ የወንጀል ዜናዎች በስፋት ይሰማሉ። በህብረተሰቡም በኩል አስተማሪ ቅጣት ባለመኖሩ ነው የሚሉ ቅሬታዎችና አስተያየቶችም ይደመጣሉ። በአንዳንዶች በኩል ደግሞ ጉዳዮች ወደ መገናኛ ብዙሃን በማህበራዊ ድረ ገጾች አማካይነት በስፋት ስለሚራገቡ እንጂ በመብዛቱ ምክንያት አይደለም የሚሉ ክርክሮችም ይደመጣሉ። የሥነልቡናና የሕግ ባለሙያዎችም እንደሙያቸው ምክንያት ያሉትን ሲገልጹ ይሰማሉ። ያም ሆነ ይህ አንድም የሰው ልጅ ሕይወት መጥፋት የለበትም፤ የሰው ልጆችን ሕይወት የሚያጠፉ በሰዎች ላይ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት የሚፈጽሙ፤ አካል የሚያጎድሉ ሁሉ ወንጀለኞች በመሆናቸው አስተማሪ ቅጣት ሊጣልባቸው ይገባል የሚለው በሁሉም ዘንድ ገዢ ሃሳብ ነው።

በቅርቡ የሰማነው የወንጀል አይነት ደግሞ ትናንት በሩቁ ስንሰማው የነበረው የተመሳሳይ ጾታ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ይሄ የኢትዮጵያን ሕግ፣ ባህልና ሃይማኖትን የሚጻረር ጉዳይ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት በ“ሴቭ ዘ ቺልድረን ካናዳ” እና በ“ብራይት ፎር ቺልድረንስ ቮለንተር አሶሴሽን” ትብብር የተካሄደ ጥናት እንዳመለከተው፤ በከተማችን አዲስ አበባ ከሚፈፀሙ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች መካከል 22 በመቶ የሚደርሱት የተፈፀሙት በወንዶች ላይ ነው፡፡ ሴቶቹም ላይ ቢሆን ቁጥሩ ከፍ ባይልም ይህን መሰል ጥቃቶች መኖራቸው ተመላክቷል። ዛሬ ‹‹በተናጋሪው ዶሴ ›› አምዳችን በዚህ ዙሪያ ላስነብባችሁ የወደዱኩት ጉዳይ በቤት አሰሪዋ አስገድዶ መደፈር፣ ግፍና በደል ስለተፈጸመባት ወጣት የቤት ሰራተኛ እና ፍትህ ስለሰጠው ውሳኔ ነው።

### ያላሰበችው የገጠማት ወጣት

ወጣት ናት ገና በአፍላዎቹ የእድሜ ክልል የምትገኝ። በዛ ላይ ቀይ ቆንጆ ደንቦል ያለች ፍልቅልቅ ወጣት ናት - እቴነሽ ባህሩ። እቴነሽ እንደ አብዛኞቹ የትውልድ ቀዬቸውን ለቀው እንደሚሰደዱ ወጣቶች አዲስ አበባ ሄዶ መስራትን ህልሟ አድርጋ ነበር ያደገችው። በልጅቷ እንደ አካባቢዋ ታዳጊዎች ሁሉ በእረኝነት ነው። ከብቶች በመጠበቅ ውሃ በመቅዳት ቤተሰቦቿን ታገለግላለች። ሆኖም እድሜዋ ከልጅነት ወደ ወጣትነት ሲሸጋገር የልጅነት ህልሟ ወደሆነችው የአዲስ አበባ ከተማ በአስራ አምስት ዓመቷ ትመጣለች።

ታዳጊዋ ወጣት አዲስ አበባ አክስቷ ቤት አርፋ የከተማዋን አየር ከተለማመደች በኋላ በአቅሟ ልትሰራው የምትችለው የቤት ሰራተኛነት ስራ ይፈለግላታል። በዚሁ መሰረት አቅሟን ያገናዘበ መጀመሪያ በሞግዚትነት ትቀጠራለች። እዛም የተወሰነ ጊዜ ከቆየች በኋላ ሙሉ ሰራተኝነት የተሻለ ገንዘብ ያስገኝልኛል በማለት የቤት ሰራተኛ ሆና ብዙ ቤተሰብ ያለበት ቤት ትገባለች። ወጣቷ ከልጅነቷ ጋር ተደምሮ በአናት በአናቱ የሚደራረበውን ስራ መቋቋም ያቅታታል።

ስድስት የቤተሰብ አባላት ያሉበትን ቤተሰብ ቀጥ አድርጋ ለማስተዳደር በአፍላ ጉልበቷ አልሆንላት ያላት ልጅ ከድካምም አልፎ ለህመም ትዳረጋለች። ስራውን እርግፍ አድርጋ በመተው ከአክስቷ ጋር የተወሰነ ጊዜ ከተቀመጠች በኋላ ታገግማለች። ወደቀድሞ አቋሟ መመለሷን የተመለከተችው አክስቷ ቀለል ያለ ስራ መስራት እንድትችል በሰው በሰው ታጠያይቅላት ጀመር። በኋላም አንድ ቤት ተገኘ “አንዲት ብቸኛ ሴትን መንከባከብ ብቻ ነው፤ ስራው አያደክምም...” ይሏትና ሰብለወንጌል እያሱ በተባለች ግለሰብ ቤት ትቀጠራለች።

እውነትም እንደተባለው የከበደ ስራ አልነበረም። ለእሷና ለቀጣሪዋ የሚሆን ምግብ ማዘጋጀት የሁለቱን ፅዳት መጠበቅና እጅግ በጣም አነስተኛ የሚባሉ ስራዎችን ከመስራት ያለፈ የሚያደክማት ስራ አትሰራም ነበር። ድካሟ እየለቀቃት ሰውነቷ እየተመለሰ ሲሄድ ግን የቀጣሪዋ አስተያየት እየተቀየረባት ሄደ። ግራ የሚያጋባ ስሜት እየተሰማት የሆዷን በሆዷ ይዛ ዝም አለች። ሁኔታውን ግን በልቧ ከትታ እሷም የሚሆነውን ነገር ማድመጥና ማየት የየእለት ስራዋ አደረገች።

“ሴትን በዚህ መልክ የሚያዩትና የሚመኙት ወንዶች አይደሉም እንዴ? ለምን ግን እንደዚህ ታየኛለች፣ ትነካኛለች ...?” የሚል ጥያቄ ወጣት እቴነሽ ልብ ውስጥ ይመላለሳል። ብዙን ጊዜ ከቤት እንድትወጣና ከሌሎች ሰዎች ጋር እንድታወራ ስለማይፈቀድላት ለማንም መማከር አልቻለችም ነበር። ከጎረቤት ጋር ቆማ ብታያት በጩኸት ስለምታስበረግጋት ተደብቃ የሚናፍቃትን ደጅ ከማየት ያለፈ ከቤት ወደ ውጭ ውልፍት አትልም ነበር።

“ከዚህ ሁሉ ለምን እረፍት ጠይቄ ለአክስቴ የሆነውን አልነግራትም...” ትልና እረፍት ትጠይቃለች። በመልሱ ግን መሄድ እንደማትችል የተነገራት ወጣት ግራ በመጋባት ውስጥ ሆና ልቧ በስጋት ተወጥሮ ምን ማድረግ እንዳለባት እያሰላሰለች በነበረበት ወቅት ነው የላሰበችው ድርጊት የተፈፀመባት።

### ዱብዳው

በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 አልታድ ሚካኤል ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ነው። የ30 ዓመት እድሜ ያላት የእቴነሽ ቀጣሪ ሰብለ ወንጌል እያሱ ተከራይታ ከምትኖርበት ቤት ውስጥ ነው ይህ ድርጊት የፈፀመችው። በቤት ሰራተኝነት ያመጣቻትን ወጣት እቴነሽን ባላሰበችውና ባልጠበቀችው ሁኔታ በግንቦት ወር 2012 ዓ.ም አንድ ምሽት ላይ ጥቃት ታደርስባታለች።

ነገሩ እንዲህ ነው በእለቱ ትንሽ መጠጥ ቀማምሳ የመጣችው አሰሪ ይዛ የመጣችውን አረቄ እቴነሽ በግድ እንድትጠጣ ታደርጋታለች። ከዛም በኋላ በቢላዋ በማስፈራራት ልብሷን ሙሉ በሙሉ በማስወለቅ እና ኢሰብአዊ ድርጊት ትፈጽምባታለች ፤ ቀጥላም አፏን በነጠላ በማፈን የሴቶች ፀጉር መስሪያ ፓይስትራ ሶኬቱን በመሰካት በግል ተበዳይ ብልት ውስጥ በኃይል በመክተት የግል ተበዳይ ድንግልና እንዲገረሰስ እና ደም እንዲፈሳት ካደረገቻትም በኋላ ፀያፍ ድርጊት ፈፅምባታለች፡፡

ባለሰበችው ፍጥነት ያላሰበችው ዱብዳ የወረደባት ወጣት ራሷን ለማስጣል የተለያዩ ሙከራዎች ብታደርግም አቅም ታጣለች። ቀጣሪዋ የፈፀመችው ፀያፍ ድርጊት አልበቃ ብሏት በተደጋጋሚ ጊዜ በቢራ ጠርሙስ እና በታኮ ጫማ ግንባሯን፣ ጀሮዋን፣ አፍንጫዋን እንዲሁም እግር እና እጇን የመታቻት ሲሆን በዚህም ጆሮዋ እንዲጎዳ ፤ የላይኛው የፊት ጥርሷ እንዲሰበር ከማድረጓም በላይ የፈላ ውሃ የተጎጂዋ ደረት ላይ በመድፋት አካሏ እንዲላጥ አድርጋለች፡ ፡ በተጨማሪም በቢላዋ ጀርባዋን በመውጋት ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስባት በማድረጓ የግል ተበዳይ በዚህ ተደጋጋሚ ጥቃት ምክንያት ሰውነቷ ላይ ጠባሳዎች ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡

ሴትዮዋ ከቤት በምትወጣበት ጊዜ የግል ተበዳይ ላይ ቆልፋባት የምትወጣ በመሆኑ ድርጊቱ ከተፈጸሙበት ከመጋቢት 27/2012 ዓ.ም እስከ ግንቦት 19/2013 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ ተጎጂዋ በቤት ውስጥ ምግብ እና የፀሃይ ብርሃን ተከልክላ ለአንድ ዓመት ከሁለት ወር በማቆየት በስቃይ ላይ ስቃይ ስትደራርብባት ቆይታለች፡፡

### የማምለጥ ሙከራ

የሰቆቃው ብዛት “ከዚህስ ሞት ይሻላል” እንድትል ያደረጋትን ይህን ጥቃት ለማምለጥ አቅሟን ማጠናከር ጀመረች። በኋላ መስኮት ጋር ጠጋ ብላ ሰው ሲያልፍ የማንኳኳት ሙከራ ብታደርግም ማንም ሰው ሊያያት አልቻለም ነበር። ቀስ ብላ ድምጿን ለማሰማት ብትሞክርም ያም ሊሰራላት አልቻለም ነበር። በመጨረሻም የግል ተበዳይ በወረቀት ፅፉ በመስኮት ቀዳዳ ትጥላለች። የጣለችውን ወረቀት አንድ ግለሰብ በማግኘቱ የፖሊስ አባላት ይሰጣል። ያኔ ፖሊሶች ለምርመራ ቤቷ በተገኙ ጊዜ ተበዳይን አልጋ ስር ደብቃት እጅ ከፍንጅ ተያዘች።

### የፖሊስ ምርመራ

የግለሰቡን ጥቆማ ተከትሎ ሰብለወንጌል እያሱ ቤት የተገኘው ፖሊስ ቤቷን እንድታሳይ ያደረገው ጥረት በሴትዮዋ እንቢታ ምክንያት ቢጓተትም፤ ፖሊስ ይዞ የመጣውን ማዘዣ በማሳየት ገብቶ ቤቱን ሲፈትሽ እጅግ በጣም የተጎዳች ወጣት በአሰቃቂ ሁኔታ አልጋ ስር ተደብቃ ይመለከቷታል። ያየውን በካሜራ በማስቀመጥ የሰውና የህክምና ማስረጃን በማሰባሰብ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የቦሌ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ዐቃቤ ሕግ ያቀርባል።

በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የቦሌ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ዐቃቤ ሕግ ከፖሊስ ጋር በጋራ በመሆን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ እና በመመርመር ክስ ሊያስመሰርት የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖሩን በማመን በ1996 ዓ.ም የወጣውን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 630/2/ሀ/ እና /ለ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በፈፀመችው ከባድ የግብረ ሰዶም እና ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ድርጊቶች ወንጀል፣ አንቀፅ 555/ሀ/ እና /ለ/ በመተላለፍ በፈፀመችው ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ እና አንቀፅ 590/ሀ/፣ /ሐ/ እና 2/ለ/በመተላለፍ በፈፀመችው ከሕግ ውጪ ይዞ ማስቀመጥ ወንጀል 3 ክሶችን መስርቶባት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በዚህም መሰረት ተከሳሽ የቀረበባትን ክስ ክዳ ተየተከራከረች ሲሆን ዐቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰው፣ የሰነድ፣ ገላጭና ኤግዝቢት ማስረጃዎች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ጉዳዩን ሲከታተል የቆየው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ወንጀል ችሎት ተከሳሽ በቀረበባት ሁሉም ክስ ስር እንድትከላከል ብይን ቢሰጥም ተከሳሽ ያቀረበቻቸው ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ ማስተባበል ሳይችሉ በመቅረታቸው በተከሰሰችባቸው ክሶች ሁሉ ስር ጥፋተኛ ነሽ ሲል የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

### ውሳኔ

የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ወንጀል ችሎት ጥቅምት 17 ቀን 2015ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከሰማ በኋላ ተከሳሽ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑዋን፣ የቀድሞ የወንጀል ሪከርድ የሌለባት መሆኑን፣ ህመምተኛ መሆኑዋን እና የበጎ ስራ ላይ ትሰማራ የነበረ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃዎችን ተቀብሎ በድምሩ አራት የቅጣት ማቅለያ ተይዞላት ተከሳሽን ያርማል፤ ሌላውን ያስጠነቅቃል በማለት ተከሳሽን በ 14 ዓመት ፅኑ እስራት እንድትቀጣ ሲል የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ተጠያቂነት እንዲኖር እንተዋቸው

**አቤል ገ/ኪዳን**

እኛ ቤት የእህቴ ልጅ አለ:: የአንደኛ ክፍል ተማሪ ነው:: በትምህርቱ ደህና የሚባል ልጅ ቢሆንም እንደ ማንኛውም ልጅ ጨዋታ ያታልለዋል:: በዚህም የተነሳ የቤት ሥራውን በተደጋጋሚ ይዘነጋል:: በቀደምም የሆነው ይሄው ነው:: እናቱ በተደጋጋሚ የቤት ሥራ ያለው እንደሆነ ስትጠይቀው መልሱ የለኝም ነበር:: እሷም በሰጣት መልስ መሠረት የቤት ሥራ ከሌለው በጊዜ እንዲተኛ ነግራው ሥራዎቿን መሥራት ቀጠለች:: ሥራዎቿን ጨራርሳ ቴሌቪዥን ልታይ ቁጭ ስትል ግን ልጅ የቤት ሥራ እንዳለው ትዝ አለው:: የቤት ሥራ አለኝ አላት:: ተናደደች፤ ተቆጣች:: አማራጭ ስላልነበራት ግን በመኝታ ሰዓት እንደገና የእሱን ደብተር መፈለግ እና የቤት ሥራ ማሠራት ያዘች:: ሰዓቱ በጣም መሽቶ ስለነበር ልጅም እንቅልፍ እየተጫጫነው ነበር:: በዚህም የተነሳ ብዙውን የቤት ሥራውን ክፍል የሠራችው እሷ ናት ማለት ይቻላል:: እንደምንም ተሰርቶ ሲያልቅ ልጅ ወደ መኝታው ሄደ:: የቤት ሥራውን የሠራው የተማረው ምን ያህል እንደገባው ለመገንዘብ ሳይሆን በቀጣይ ቀን ከሚጠብቀው የመምህሩ ዱላ ለማምለጥ ነው:: እናትም የቤት ሥራውን ያሠራችው ልጁ ምን ያህል የተማረው እንደገባው ለማየት ሳይሆን ልጁን በቀጣዩ ቀን ከሚጠብቀው ተጠያቂነት ለማዳን ነው::

ይህ ዓይነቱ ነገር በየቤቱ ያለ ጉዳይ ነው:: ልጅ ካለ እንዲህ አይነት ነገር አለ:: አንዳንዱ ቤት በጣም ከመሸ ሲሆን ሌላው ቤት ደግሞ ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት በመሄጃ ሰዓት ልጆች የቤት ሥራ እንሥራ ይላሉ:: ወላጅም የትምህርት ቤት መግቢያ ሰዓት እንዳይረፍድ የቤት ሥራውን ልጁ መልሱን እየጻፈ ወላጅ መልሱን እየተናገረ ይሠራና ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል::

**አንዳንዴ ተጠያቂነት የምንወዳቸው ሰዎችን የተወሰነ ችግር ቢያስከትልባቸውም በዘለቄታው ግን ጤናማ ያደርጋቸዋል**

እንዲህ ዓይነት ነገር አንዳንዴ የሚጋጥም ቢሆንም ሲደጋገም ግን ችግር መሆኑ አይቀርም:: የልጁን የቤት ሥራ አንዳንዴ ወላጅ ሌላ ጊዜ አስጠኚ ፤ አንዳንዴ ታላቅ ወንድም ወይም እህት ፤ ሌላ ጊዜ ጎረቤት ያለ ደህና የሚባል ሰው እየሠራለት ይቀጥላል:: ልጅም እንዝላልነትን በዚህ መልኩ እየተለማመደ ይሄዳል:: ከሁሉ በላይ ግን ልጅ ወላጅን አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ከትቶ የእሱን ፍላጎት እንዲፈጽሙ እና ግዴታውን እንዲወጡለት ማድረግን ይለማመዳል:: ይህ አደገኛ ልምምድ ያድግና ከፍ ሲል ወንጀል ፈጽሞ ወላጆቹ መጥተው እንዲያስፈቱት ፤ ገንዘብ አውድሞ እንዲከፍሉለት ፤ መኪና አጋጭቶ መጥተው ዋስ እንዲሆኑት ወዘተ መጠበቅን ይለምዳል:: ለእንዝላልነት ዋጋ እንደሚከፈል መማር ያለበት በጊዜ ገና በልጅነቱ እንደሆነ እንገነዘባለን::

ይህን ከፍ ባለ አውድ ስንመለከተው በሀገር ደረጃ መንግሥትን እና ሕዝብን የማይሆን አደገኛ ቅርቃር ውስጥ ከትተው የሚፈልጉትን የሚያስፈጽሙ ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ ያህል ነጋዴው ከመንግሥት አንዳች ነገር ይፈልጋል ፤ ነገር ግን መንግሥት ያንን እንደማይፈጽምለት ያውቃል:: ስለዚህም ለዚህ እንደ መፍትሔ የሚከተለው መንገድ ላይ ምርትን መያዝ ነው:: መንግሥት ይህን ሳቦታጅ ይለዋል:: ምርትን ይደብቃል፤ፍላጎት እያየለ ይሄዳል፤ፍላጎት እየጨመረ ሲሄድ ግን አቅርቦት ታግቶ ተይዟል፤ይሄኔ የዋጋ ውድነት ይፈጠራል፤ሕዝብ መቆጣት ይጀምራል:: የሚቆጣው ግን ነጋዴውን አይደለም ፤ የሚቆጣው እና የሚያማርረው መንግሥትን ነው:: ለዚህ ብዙ ጊዜ መንግሥት የሚወስደው አማራጭ ለነጋዴው ፍላጎት ሽብረክ ማለት አልያም ቁጣው እያየለ ቢሄድም ዝም ማለት ነው:: መንግሥት የሚመርጠው የመጀመሪያውን እንደሆነ እርግጥ ነው:: ስለዚህም መንግሥት የነጋዴውን የቤት ሥራ ሠርቶ ምርቱን ያስለቅቃል:: ነጋዴውም በጉልበት የመንግሥትን እጅ ጠምዝዞ ፍላጎቱን አስፈጸመ ማለት ነው::

እንደኔ ግምት እንዲህ የሚያደርጉት ከመሸ የቤት ሥራ እንሥራ እያሉ ወላጅን የሚያስጨንቁት ልጆች አይነት ናቸው:: የቤት ሥራው እንደተደበቀው ምርት ነው:: መምህሩ ምርትን እንደሚጠብቀው ሕዝብ ነው:: ወላጅ እንደ መንግሥት ነው:: ወላጅ ሳይወድ በግድ የመምህርን ቁጣ ለማስታገስ የልጁን የቤት ሥራ ይሠራል:: ልጅ ለእንዝላልነቱ ሳይቀጣበት ያልፋል:: ነጋዴም እንዲሁ ለፈጠረው ሳቦታጅ እና ላስከተለው ችግር ተጠያቂ ሳይሆን ይሾልካል::

ወላጅ ልጁን ይወዳል ፤ መንግሥትም የልማት አጋሩ ነውና ባለሀብትን ይወዳል:: ነገር ግን አንዳንዴ የምንወደው ላይ መጨከን ግድ ይሆናል:: ለልጅህ ዛሬ አንተ የትምህርት ቤት የቤት ሥራውን ልትሠራለት ትችላለህ:: ነገር ግን ነገ ለሚገጥመው የሕይወት የቤት ሥራ ዝግጁ እያደረግከው አይደለም:: አድጎ ሥራ ላይ ፤ ትዳር ላይ ፤ ማኅበራዊ ኑሮ ላይ የሚገጥመውን ፈተና ወላጅ አይወጣለትም:: በተመሳሳይም መንግሥት ዛሬ ተንከባክቦ ያለ ብዙ ተጠያቂነት የያዛቸው ነጋዴዎች ዛሬ ላይ የፈለጉትን ማግኘት ቢችሉም ይህ የመንግሥት የዛሬ እንክብካቤ ግን ሉላዊ እየሆነች በመጣች ዓለም ውስጥ ለሚገጥማቸው ብርቱ ተግዳሮት ምንም አያግዛቸውም:: ለማብቃት ተብሎ የሚደረግ ትዕግስት እና ቻይነት እንደ ነገ ግን ባለሀብት ሽፍታን ይፈጥራል:: ስለዚህም የተወሰነ ተጠያቂነት ሊኖርባቸው የተገባ ነው::

እንዲያው በጥቅሉ ለማለት የተፈለገው መልዕክት ምንድን ነው ፤ አንዳንዴ የምንወዳቸውን ሰዎች እንዲያድጉ ከፈለግን በተወሰነ መልኩ ኃላፊነት እንዲወስዱ እናድርግ ነው:: ልጅ የቤት ሥራ አስታውሶ ካልሠራ አስተማሪው እንዲገስጸው መተው አለብን:: ተግሳጽ አይገድለውም:: ነገ መምህሩ ሊቀጣው ይችላል በሚል የቤት ሥራውን ተቀብሎ መሥራት ግን ልጁን በቋሚነት ያጠፋዋል:: ይህ ለመማር ማስተማሩ ሥራ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ጉዳይ የሚያስፈልግ መርሕ ነው:: አንዳንዴ ተጠያቂነት የምንወዳቸው ሰዎችን የተወሰነ ችግር ቢያስከትልባቸውም በዘለቄታው ግን ጤናማ ያደርጋቸዋል:: ከሁሉም በላይ ግን በምንም ሁኔታ የምንወዳቸው ሰዎች መውደዳችንን እንደ እድል ብቻ እየተመለከቱ የእነሱን ጣጣ እንድንወጣላቸው እንዲያደርጉ አንፍቀድ:: ነጋዴ ገበያውን ሳቦታጅ ማድረግ እንደሌለበት ሁሉ ሰዎችም ፍቅርን ሳቦታጅ ማድረግ የለባቸውም ፤ እንዲያደርጉም ሊፈቀድላቸው አይገባም::

# ዓለም አቀፍ



## በስፔን አንድ ሙሉ የገጠር መንደር ለሽያጭ ገበያ ላይ ቀረበ

በስፔን ሳልቶ ዲ ካስትሮ የሚባል አንድ የገጠር መንደር ለሽያጭ ገበያ ላይ ቀርቧል። ደላሎችም ገዢ እያፈላለጉለት ነው። ሳልቶ ዴ ካስትሮ በሰሜን ምዕራብ የሚገኝ ገጠራማ ትንሽ መንደር ነው። ከፖርቹጋል ድንበር ጠጋ ብሎ ዛሞራ በሚባል አውራጃ የሚገኘው ይህ መንደር የሽያጭ ዋጋው 259ሺህ ዶላር ይጠራል።

ይህ መንደር ከማድሪድ ከተማ የሦስት ሰዓት የመኪና መንገድ ነው። መንደሩ ይህ ቀረሽ የሚባል አይደለም። በርካታ መኖሪያ ቤቶች፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ትምህርት ቤት፣ ማዘጋጃ ቤት፣ መዋኛ፣ ሆቴል ያሟላ ነው። የጎደለው አንድ ነገር ነው፤ ነዋሪ።በዚህ የገጠር መንደር ነዋሪ የለም።

ሳልቶ ዲ ካስትሮ መንደር ላለፉት 30 ዓመት ሰው ኖሮበት አያውቅም። አንድ ባለጸጋ ይህን የገጠር መንደር በፈረንጆች 2000 ገዝተውት ነበር። ለቱሪስት ምቹ አደርገዋለሁ ብለውም እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር።

ይሁንና በአውሮፓ በወቅቱ የነበረው ቀውስ ሕልማቸውን አጨለመው። ባለጸጋው ሆቴል ለመገንባትም የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠው ነበር፤ ዕቅዳቸው አልተተገበረም እንጂ። ባለጸጋው 80ዎቹ ዕድሜ ላይ ሲሆኑ የገጠር መንደሩን የሚሸጡት እሳቸው የከተማ ነዋሪ ስለሆኑና እንዳሰቡት አካባቢውን መንከባከብ ባለመቻላቸው እንደሆነ ገልጠዋል።

ይህ የገጠር መንደር ለገበያ የቀረበበት የደላላ ድረ ገጽ እስከ አሁን 50ሺህ ሰዎች እንደጎበኙት ታውቋል። 300 ሰዎች ደግሞ የመግዛት ፍላጎታቸውን ገልጸዋል። እነዚህም ከሩሲያ፣ ከፈረንሳይ ከቤልጂየም እና ዩናይትድ ኪንግደም ናቸው የመጡ ሰዎች ናቸው። አንድ ስማቸው ያልተገለጸ ባለጸጋ ቀብድ ከፍለዋል ተብሏል።

ሳልቶ ዴ ካስትሮ በ1950ዎቹ በአንድ የኤሌክትሪክ ኩባንያ አማካኝነት ለሠራተኞቹ ቤት በመገንባት የተመሠረተ ገጠር ነው። ነገር ግን ሠራተኞቹ የኤሌክትሪክ ዝርጋታ ሥራውን ሲጨርሱ ያንን ገጠር ለቀው ወጡ። ከ1980ዎቹ ወዲህ ይህ ገጠር ነዋሪ አልባ ሆኖ ቀረ። ይህ የገጠር መንደር ለገበያ ሲቀርብ ይህ የመጀመሪያው አይደለም።

ከዚህ ቀደም በ6.5 ሚሊዮን ዩሮ ለገበያ ቀርቦ የነበረ ሲሆን ገዥ አጥቶ ቀርቷል። አካባቢው የነበሩ ቁሳቁሶችም በሌሎች ተዘርፎ እንዲሁ ኦና ሆኖ ቀርቶ ነበር። አሁን ጠቅላላ የገጠር መንደሩን ለመሸጥ የቀረበው ዋጋ በማድሪድ ወይም ባርሴሎና አንድ ቆንጆ ባለ አንድ መኝታ አፓርታማ መግዛት ቢችል ነው ሲል የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።



## ኢምራን ካሃን ከግድያ ሙከራ ከተረፉ በኋላ የፖለቲካ ጉዟቸውን ጀመሩ

የፓኪስታን የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካሃን ባለፈው ሳምንት ከተደረገባቸው የግድያ ሙከራ ካገገሙ በኋላ የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸውን ዳግም ጀምረዋል።

ኢምራን ካሃን ለደጋፊዎቻቸው ወደ ዋና ከተማዋ ኢስላማባድ የሚያደርጉትን “ረጅም ጉዞ” እንዲቀጥሉ አሳስበዋል። በተንቀሳቃሽ ምስል ባስተላለፉት መልዕክት ካሀን “ለእውነተኛ ነፃነት” ትግሉን ለመቀጠል ቃል ገብተዋል።

የፓኪስታን ቴህሪክ ኢ-ኢንሳፍ ፓርቲ ተኩስ በተደረገበት ዋዚራባድ ቦታ ላይ ሰልፍ እንዲያደርጉ ደጋፊዎቻቸው እገዳዎችን እንዲያነሱ አሳስበዋል። “ራዋልፒንዲ እደርሳለሁ። ሁላችሁም እንድትመጡ እና ከእኛ ጋር እንድትዘምቱ እጋብዛችኋለሁ ምክንያቱም የነገ የሀገር እና የልጆቻችሁ እጣ ፈንታ ጉዳይ ነው” ማለታቸውን የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን የሆነው ዘ ኔሽን ዘግቧል።

ኢምራን ካሃን በሚያዝያ ወር በእንደራሴዎች ድምጽ ከስልጣን ከተነሱ በኋላ ምርጫ እንዲደረግ ለመግፋት በተካሄደ ሰልፍ ላይ ነበር በጥይት የተመቱት። በዚህ ጥቃት የአንድ ሠው ሕይወት ሲጠፋ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር በተቀናቃኞቻቸው የተደረገ “የግድያ ሙከራ” መሆኑን ተናግረዋል።

ባለፈው ሳምንት ፖሊስ ይፋ ባደረገው ሪፖርቱ መሐመድ ናቪድ የተባለ ግለሰብ የዋዚራባድን ጥቃት ፈጽሟል። ተጠርጣሪው በቁጥጥር ስር የዋለው በቦታው ላይ በካሃን ደጋፊ ከተጠለፈ በኋላ ነውም ተብሏል። ካን ቢያንስ ሁለት ተኳሾች ባለፈው ሳምንት “የታቀደውን” ጥቃት ፈጽመዋል ሲሉ የፖሊስን ሪፖርት ውድቅ አድርገዋል።

ካሃን የፓኪስታን ጠቅላይ ሚኒስትር ሼህባዝ ሻሪፍ፣ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ራና ሳኑላህ እና ሜጀር ጀነራል ፋይሰል ናሲር ግድያውን በማሴር በሃይማኖታዊ አክራሪ ላይ አላከዋል ብለዋል። ይህ እቅድ እንደተዘጋጀ እና የሃይማኖት አክራሪዎች እንደሚወቅሱበት አስቀድሜ ከወራት በፊት ተናግሬ ነበር ብለዋልም።

ይሁን እንጂ የፓኪስታን መንግሥት እና ወታደራዊ ኃይሎች ክሱን አጥብቀው አስተባብለዋል። ተኳሹ ጥቃቱን በሃይማኖታዊ መሠረት ያደረገ “በራስ ተነሳሽነት ነው” ብለዋል። ካሃን ግድያውን በማሴር የፓኪስታን ጠቅላይ ሚኒስትር ሼህባዝ ሻሪፍን ወንጅለዋል ሲል አል ዐይን ዘግቧል::

# መጋቢ አዕምሮ

# ሁሉም በቦታው

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

የሁለቱም ቡድኖች ደጋፊዎች ድማጻቸውን ከፍ አድርገው እየደገፉ ነው፡፡ ድጋፋቸውም ቡድናቸው አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ የሚያደርግ እንዲሆን ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የደጋፊዎች የእርስ በእርስ ብሽሽቅ ሌላው የጨዋታው ድምቀት ነው፡፡ ብሽሽቁ መስመር ስቶ ወደ ብጥብጥ የሚያልፍበት ሁኔታም አለ፡፡ ከጨዋታው መጀመር ጀምሮ ድጋፋቸውን ሲገልጹ የነበሩ ደጋፊዎች ጨዋታው ሲጀመር እንደ ጨዋታው ሁኔታ ድጋፋቸው ሞቅ ቀዝቀዝ እያለ ይቀጥላል፡፡

ዳኞች በእግር ኳስ ጨዋታ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ትርጉሙ ቀላል አይደለም፡፡ የዳኞች ውሳኔ በእግር ኳስ ስፖርት ውስጥ ብዙ ውይይት የሚፈጥር ጉዳይም ሆኖ እንመለከታለን፡፡ ደጋፊዎች በስሜት ውስጥ ሆነው በርቀት በሚያዩት ዳኛ ላይ ማለት የሚፈልጉትን ለማለት በብዙ ይደክማሉ፡፡ ዳኞች የሚሠሩትን ስህተት ለመቀነስ ረዳት ዳኞች የሚያደርጉላቸው እገዛ ያለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቴክኖሎጂ ድጋፍም እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ ቴክኖሎጂም በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ በዋለበት ሁኔታ በዳኞች አካባቢ ውይይትን የሚፈጥር ክስተት መፈጠሩ አልቀረም፡፡

የስፖርት ሚዲያው ዘርፍ ሌላው በሰፊው በስፖርት ኢንዱስትሪ ውስጥ በዋናነት በእግር ኳስ ውስጥ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ ያለው ነው፡፡ ስፖርቱን ከሚዲያ ነጥሎ መመልከት ፈጽሞ በማይታሰብበት ደረጃ ላይም ይገኛል፡፡ ብዙ አይነት የስፖርት ውድድሮች የሚደረጉ ቢሆንም የሰውን ትኩረት ስበው የሚያወያዩት በአብዛኛው የሚዲያ ሽፋን ያላቸው ናቸው፡፡ ትላልቅ የሊግ ውድድሮች በቅርበት ከመላው ዓለም በርካታ ተከታይ እንዲያፈሩ መቻላቸው ከሚዲያ ውጭ ፈጽሞውኑ ሊታሰብ የሚችል አይደለም፡፡ በሚዲያ አማካኝነት የስፖርት ውድድርን ካሉበት ቦታ ሆነው የሚከታተሉ ሰዎች በስታዲየም ውስጥ ተገኝተው ይከታተሉ ቢባል ምን አይነት ስታዲየም ሊበቃ እንደሚችል ማሰብ ከባድ ነው፤ ፈጽሞውኑ ሊታሰብም የሚችል አይደለም፡፡

የትጥቅ አምራቾች ሌሎች በስፖርት ውድድር ውስጥ ትርጉም ያለው አስተዋጽዖ ያላቸው ናቸው፡፡ የደጋፊዎች ማኅበር፤ የክለብ ባለቤቶች፤ የተጨዋቾች ወኪሎች ወዘተ እያልን ከ 90 ደቂቃ የኳስ ጨዋታ ጀርባ ያለውን በርካታ ውስብስብና ቅንጅታዊ ሥራዎችን ስንመለከት በአንድ ሥራ ውስጥ ያለውን የተለያዩ አካላትን ድርሻ እንመለከታለን፡፡ ተጫዋች መልምሎ ወደ ከፍተኛ ደረጃ በሚደርስበት ሂደት ውስጥ የተለያዩ አካላት የሚያደርጉት አስተዋጽዖ ወይም የሚኖራቸው ሚና በቀላሉ ተገልጾ ማለፍ የሚቻል አይደለም፡፡

ዛሬ የእግር ኳስ የስፖርት ዓለምን በምናባችን ላይ እያየን ሁሉም በቦታው እንዘልቃለን፡፡ እያንዳንዳችን ዛሬ የዋልንበት ቦታ በሕይወታችን ውስጥ የሚኖረው ትርጉም ኢምንት ቢመስለንም እያንዳንዱ ጥቂት የምንለው ነገር ተደምሮ የሚፈጥረው ትልቅ ባህር ስላለው ኃይል እንመለከታለን፡፡ በእጃችን ያለውን ትንሽ የተባለውን ነገር ዘርዝረን ጽፈን እንዴት እንደ ችግኝ አሳድገን ትልቅ ዛፍ ማድረግ እንደምንችል እናስባለን፡፡

በዚሁ ዓመት ላይ ከእዚህ ቀደም በተለያዩ የመጣጥፍ ርዕሶች ስር ያነሳናቸውን አስተማሪ ነጥቦችን ሁሉም በቦታውን ለማስረዳትም እንሞክራለን፡፡

## 1) ራስን መቀበል

በስፖርቱ ዓለም ስማቸው የገዘፉት ተጫዋቾች ለራሳቸው የሰጡትን ቦታ እናስብ፡፡ ራስን መቀበል መቻል የሚበረታታ እያንዳንዱ ሰው ሊያደርገው የሚገባ ነው፡፡ ለራስ ቦታ መስጠት ተገቢነቱ እንዲሁ አያጠያይቅም፡፡ ፈጣሪም ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን እንድንወድ ሲጋብዘን ለራሳችን ከምንሰጠው ቦታ ተነስተን መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ ለራስ ቦታ መስጠትና ለራስ የተለየ ትርጉም መስጠት ሁለቱ ይለያያሉ፡፡

ሰዎች ባደጉበት ባህል፣ በሚናገሩት ቋንቋ፣ በዕድሜያቸው፣ በጾታቸው፣ በትምህርት ዝግጅታቸው፣ በሚሠሩት ሥራ፣ ባላቸው ተሰጥዖ ወዘተ ልዩነት ሊኖራቸው ቢችልም በመሠረታዊነት ሰው በመሆናቸው ግን አንድ ናቸው፡፡ ከቆዳ ቀለማቸው ባሻገር በሰውነታቸው የሚጋሩት የጋራ ማንነት ከፍ ያለነው፡፡ በምድር ላይ ባሉ የሰው ልጆች መካከል ያለው ልዩነት ካለን አንድነት አንጻር ፈጽሞውኑ ለውድድር የሚቀርብም አይደለም፡፡

ሆኖም በታሪክ ውስጥ ለራስ በሚሰጥ የተሳሳተ ትርጉም የተነሳ ብዙ ጥፋት ሲሆን አይተናል፡፡ ለራስ የሚሰጠው የተሳሳተ ትርጉም ራስን ከሌሎች የተለየ አድርጎ ማሰብ፣ ሌሎችን ከራስ በታች አሳንሶ ማየት፣ ሌሎች ከእኛ ተለይተው በሚታዩበት ልዩነት ምክንያት ከሰውነት አውርዶ መመልከት ወዘተ ነው፡፡ ለራስ የሚሰጥ የተለየ ትርጉም ያለንበትን ትክክለኛ ነባራዊ ሁኔታ እንዳንረዳና የተሳሳተ መንገድ ውስጥ እንድንገባ ያደርገናል፡፡

አይሁድን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የተዘረጋው ፕሮጀክት መነሻና መድረሻው ለራስ የተለየ ትርጉም መስጠት ነበር፡፡ ጣሊያን ኢትዮጵያን ዳግም ለመውረርና ለከፍተኛ ጥፋት ድግስ ውስጥ እንድትገባ ያደረጋት ለራስ የተለየ ትርጉም መስጠት ነበር፡፡ የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓትን ከአሜሪካ ለማስቀረት የተደረገው ትግል ሚሊዮኖችን እንዲጨርስ ሊንከንንም በበቀል ለመግደል የተደረገው ለራስ በሚሰጠው የተለየ ትርጉም ነው፡፡ የፍሎይድ አሟሟት የቀሰቀሰው የጥቁርም ሕይወት ይጐዳል የተሰኘው እንቅስቃሴ መነሻው ለራስ ከሚሰጥ የተለየ ትርጉም የተነሳ የተፈጠረን ኃዘን ለመግለጽ ነው፡፡ በሀገር እንዲሁም በዓለምአቀፍ ደረጃ ካሉት ማሳያዎች ወደ አካባቢያችን እንዲሁም ቤተሰባችን ጉዳዩን ይዘን ብንመጣ የበረከቱ ማሳያዎችን ልናነሳ እንችላለን፡፡

ራስን በመቀበልና ለራስ የተለየ ትርጉም መካከል ያለውን ልዩነት በመረዳት ጤናማ ሕይወትን እርሱም ከሌሎች ጋር በሰላም የመኖርን ጥበብ ማግኘትን ይገባል፡፡ ብቻችንን ልንኖረው የምንችለው ሕይወት ምድር ላይ እንደሌለ በመረዳት በዙሪያችን ላሉት ሰዎች ከየትኛውም ልዩነት ባሻገር ትርጉም በመስጠት መኖርን መልመድ አለብን፡፡

ሁላችንንም ያለብንን ውስንነት በመረዳት በውስንነት ውስጥ የምንኖር በመሆናችን መደጋገፋችን የግድ መሆኑን በመገንዘብ መኖር ብልህነት ነው፡፡ ራስን ውስንነት የሌለበት፤ ሌላውን ግን በውስንነት የሚኖር አድርጎ የመሳል ውስንነትን በማስወገድ፡፡

## 2) ሰው

በምድር ላይ እየሆነ ያለውን ሁሉንም እንቅስቃሴ ሰውን አውጥተን ለማየት እንሞክር፡፡ ትራንስፖርት ዘርፉን ከሰው ለይተን እንየው፡፡ ትምህርት ቤቶችን ከሰው ለይተን እንያቸው፡፡ እግር ኳስን ከሰው ለይተን እንየው፤ ሆስፒታሎቻችንም እንዲሁ፡፡ ሆቴልም ቢሆን ወይም ሚዲያ፡፡ ግብርና ቢሆን ኢንዱስትሪ ወዘተ ከሰው ለይተን እንመልከተው፡፡ ምን ይታየን ይሆን? ምንም ሊታየን አይችልም፡፡ እፅዋትም ሆኑ አዕዋፍትን፣ ጸሐይም ሆነች ከዋክብትን፣ የወቅት መፈራረቅም ሆነ እሳተ ጎሞራ ሁሉም ሰውን ማዕከል አድርገው ሲታዩ ነው ትርጉማቸው የሚታየው፡፡ ሁሉም ስለ ሰው ልጆች የተሰናዱ ሆነው ይታያሉ፡፡ የሰው ልጅን በልዩነት መመልከት የግድ እንደሚለን በቅጽበት በጥሞና መመልከት ብቻ ተገቢ ነው፡፡

ያከበርከው፤ ያከበርሽውን በምናስብበት ጊዜ ሰውን መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም ሰው በቦታው ሆኖ ሲንቀሳቀስ ትልቅ ነገርን መፍጠር እንደሚችል ስናስብ ለሰው የምንሰጠውን ቦታ እንረዳ፡፡ በአምላክ ጉዳይ ላይ ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ግንዛቤ ባይኖረውም በተፈጥሮ ዓይኑ ተመልክቶ የተቀራረበ አይነት መረዳትን ለመያዝ ሲሞክር ሰውን ያገኛል፡፡ ሰው ልዩ ፍጡር ነው፡፡ አንበሳን በቁጥጥሩ ስር አድርጐ ለጎብኚዎች የሚያስጎበኝ፡፡ እንዴት አድርጎ ወቅቶችን መጠቀም እንዳለበት በሺ ዓመታት ውስጥ ስሌቱን አግኝቶ መስመሩን ያሳመረ፡፡

ለሕይወት ያለን ግንዛቤ ጤናማ ይሁን አይሁን ለመመርመር ስናስብ ስለሰው ያለንን ግንዛቤ በመመርመር ብንጀምር ከብዙ ድካም ያተርፈናል፡፡ ሰው በቃ ሰው ነውና፡፡ በእድሜው፣ በጾታው፣ በትምህርት ደረጃው፣ በደረበው ማዕረግ ወዘተ ሳይሆን ሰው እንዲሁ ሰው በመሆኑ ብቻ ልዩ ቦታን የተሰጠው ሆኗልና፡፡ ያከበርከው ምን እንደሆነ በምትጠይቅበት ጊዜ ለሰው ያለህን ቦታ መርምር፡፡ ያከበርሽውን በምትዘረዝሪበት ጊዜ ለሰው ያለሽን ቦታ መርምሪ፡፡ ሰው አስቀድመን እንዳልን ሰው ነው፡፡

በሕይወት ውስጥ የሚገጥሙን ችግሮች ከችግሮቹ መፈጠር እንዲሁም ከችግሮቹ መውጫ ስሌት ውስጥ ሰው በደንብ አለ፡፡ ዛሬ በምን ችግር ውስጥ እንገኝ ይሆን? ዛሬ ያለንበት ችግር ከሰዎች ጋር ባለን መስተጋብር የተፈጠረ ይሆን? መውጫውን ስናስብስ የምንሻው የሰዎች እርዳታ ይኖር ይሆን? ምላሹ አዎን ሊሆን እንደሚችል ጸሐፊው ያምናል፡፡ ፈጣሪ ሰዎችን ተጠቅሞ ወደ መፍትሔ እንድንደርስ እንደሚረዳን እናምናለን፡፡ ሰዎችን ተጠቅሞ መባሉን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

አለን የምንለውን በሙሉ ዘርዝረን ትርጉም በሚሰጥ መነጽር ስናየው ሁሉንም ወደ ፈጣሪ የመውሰድ አተያይ እንዳለን በሰፊው ይስተዋላል፡፡ ለእኔ እንደ አንድ አማኝ ትክክለኛና ጤናማ አተያይ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በፈጣሪ ስር ነገሮችን በማድረግ ደግሞ ነገሮችን ነጣጥሎ ከመመልከት ሊከለክለን እና የጠራ መረዳት እንዲኖረን ከመደረግ መከልከል አለብን ብዬም አላምንም፡፡ ሁሉም ነገራችን ምንጬ ፈጣሪ ቢሆንም፤ በራሱ መንገድ የምንገልጸው መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ መልካም ሰዎች ከአምላክ እናገኝ ይሆናል፤ መልካም ሰዎችን በዙሪያችን ማቆየት ግን የእኛ ኃላፊነት መሆኑን መረዳት አለብን፡፡

ያከበርከው በሕይወትህ ውስጥ ትርጉም እንደሚሰጥ መረዳቱ ካለህ ሰውን እንዴት እንደምትመለከት ዛሬ መርምር፡፡ የእይታ ለውጥ የአዲስ ዘመን መነሻ ቢሆን ምንኛ ባተረፍን፡፡ ሰዎችን በገንዘባቸው ብዛት ለከተሃቸው ይሆን? በትምህርት ደረጃቸው ወይንስ በምን? ዛሬ ቆም ብለን ማሰብ የሚገባን ማንኛውም ሰው ጨቅላ ይሁን አዛውንት፣ ባለ ማስተርስ ይሁን ፊደል ያልቆጠረ፣ ባለቢሊዮን ይሁን እጁን ለምጽዋት የዘረጋ፣ ወዘተ ማንም ሰው ክቡር ነው፡፡ መከበር የሚገባው፡፡ በአስተሳሰብ ወቅራችን ውስጥ በተፈጥሮ ዓይናችን ከምናያቸው ፍጡራን ሁሉ ልዩ ቦታ ልንሰጠው የሚገባ፡፡

ሁሉም ሰው በሰውነቱ የምንሰጠው ቦታ እንዳለ ሆኖ በተለየ ሁኔታ የምንመለከተው ሰው በሕይወታችን ውስጥ የመኖሩ ጉዳይ አብሮ ይነሳል፡፡ ጥያቄው ትክክለኛ ጥያቄ ነው፡፡ ለሰው እንደ ሰውነቱ የምንሰጠው ቦታ እንዳለ ሆኖ ከሰዎች ሁሉ በፊት ለራሳችን የምንሰጠው ቦታ አለ፡፡ ራስን ማወቅ፣ ራስን መቀበል፣ ራስን ማዳበር ወዘተ የሚመጣው መቅደም የሚገባውን ማስቀደም ስንችል ነው፡፡ ራስን ማስቀደም ራስ ወዳድነት አይደለም፤ ራስ ወዳድነት የሚሆነው ራሳችን ላይ ያለውን አቅም ለሌሎች መመንዘር የማንችል ከሆንን ነው፡፡ ራሳችን ላይ የተሠራውን ሥራ ሌሎችን ወደ መልካም ለማምጣት የምንሠራበት ከሆነ እርሱ ራስ ወዳድነት አይደለም፡፡

ከራሳችን እልፍ ስንል ደግሞ ቤተሰባችንን እናገኛለን፡፡ ቤተሰብ ትልቅ ተቋም ነው፡፡ በአክብሮትና በጥንቃቄ መያዝ ያለበት ሰው የሚባለው የከበረ ፍጡር የሚገኝበት ትልቅ ተቋም፡፡ ከራስ አልፈን ቤተሰብን እናገኛለን፡፡ በመቀጠል የሥራ ባልደረቦች እያልን መጥቀስ እንችላለን፡፡

ከሰዎች ሁሉ በፊት ስለሚቀድመው ሰው ማሰብ ደግሞ የግድ ይላል፡፡ ሰው ሁሉ በእርግጥ እኩል ነው፡፡ ሰው ሁሉ ክብሩ ነው፡፡ ሰው ሁሉ በሰውነቱ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ከሰዎች ሁሉ በፊት ግን ራንስ መመልከት መቻል፣ ቤተሰብን፣ የሥራ ባልደረቦችን ወዘተ እያለን መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ከሁሉ የሚቀድመው ራስ መሆኑ መሰመር አለበት፡፡

ሁሉም በቦታው ስናስብ ሁሉም በቦታው የምንጠብቀውን ሰውን አሰብን፡፡ ሰው በጊዜ ውስጥ ትርጉም ያለው ሥራን የሚሠራ መሆኑን ደግሞ ቀጥለን እንመልከት፡፡ እግር ኳስ ተጫዋች ጫማ ከመስቀሉ በፊት የሚመለከተው አንድ ነገር እድሜውን ነው፡፡



## 3) ጊዜ

ዘጠና ደቂቃ በእግር ኳስ ውስጥ ትርጉሟ ብዙ ነው፡፡ ሁሉም የዘርፉ ተዋንያን ከሜዳ ጨዋታው ባሻገር በየመስመራቸው የበዛ ተግባራትን ያከናውኑበታል፡፡ የቤንጃሚን ፍራንክሊን "ጊዜ ገንዘብ ነው" የሚለውን አባባል ከሊኦ ቶልስቶይ "ሁለቱ ኃያል መሣሪያዎች ትዕግስትና ጊዜ" ናቸው የሚለውን አቀናጅተን ስናይ ጊዜ ከገንዘብም በላይ የሆነ በሕይወት ውስጥ ዘርፈ ብዙ ትርጉም እንዳለው እንረዳለን፡፡

"የሀበሻ ቀጠሮ" የተሰኘው ያልተጻፈውን ሕግ ለራሳችን አንብበን ስለ ጊዜ ያለንን መረዳት እንፈትሽ፡፡ ሰው በመሆናችን ውስጥ ካሉን ሃብቶች መካከል ቀዳሚው ጊዜ ነው፡፡ በጊዜ ውስጥ መሆን የምንሻውን ለመሆን ጉዞ እናደርጋለን፡፡ በጊዜ ውስጥ የሆነውን መርምረን በነገው ጊዜ ውስጥ ማስተካከያውን እንተልማለን፡፡ ትምህርት ለመቅሰም ይሁን ገንዘብ ለመሥራት፤ ወደ ስልጣን ለመውጣትም ይሁን ከስልጣን ለመውረድ ጊዜ ትርጉሙ ብዙ ነው፡፡ ለማከናውን ባቀድነውና በተጨባጭ በተከናወነው መካከል ሰፊው ልዩነት ለጉዳዩ የተሰጠው ጊዜም ሆኖ ይታያል፡፡

ሁሉም በቦታው ሆኖ ስለሚሠራው አስደናቂ ነገር በምናስብበት ወቅት ጊዜን መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ ያከበርሽው ምን እንደሆነ በምትጠይቂበት ቅጽበት ስለጊዜ ላታስቢ በፍጹም አትችይም፡፡ "ጊዜ ዳኛ ነው" ይባላል፤ አዎን ዳኛ ነው፡፡ ጊዜ ዳኛ ብቻም አይደለም "ጊዜ አቃቢ ሕግም" ነው፡፡ ጊዜ መምህርም ነው፡፡ ጊዜ ሐኪምም ነው፡፡ ጊዜ መጽሐፍም ነው፡፡ ጊዜ ፊልምም ነው፡፡ በአጭሩ ጊዜ ሁሉንም ነገር ነው፡፡

ወቅት ሲቀየር የሚቀየረው በጊዜ ስሌት ውስጥ መሆኑንም መዘንጋት አይገባም፡፡ የዘመን መለወጫ የቁጥር ለውጡ በሕይወት ውስጥ ትርጉም ይኖረው ዘንድ ትክክለኛ እይታን ከሚሹት መካከል ጊዜ ተጠቃሽ ነው፡፡ በምርት ወቅት ጎበዙ ገበሬና ሰነፉ ገበሬ የሚለዩት ለግብርናቸው በሰጡት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ በተማሪውም ሆነ በነጋዴው ስሌቱ ተመሳሳይ ነው፡፡

መስጠትን የሕይወቱ መርሕ ላደረገ ሰው ከመቀበል ይልቅ መስጠትን ያስቀድማል፡፡ አልበርት አንስታይን "የሰው ልጅ ዋጋ መቀበል በቻለበት አቅም ሳይሆን በመስጠቱ ይለካል" ማለቱን ልብ እንላለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም "ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው" በማለት የመስጠትን ዋጋ ይገልጻዋል፡፡ የሚሰጠው ነገር ምንድን ነው የሚለውን ማወቅም እንዲሁ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ለጊዜ ትኩረት መስጠት ሲባል ለምን ጉዳይ ምን አይነት ሰዓት የትኛውን ሰዓት ብሎ መደቦ መጠቀምን ይጠይቃል፡፡ በእውቀት ደረጃ ብዙ ሰዎች ጊዜን በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ ቢያስቡም እንዴት የሚለው ግን ጥያቄ ይሆናል፡፡

ሁሉም በቦታው ታሪክን እንዲሠራ ለጊዜ ከፍተኛውን ቦታ እንስጥ፡፡ የዘጠና ደቂቃንም ሆነ ጫማ የመስቀያውን እድሜ እናስብ፡፡ መልካም አብሮ የመቆም፣ መልካም ውጤት፡፡

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የአንድ ጠገራ ብር ቱሩፋት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ተወልደው ያደጉት በቀድሞው ወለጋ ክፍለ ሐገር ሆሮ ጉድሩ ነው:: ወላጅ አባታቸው የቄስ ትምህርት አጠናክረው እንዲቀጥሉና ፣ ግዕዝ ተምረው፣ ዳዊት ደግመው፣ ቄስ እንዲሆኑ ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው:: እርሳቸው ግን ለንግድ ጥልቅ ፍላጎት ያላቸው በመሆኑ ገና በታዳጊነት ዕድሜያቸው ጀምረው ያስቡትን የንግድ ሥራ ለማሳካት ያወጡና ያወርዱ ጀመር::

በልጅነት ዕድሜያቸው ‹‹ነጋዴ መሆን አለብኝ›› በማለት በ 14 ዓመታቸው የንግድ ሥራን ‹‹ሀ›› ብለው የጀመሩት የዛሬው የስኬት እንግዳችን አቶ ጠና ከበደ ናቸው:: በ14 ዓመታቸው ከወላጅ እናታቸው አንድ ጠገራ ብር ተበድረው በዶሮ ንግድ የንግድ ሥራን የተቀላቀሉት አቶ ጠና፤ ከስድስት አስርት ዓመታት በላይ በተለያዩ የንግድ ሥራዎች በመሳተፍ ውጤታማ ሆነዋል:: ‹‹ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል›› እንዲሉ እስከ አስመጪነት ደርሰዋል:: የሕንጻዎችና የሆቴልና ሪዞርት ባለቤት መሆን ችለዋል::

ለንግድ ባላቸው ጥልቅ ፍላጎት ላይ የግል ጥረትና ትጋታቸው ታክሎበት በንግድ ሥራቸው አንቱ የተባሉት አቶ ጠና፤ የሕይወት ዘመናቸውን ሙሉ በሚባል ደረጃ ጊዜያቸውን ለንግድ ሥራ ሰጥተዋል:: በንግድ የሕይወት ጉዟቸውም እስራትን፣ ስደትን ጨምሮ የተለያዩ ውጣ ውረዶችን አሳልፈዋል:: በመውጣት በመውረዳቸው ውስጥ እግዚአብሔር አብሯቸው ይመላለስ እንደነበር በጽኑ የሚያምኑት አቶ ጠና፤ ዛሬ ለደረሱበት ስኬት ምክንያቱ የእግዚአብሔር እርዳታ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ::

ከዶሮ ንግድ ቀጥለው በሸቀጣ ሸቀጥ፣ በመኪና ዕቃ መለዋወጫና በመኪና ኪራይ፣ ብትን ጨርቅ ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ በማስመጣት እና በሌሎችም የንግድ ሥራዎች ተሳትፈዋል:: በእነዚህና መሰል የንግድ ሥራዎች ወጥተው ወርደው ባካበቱት ጥሪትም በአዲስ አበባ ቦሌ ስካይ ላይት ሆቴል ፊትለፊት የሚገኙ እያንዳንዳቸው ስምንት ፎቅ ያላቸውን ሁለት ሕንጻዎች ገንብተዋል:: በቅርቡም ቢሾፍቱ ቲኬ ሆቴልና ሪዞርትን ገንብተዋል::

ከአርሶ አደር እንዲሁም ፈሪሃ እግዚአብሔር ካደረበት ኃይማኖተኛ ቤተሰብ ስለመገኘታቸው የሚናገሩት አቶ ጠና፤ አባታቸው በወቅቱ የንግድ ሥራቸውን ተቃውመው እንደነበርም ያስታውሳሉ:: ገና በጠዋቱ ‹‹የወዲፊት ዕጣ ፈንታዬ ነጋዴ መሆን ነው›› ያሉት አቶ ጠና፣ የወላጅ አባታቸውን ቁጣ ቻል አድርገው ለነብሳቸው ጥሪ ምላሽ በመስጠት የዶሮ ንግድ ሲጀምሩ ዛሬ ላይ እዚህ እደርሳለሁ በሚል አልነበረም::

ይሁንና በወቅቱ ከወላጅ እናታቸው በወሰዱት አንድ ጠገራ ብር በአካባቢያቸው ከሚገኝ ገበያ እያንዳንዳቸው 20 ሳንቲም ያወጡ ስምንት ዶሮዎችን በመግዛት የልጅነት ህልማቸውን ዕውን ለማድረግ ጉዟቸውን አንድ ብለው ጀመሩ:: በ20፤ 20 ሳንቲም የተገዙት ዶሮዎችም በእጥፍ አትርፈው እያንዳንዳቸው በ40 ሳንቲም ተሸጡ:: ከወላጅ እናታቸው የተበደሩትን ገንዘብ ወዲያው ከፈሉ:: በወቅቱ በእጥፍ አትርፈው አንድ ጠገራ ብር ማግኘት በመቻላቸው ደስታቸው እጥፍ ድርብ እንደነበርም አጫውተውናል::

በትርፋቸውም ተጨማሪ ዶሮዎችን ገዝተው በመሸጥ የንግድ ሥራቸውን ማቀላጠፍ ቀጠሉ:: የዶሮ ንግዱ ጠቀም ያለ ትርፍ ሲያመጣላቸው የንግድ ሥራቸውን ከዶሮ ንግድ ወደ ሸቀጣሸቀጥ ሱቅ አሳደጉት:: የሸቀጥ ንግዱም እንዲሁ ከፍ ከፍ እያለ ሲሄድ መኪና እንዲገዙ በር ከፈተላቸው:: መንጃ ፈቃድ አውጥተው በመኪናው ሲሰሩ ቆዩና የመኪናዎቹን ቁጥር ሶስት አደረሱ:: ይህን ጊዜ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የንግድ ሥራቸውን ይበልጥ ማስፋት ያሰቡት አቶ ጠና፤ መኪኖቻቸውን በሙሉ ይዘው ወደ አዲስ አበባ በመምጣታቸው ኑሮው ብዙም አልፈተናቸውም::

አዲስ አበባ ሲገቡ የመጀመሪያ እርምጃቸው የኔታ



**አቶ ጠና ከበደ**

ዘንድ ፊደል ቆጥረው ዳዊት ደግመው ገታ ያደረጉትን ትምህርት መቀጠል ነበርና ካቴድራል ትምህርት ቤት በመግባት በማታው ክፍለ ጊዜ ትምህርታቸውን ቀጥሉ:: ከትምህርታቸው ጎን ለጎን የመኪና ሥራቸውን በማስፋፋት አምስት ስድስት እያሉ የመኪኖቻቸውን ቁጥር አበራከቱ:: ከነተሳቢዎቹ አስር የደረሱት መኪኖች አሰብ ድረስ እየሄዱ የጭነት አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ ፈጠሩላቸው:: በዚህ ጊዜም ነው ትዳር የመሰረቱት::

በወቅቱ ገቢያቸው እየተበራከተ ሲመጣ የንግድ ቤት መግዛት እንዳለባቸው አሰቡ:: አስበውም አልቀሩ፤ ፒያሳ ራስ መኮንን ድልድይ አቅራቢያ ሞዝቮልድ አጠገብ የሚገኘውን ህንጻ በ650 ሺ ብር መግዛት ቻሉ:: በሕንጻው አንዱ ክፍል ቢሯቸውን በማድረግ ቀሪዎቹን ደግሞ በማከራየት ሥራቸውን ቀጠሉ:: ወቅቱ ደርግ ወደ ሥልጣን የመጣበት በመሆኑ ብዙም ሳይቆይ ደርግ ‹‹የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ሁሉ የመንግሥት ነው›› የሚል አዋጅ አወጣ:: አዋጁም ተግባራዊ ሆነና ሙሉ ሕንጻቸው በመንግሥት ተወረሰ::

አቶ አሁንም ተስፋ አልቆረጡም:: ‹‹ደርግ የማይወርሰው ምንድነው›› ብለው መጠየቅ ጀመሩ:: የማይወርሰው የሸቀጥ ንግድ መሆኑንም ተረዱ፣ መርካቶ ጣቃ ጨርቅ ቤት ከፍተው ብትን ጨርቆችን ከኮርያ በማስመጣት ማከፋፈል ጀመሩ:: ብዙም ሳይቆይ በድጋሚ ደርግ የገቢ ንግዱን የሚከለክል አዋጅ አወጣ:: በወቅቱ ከፍተኛ መጠን ያለው ጣቃ ጨርቅ ከኮርያ እንዲመጣላቸው አዘው መርከብ ላይ ነበርና አጋጣሚው ጥሩ የገበያ ዕድል ፈጠረላቸው:: እጃቸው የገባው ከፍተኛ መጠን ያለው ጣቃ ጨርቅ ሌሎች ዘንድ ባለመኖሩ በእጥፍ ተሸጦ በብዙ ማትረፍ አስችሏቸዋል::

ወቅቱ ገንዘብ ያለው ሰው የማይፈለግበት የደርግ ዘመን እንደመሆኑ አቶ ጠና ከዶሮ ንግድ ጀምረው ባካበቱት ሀብት አድሃሪ ተብለው ታስረዋል:: የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው በዋስ ሲፈቱ አገራቸውን ለቀው ለመሰደድ ተገደዱ::

ያኔ በናይሮቢ ኬንያ አድርገው አሜሪካ ገቡ:: በአሜሪካም ከነብሳቸው የተወዳጀውን የንግድ ሥራ ቀጥለው የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን ሠርተዋል:: ከአሜሪካ ስራዎቻቸው መካከልም ትልቅ ሱፐርማርኬት ከፍቶ በርካታ ሸቀጦችን መነገድ አንዱ እንደነበር ያስታውሳሉ:: ከሥራቸው ጎን ለጎንም እዛው አሜሪካ ከልጆቻቸው ጋር በመሆን የኮሌጅ ትምህርታቸውን ተከታትለው ዲፕሎማ አግኝተዋል::

ከ 12 ዓመታት የስደት ቆይታ በኋላ የደርግ ዘመነ መንግሥት አክትሞ የኢህአዴግ መንግሥት ሥልጣኑን ሲረከብ ወደ አገራቸው የተመለሱት አቶ ጠና፣ ኢትዮጵያ በገቡበት ፍጥነት የንግድ ሥራቸውን ለመቀጠል አልተቸገሩም:: የጣቃ ጨርቅ ከኮርያ በማስመጣት የቀድሞ የንግድ ሥራቸውን ማስቀጠል ቻሉ::

ይህ ብቻም አይደለም፤ ማርሻል የመኪና ጎማ ከኮርያ ወኪል ሆነው በማስመጣት ያከፋፍሉም ጀመር:: የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦችንም እንዲሁ ከውጭ አገራት ወደ አገር ውስጥ ማስገባቱን ተያያዙት:: ቀስ በቀስም ወደ ቀደመው ሀብታቸው በመመለስ መደራጀት ሲጀምሩ አሜሪካ ትተዋቸው የነበሩትን ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን ወደ ሀገር ቤት እንዲመጡ በማድረግ የንግድ ሥራቸውን ቀጠሉ::

ከስደት ወደ አገራቸው ተመልሰው በኪራይ ቦታ የንግድ ሥራቸውን ያስቀጠሉት አቶ ጠና፤ መሬት በሊዝ ገዝተው ሕንጻ መሥራት እንዳለባቸው በማሰብ መሀል ቦሌ ላይ 1009 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ቦታ በመግዛት ሕንጻ ገነቡ:: በድጋሚም ከጎኑ ያለውን ቦታ በሊዝ በመግዛት ተጨማሪ ሕንጻ በመሥራት ለቢሮ ማከራየት ችለዋል::

አቶ ጠና ቦሌ ከስካይ ላይት ሆቴል ፊት ለፊት ጠና ቲኬ ህንጻ / ከበደና ቤተሰቦቹ በሚል የሚጠሩትን እያንዳንዳቸው ስምንት ወለል ያላቸውን ሁለት ሕንጻዎች በመገንባት አላቆሙም:: ወደ ሆቴል ኢንቨስትመንት ፊታቸውን በማዞር በቢሾፍቱ ሀይቅ ዳር ባለ አምስት ኮከብ ደረጃ ያለውን ቢሾፍቱ ቲኬ ሆቴልና ሪዞርትን ገነቡ::

ሆቴሉ ከሌሎቹ ሆቴልና ሪዞርቶች ልዩ የሚያደርጉት በርካታ መሰረተ ልማቶች ያሉት ሲሆን፣ የሆቴል ግንባታው ከየትኛውም ሥራ በበለጠ እንዳደከማቸውም አቶ ጠና ያስታውሳሉ:: ቦታውን ለማግኘት ከክልሉ አስተዳደር ጋር ያደረጉትን እልህ አስጨራሽ ጥረትን ጨምሮ ሆቴሉን ገንብቶ ለማጠናቀቅ አጠቃላይ 13 ዓመታት ወስዶባቸዋል::

ሆቴሉ በሀይቅ ዳርቻ አቅራቢያ እንደ መገንባቱ ከሆቴሉ እስከ ሃይቁ የሚወስዱ 450 ደረጃዎች አሉት:: እጅግ አስቸጋሪና ገደላማ የሆነውን ቦታ በማልማት ሀይቁ ከሆቴሉ ሥር ረግቶ እንዲቀመጥና ለአይን እንዲማርክ ሆኗል:: ሆቴልና ሪዞርቱን ለመገንባት 750 ሚሊዮን ብር ወጪ እንደተደረገበትም ይገልጻሉ::

ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ የበኩላቸውን የተወጡት አቶ ጠና፤ የቢሾፍቱ ቲኬ ሆቴልና ሪዞርት ብቻ ለ150 ሠራተኞች፤ በሕንጻዎቻቸው ሥርም እንዲሁ ለ200 ዜጎች በድምሩ ለ350 ሠራተኞች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል::

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ሰፊ አበርክቶ ያላቸው አቶ ጠና፤ በአሁኑ ወቅት ከሆቴሉም ሆነ ከሕንጻዎቻቸው የሚገኘው ገቢ ለሁለት ተከፍሎ ግማሹ ለበጎ አድራጎት ይሰጣሉ፤ ግማሹን ደግሞ ለልጆቻቸው ያስቀምጣሉ:: በተለይም ጠና ከበደ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚለው መጠሪያ አቅመ ደካሞችን በመርዳት የበጎ አድራጎት ሥራ ይሠራሉ:: ለአብነትም በተለያየ ቦታ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ለቤተክርስቲያንና አቅመ ደካማ ነኝ ብለው ለሚመጡ ሁሉ መርጃ ይውላል::

በዚህ የበጎ አድራጎት በቋሚነት በየወሩ እየመጡ ሶስት ሺ ብር ከሚወስዱ ግለሰቦች በተጨማሪ የተለያዩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችም ተጠቃሚዎች ናቸው:: ለመቄዶንያ የአረጋውያን መርጃ ድርጅት ብቻ በዓመት አንድ ሚሊዮን ብር የሚሰጡት አቶ ጠና፣ ይህ በጎ ሥራ በእጅጉ የሚያስደስታቸው እንደሆነ ነው ያጫወቱን::

‹‹ከምንም ተነስቼ ድህነትን ለማሸነፍ ባደረግኩት ጥረት ዛሬ ላይ መድረሴን ሳስበው የሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር እገዛ እንደሆነ አምናለሁ:: እዚህ ላደረሰኝ አምላክም ምስጋና አቀርባለሁ›› የሚሉት አቶ ጠና፤ ዕድሜ ዘመናቸውን በሙሉ በንግድ ሥራ ውስጥ ወጥተዋል፤ ወርደዋል፤ ባፈሩት ሀብትና ንብረትም ለልጅ ልጅ የሚተርፍ ተግባር አከናውነዋል:: በቅርቡም 80 ዓመታቸውን ያከበሩ ሲሆን፣ ከእንግዲህ እረፍት ያስፈልገኛል በማለት ጡረታ ለመውጣት ተሰናድተዋል::

በአሁኑ ወቅትም ድርጅቶቻቸውን ለልጆቻቸው በማስረከብ ሂደት ላይ የሚገኙት አቶ ጠና፤ በቀጣይ በብዙ ድካምና ጥረት ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ልጆቻቸው በአግባቡ ማስተዳደር እንዲችሉ ይመክራሉ:: በተለይም ልጆቻቸው ድርሻቸውን ከመጠቀም ባሻገር ለእግዚአብሔር የሚገባውን መባእና አስራት እንዲያወጡ፣ ድሆችን መርዳት እንዳይረሱና እርሳቸው የጀመሯቸውን ራዕዮች ጠብቀው ሥራውን እንዲያስፋፉ ምኞትና ፍላጎታቸው ነው::

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ሊስፋፉ የሚገባቸው የመስኖ ቴክኖሎጂዎች

**መላኩ ኤሮሴ**

ኢትዮጵያ በብዙ ጅረቶችና በትላልቅ ወንዞች የተከበበ በሚሊዮን ሄክታር የሚቆጠር በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት አላት፡፡ በግብርናው ዘርፍ ለሚታየው ተጨባጭ ለውጥ የመስኖ ልማት መስፋፋት እጅግ መሠረታዊ ከመሆኑ አንጻር ይህን የተፈጥሮ ሃብት በሚገባ ጥቅም ላይ ማዋል የአርሶ አደሩን ሕይወት የበለጠ ለማሻሻል እና ግብርና በሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ የሚኖረውን አስተዋጽዖ ይበልጥ ለማሳደግ በእጅጉ ይረዳል፡፡ በአፍሪካ ሊታረስ ከሚችለው ጠቅላላ መሬት ስድስት በመቶ የሚሆነው ብቻ እስካሁን ድረስ በመስኖ የለማ ሲሆን የተቀረው መሬት ግን የመልማት ከፍተኛ አቅም ያለው ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውል ቆይቷል፡፡

ኢትዮጵያ ከዚህ የልማት ሬሾ ውስጥ የተሻለ እንቅስቃሴ ከሚታይባቸው ሀገራት መካከል ብትሆንም ሀገሪቱ ካላት የውሃ ሃብት እና ለመስኖ ምቹ ከሆነው የመሬት ሀብት አንጻር እስካሁን የለማው የመሬት መጠን የሚያኩራራ አይደለም፡፡ ባለፈው ዓመት ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የወጣው መረጃ እንደሚያሳየው በመስኖ ሊለማ ከሚችለው መሬት ውስጥ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ እየለማ ነው፡፡

እ.አ.አ. በ2018 የማላቦ ሞንትፔለር ፓናል ይፋ ያደረገው ሪፖርት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ከ1994 አንስቶ የመስኖ ልማት እድገቱ በ52 በመቶ እድገት ያስመዘገበ ሲሆን በ2007 ብቻ ለመስኖ ዝግጁ የሆነው የሚታረስ መሬት በሄክታር 848 ሺህ 340 ሄክታር ደርሶ እንደነበር በሪፖርቱ ተመዝግቧል፡፡ ከዚያ በኋላ የመጣውን ሀገራዊ ለውጥ ተከትሎ ለመስኖ ዘርፍ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

ይህንን ሁኔታ ለመቀየር የአስር ዓመት እቅድ ላይ ለመስኖ ፕሮጀክቶች ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው፡፡ ሀገሪቱ ለመስኖ ልማት ከፍተኛ በጀት መድባ እየተንቀሳቀሰች ሲሆን፤ በተለይም በቆላማ አካባቢዎች ለመስኖ ልማት ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል፡፡ በተለይም መንግሥት በወሰደው ተነሳሽነት የሀገሪቱን የስንዴ ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በሚደረገው ከፍተኛ ጥረትም የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ከመሸፈን አልፎ ወደ ውጭ ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ግብ ተቀምጦ እንቅስቃሴዎች ቀጥለዋል፡፡

በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት አገልግሎት እየሰጡ ካሉ አነስተኛ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች መካከል ትሪድል ፓምፕ፣ ዋሸር ፓምፕ፣ ሮፕ ፓምፕ እና የመሳሰሉት ቴክኖሎጂዎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንደ መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መረጃ ከሆነ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በሀገራችን በመጠኑም ቢሆን አገልግሎት መስጠት እየጀመሩ ነው፡፡ እነዚህን ቴክኖሎጂዎችን ለማዳረስ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ብዙነህ ቶልቻ እንደሚሉት፤ አንዳንድ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች በሀገሪቱ ውስጥ ጥቅም ላይ እየዋሉ ሲሆን፤ ሀገሪቱ ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ካሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች መካከል የወለል መስኖ ቴክኖሎጂ አንዱ ነው፡፡ የወለል መስኖ በአገራችን በአንፃራዊነት ለረዥም ዓመታት የተለመደና እየተተገበረ ያለ የመስኖ ቴክኖሎጂ ሲሆን ለጥጥ፣ ለበቆሎ፣ ለሸንኮራ አገዳ ወዘተ እና ሰፋፊ ሄክታር ለሚሸፍኑ ሰብሎች ተስማሚ ቴክኖሎጂ ነው።

ተፋሰስን መሠረት በማድረግ የፈሮው (የቦይ) መስኖን በማቀናጀት የሚተገበር ሲሆን የውሃ ፍሰቱ ጥሩ በመሆኑ አፈር ውስጥ ሰርጎ ለመግባት አይቸገርም፡፡በአብዛኛውሜዳማበሆኑማሳዎችጥቅምላይ ይውላል፡፡ የወለል መስኖ አካል የሆነው ተፋሰስ መስኖ ጎርፉን በትንንሽ ቦዮች በመጥለፍ ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ ይህም ለሜካናይዝድ ሰፋፊ የእርሻ ማሳዎች እንደሚያገለግል አብራርተዋል፡፡

የወለል መስኖ አካል የሆነው የፈሮው (ቦይ) መስኖ በሰፋፊ ማሳዎች ላይ ትናንሽ ሰርጦችን በመፍጠር ጥቅም ላይ እንደሚውል ያብራሩት አቶ ብዙነህ፤ ውሃው



**የመሐል ምሰሶ መስና ቴክኖሎጂ**

በእያንዳንዱ ጉድጓድ አናት ጫፍ ላይ በስበት ኃይል የሚፈስ ሲሆን ይህም በተዘጋ ቧንቧና በሳይፈን አማካኝነት ውሃውን ይረጫል፡፡ የፈሮ መስኖ በተለይ ለጥጥ፣ ለበቆሎ ለሸንኮራ አገዳና መሰል ሰፋፊ ሄክታር ለሚሸፍኑ ሰብሎች ተስማሚ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ብዙነህ ማብራሪያ፤ በስፋትም ባይሆን የርጭት ስፕሪን ኪለር የሚባለው በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተሞክሯል፡፡ በአማራ ክልል ራያ ቆቦ አካባቢ፣ በትግራይ ክልል ራያ አዘቦ አካባቢ ስፕሪን ኪለር ጥቅም ላይ ሲውል ነበር፡፡ በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ቢሆንም ስፕሪን ኪለር የሚባለው የመስኖ ዘዴ ተሞክሯል፡፡

የሀገሪቱን የመስኖ ልማት ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች እስካሁን በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ እየዋለ አይደለም፡፡ የመሐል ምሰሶ መስኖ ቴክኖሎጂ እና የግፊት ተንቀሳቃሽ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ለሀገራችን የመስኖ ዘርፍ ሽግግር ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ናቸው፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ የመሐል ምሰሶ መስኖ (Center Pivot Irrigation) ቋሚ ምሰሶ ላይ በተሠራ የብረትና የአሉሚኒየም ቧንቧ ተሽከርካሪ ማማዎች ላይ በተገጠሙ የውኃ መስመሮች የውሃ ማጠጫ መስኖ ዘዴ ነው። ውሃ ተሸካሚው ማሽን 360 ዲግሪ የሚንቀሳቀስ ሲሆን በክቡ መሐል ካለው ምሰሶ ውኃውን በሁሉም ቅርንጫፎች ይረጫል።

ለመሐል ምሰሶ አቀማመጥ ምቹነት ሲባል መሬቱ በተመጣጣኝ ሁኔታ ለጥ ያለ ሜዳ ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ይህ ቴክኖሎጂ ለቆላማና ሜዳማ አካባቢዎች በጣም ተስማሚ ነው፡፡ መሐል ምሰሶ በበርካታ የዓለማችን ክፍሎች የመስኖ እርሻ ልማትና የውሃ አጠቃቀም ቴክኖሎጂ እንዲጨምር አድርጓል።

በተለይም በዩናይትድ ስቴትስ፣ በአውስትራሊያ፣ በኒውዝላንድና ብራዚል እንዲሁም ከሰሃራ በረሃ በታች ባሉ ሀገራትና በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የመሐል ምሰሶ መስኖ ልማት በሀገራችን ኢትዮጵያ በተወሰኑ አካባቢዎች የተጀመረ ሲሆን በተለይም ራያ፣ ሑመራ፣ አፋርና ሶማሌን በመሳሰሉ ሞቃታማና ቆላማ አካባቢዎች ላይ ቢተገበር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

የመሐል ምሰሶዎች በተለምዶ ከ500 ሜትር ርዝመት ክብ ራዲየስ ያነሱ ሲሆኑ በመደበኛነት የተለመደው መጠንም 400 ሜትር ርዝመት ያለው ራዲየስ ማሽን ነው። የተለመደው 400 ሜትር ራዲየስ የሰብል ማሳ 125 ሄክታር መሬት ይሸፍናል፡፡ ይሁን እንጂ ቴክኖሎጂው ውድና በቅርብ የማይገኝ በመሆኑ እንዲሁም በሜዳማ አካባቢዎች ብቻ የሚያገለግል ሆኖ የራሱ ውስንነት እንዳለበት ይነሳል፡፡

በሀገራችን በስፋት ጥቅም ላይ ቢውል ከፍተኛ ጠቃሜታ የሚያስገኘው እና እስካሁን ድረስ ብዙም ጥቅም ላይ ያልዋለው የግፊት ተንቀሳቃሽ የመስኖ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ የግፊት ተንቀሳቃሽ የመስኖ ቴክኖሎጂ በሚባለው የቴክኖሎጂ ዓይነት ቴክኖሎጂው በፓይፕ ወይም በቱቦ አማካኝነት ውሃውን በበርካታ ቀዳዳዎቹ እንዲረጭ በማድረግ ማሳውን በቂ ውሃ ያጠጣል፡፡ መሳሪያው እየተሽከረከረ ሌሎች ስፍራዎችን ውሃው በርጭት እንዲያዳርስ ያደረጋል።

ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፤ የግፊት ተንቀሳቃሽ መስኖ በእርሻው መካከል ረጅም የውሃ ምሰሶ በመትከል ውኃውን በቋሚ የገመድ ቱቦ በማፍሰስ የሚተገበር ሲሆን ከ100-130 ሚሊ. ሜትር ወይም ከአራት እስከ አምስት ኢንች ዲያሜትር የአሉሚኒየም ቧንቧ ለዚህ አገልግሎት ይውላል። ቴክኖሎጂው በውኃው መጠንና በሚለማው ሰብል ቁመት ላይ የተመረኮዘ ነው። የግፊት ተንቀሳቃሽ መስኖ ለአሠራር ምቹ በመሆን፣ ተለዋዋጭ ባህሪ ባለመኖሩ፣ በብዛት በመርጨት፣ ትንሽ ቦታ በመያዝ፣ ወጭን በመቀነስ፣ ዝቅተኛ ኃይል በመጠቀምና የውሃ ጥራትን በማሳደግ ለመስኖ ልማት አስተዋፅዖው ከፍተኛ ነው፡፡

እንደ አቶ ብዙነህ ማብራሪያ፤ አብዛኞቹ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች በሀገራችን ውስጥ ገና በጅምር ደረጃ ላይ ያለ ከመሆኑ አኳያ እንዲሁም እንደ ሀገር በቂ ውሃ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ እነዚህን ቴክኖሎጂዎችን ከማስፋፋት ይልቅ የመስኖ ግድቦችን በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የማስፋፋቱ ሥራ የበለጠ ትኩረት አግኝቷል፡፡

እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በመጪው ዘመን በሀገራችን ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ የመዋል እድል እንዳላቸው የሚያብራሩት አቶ ብዙነህ፤ የውሃ እጥረት ሊያጋጥም የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ተብሎ በሚታሰብበት ጊዜ እነዚህን ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል፡፡ በተለይም እንደ ሀገር የከርሰ ምድር ውሃን በስፋት መጠቀም የሚጀመርበት ደረጃ ላይ ሲደረስ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በስፋት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ብዙነህ ማብራሪያ አብዛኞቹ የዘመናዊ መስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች ንጹሕ ውሃ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ በተለይም ደለል የሌለው ውሃ ያስፈልጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ጅምር ላይ ያሉ እንቅስቃሴዎችን የማስፋፋት ሥራው በትኩረት የሚሠራ ይሆናል፡፡

መንግሥት በተመጣጣኝ ዋጋ ሊገዙ የሚችሉ የመስኖ የፈጠራ ሥራዎች እና ቴክኖሎጂዎች ግብይት ዙሪያ መዋቅራዊ አደረጃጀት ያላቸው የማምረቻ ድርጅቶች የሚሳተፉበትን ሁኔታ መፍጠር ቢችል ድርጅቶችና በተጠቃሚው መካከል ያለውን ልዩነት ከማጥበብ አንጻር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህም የቴክኖሎጂዎቹን የግብይት ዋጋ ከአርሶ አደሮቹ አቅም ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን የአምራች ድርጅቶቹን የመሸጫ ዋጋ ቋሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስችል ይሆናል፡፡

ሀገሪቱ ካላት የሕዝብ ቁጥር አንጻር በዝናብ እየጠበቁ በዓመት አንድ ጊዜ በማምረት ብቻ የሀገሪቱን ብልጽግና ማረጋገጥ ቀርቶ የሀገሪቱን ሕዝብ መመገብ የማይታሰብ ነው፡፡ በመሆኑም የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በተለይም ዘመናዊ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች አርሶ አደሮች ዓመቱን ሙሉ እንዲያመርቱ በር የሚከፍቱላቸው ናቸው፡፡ ይህም አርሶ አደሮቹ የተሻለ ገቢ ባለቤት እንዲሆኑ የሚያስችል ነው፡፡ ለዚህም ነው በዓለማችን ያሉ ሀገራት እነዚህ ቴክኖሎጂዎችን አነስተኛ መሬት ላላቸው ለአርሶ አደሮቻቸው ለማድረስ ርብርብ በማድረግ ላይ የሚገኙት፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥም እነዚህን ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ለአርሶ አደሮች እንዲዳረሱ ማድረግ የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን አማራጭ የሌለው ምርጫ ነው፡፡ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች ወደ አርሶ አደሮቹ እንዲደርሱ ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ ይገባል፡፡

ዘመናዊ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ለማስፋፋት የሚደረገው ጥረት ለመንግሥት ብቻ የሚተው አይደለም፡፡ በትብብር መሥራትን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመንግሥት መዋቅር ስር በየደረጃው ካሉ የመንግሥት መዋቅሮች በተጨማሪ የሀገር ውስጥና ውጭ ሀገራት ባለሃብቶች ከፍ ያለ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ በተለይም በአነስተኛ ዋጋ የሚገዙ የመስኖ የፈጠራ ውጤቶችን እና ቴክኖሎጂዎችን ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት በዘርፉ ከተሠማሩት የውጭ ሀገራት እና የሀገር ውስጥ የግል ድርጅቶች ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላም ስምምነቱ አፈጻጸም ይበል የሚሰኝ ነው!

በፌደራል መንግስትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተደረሰው የሰላም ስምምነት መሰረት መንግስት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገብቷል። በተለይም አስቸኳይ የሰብአዊ እርዳታ ለሚሹ የትግራይ አካባቢዎች በቅድሚያ የሰብአዊ እርዳታ ለማድረስ ተጨማሪ ኮሪደሮችን በመክፈት ጭምር በተለያዩ አቅጣጫዎች በፍጥነትና በብዛት የሰብአዊ ድጋፉን እያደረሰ ይገኛል።

በመጀመሪያ ዙር በአንድ ሳምንት ጊዜ ብቻ የሰብዓዊ ርዳታ የምግብ አቅርቦትን በሽሬ፣ በሽራሮ፣ በአክሱም፣ በአዲ ደአሮ፣ በአዲ ነብሪ እና አዲ ሀገራይ እንዲሁም ሰለክለካ ከተሞችና ወረዳዎችን ጨምሮ በድምሩ ለ108 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች ድጋፍ አድርጓል፡፡ እንዲሁም 16 ሺህ 100 ኩንታል ስንዴ አቅርቧል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ለሰብአዊ ድጋፉ መሳለጥ የሚያግዙ የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎችን ሌት ተቀን በመስራት ላይ ነው። በጦርነቱ የተጎዱ መንገዶችንና ድልድዮችን በመጠገንና ስራ በማስጀመር እንዲሁም ለአንዳንዱ ጊዜያዊ መፍትሄ በመስጠት ጭምር የሰብአዊ እርዳታው ሳይስተጓጎል ለተረጂዎች በፍጥነት እንዲደርሳቸው የማድረጉን ስራ አጠናክሮ ቀጥሏል። ለምሳሌ ያህል ከዚህ ቀደም ከነበረው የአፋር አብአላ ኮሪደር በተጨማሪ ሌሎች አማራጭ መንገዶች እንዲከፈቱ ተደርጓል።

መንግስት ዜጎችን የመታደግ ህገመንግስታዊ ኃላፊነትም ሆነ ግዴታ አለበት፤ ከሰላም ስምምነቱም አንዱ ነጥብ ለዜጎች በወቅቱ የሰብአዊ እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ ነው። በመሆኑም መንግስት ይሄንኑ በቁርጠኝነትና በታማኝነት ተግባራዊ ማድረጉን ቀጥሏል። በዚህም መሰረት ከጥቅምት 22 እስከ 27/2015 ብቻ ከ400ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የሰብአዊ እርዳታን ማድረስ ችሏል። ከ6 ሺህ 500 ኩንታል በላይ አልሚ ምግቦች ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች እንዲደርሳቸው አድርጓል፡፡

አሁንም በሰሜን ጎንደር በኩል ወደ ሽሬ እና አጎራባች ወረዳዎች እና በሰሜን ወሎ ቆቦ ወደ አላማጣና አጎራባች ወረዳዎች እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ መስመሮች ተከፍተው ሰብዓዊ ዕርዳታና ድጋፍ ተደራሽ እየተደረገ ነው፡፡

በተጨማሪም የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በወሰደው ርምጃ ከመንገዶች በተጨማሪም አፋጣኝ የሰብዓዊ ድጋፍና ርዳታ ለማድረስ እንዲያስተባብሩ አራት ቡድኖች ተዋቅረው እየሠሩ መሆኑን አስታውቋል። ይሄ ሁሉ ርብርብ አፋጣኝ የዜጎች ሰብዓዊ ድጋፍ በሁሉም አካባቢዎች ለማድረስ ከወዲሁ ሥራዎች እየተሰሩና የመንግስትን ቁርጠኝነት ማሳያ ነው። አሁንም መንግሥት ለዜጎች አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት ተደራሽ እንዲሆን በየአቅጣጫው ከፍተኛ ርብርብ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡

በራያ፣ ራያ አላማጣ እና ኮረም ለሚገኙ ወገኖችም በተመሳሳይ ከ43 ሺህ 300 ኩንታል በላይ ስንዴ እንዲሁም ከ7 ሺህ 300 ኩንታል በላይ አልሚ ምግብ ለ287 ሺህ ዜጎች ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በድምሩም ለ396 ሺህ ዜጎች አስቸኳይ የሰብዓዊ ርዳታ መቅረቡን የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታውቋል።

በወደሙት የመሰረተ ልማት አውታሮች ምክንያት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተቋርጦባቸው የነበሩ አካባቢዎች አስቸኳይ ዝርጋታና ጥገና በማድረግ ጭምር አብዛኞቹ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል። ሌሎች ደግሞ በመልሶ መገንባት ስራ ላይ ይገኛሉ።

የመብራት ኃይል ዝርጋታው ለሰሜን ወሎ እና ለአፋር ክልል በወልድያ እየተዘረጋ ያለው መስመር እንዲያገለግል የተደረገ ሲሆን፤ ከባሕርዳር አላማጣ ያለው ዝርጋታም ጥገናው እየተጠናቀቀ ነው፡፡ ላልይበላ እና አካባቢው፣ ቆቦ እና አካባቢው እንዲሁም ሰቆጣ እና አካባቢው ሙሉ በሙሉ የመብራት ኃይል አግኝተዋል፡፡ ዝቋላ እና ዳህና ደግሞ በቅርቡ የሚያገኙ ናቸው።

በጦርነቱ የተጎዱ ዜጎች ወደ መደበኛ ኑሯቸው እንዲመለሱ በቁርጠኝነት እየተሠራ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ጥላቻን መቀስቀስ እና ልዩነትን የሚያመጡ ነገሮችን ማቆም አንዱ የሰላም የስምምነቱ አካል በመሆኑ በዚህም በኩል ሰፋፊ ስራዎች ተጀምሯል።

መንግስት በሰላም ስምምነቱ የተደረሰባቸውን ሁሉ ለማከናወን ቁርጠኛ አቋም ይዞ ወደ ተግባር መግባቱን በተግባር ያሳየ ሲሆን፤ በቀጣይ ይሄንኑ አጠናክሮ የሚያስቀጥል ይሆናል። መንግስት የሚያደርገውን ያላሰለሰ ጥረት በማገዝ በኩልም መላው ህዝብ እንዲሁም የዲያስፖራው ማህበረሰብ ርብርብ ሊያደርጉ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ወቅቱ የሰላም ድምጾችን ብቻ ለመስማት የምንገደድበት ነው

**ሚሊዮን ሺበሺ**

የሰላም ድምጽ ከሰማን እነሆ አንድ ሳምንት አለፈን ! በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል ለሁለት ዓመታት ያህል ስንሰማውና ስናየው የቆየነው አሰቃቂና አውዳሚ ጦርነት እልባት አግኝቶ ልክ በሁለተኛው ዓመት ዋዜማ ከወደ ደቡብ አፍሪካ አስደሳች ዜና ሰምተናል፡፡ ተፋላሚ የነበሩ ወገኖች እጅ ለእጅ ተጨባብጠው ማየት ሰላም ፈላጊ የሆነን ወገን ሁሉ የሚያስደስት ክስተት ነበር፡፡

እነሆ ከዚያች ቀን ጀምሮ የአገራችን አጀንዳ ሰላም ሆኗል፡፡ ታዲያ ይህ የሰላም ዜና ሲሰማ እና ያ አውዳሚ ጦርነት ሊቆም ስምምነት ሲደረግ ለፌዴራሉ መንግሥት እና ለሕወሓት መልዕክት አለኝ፤ ምንም እንኳን ፈተናዎች ቢበዙበትም የሰላም ድምጾችን ብቻ ስሙ የሚል!።

ይህ የሰላም አየር የተገኘው በፌዴራሉ መንግሥት እና በሕወሓት ቆራጥነት ነውና ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ጦርነቱ በሕዝብ ላይ ያደረሰውን እና ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት ይብቃ ብለው ለሰላም የመደራደሪያ ነጥቦችን አስቀምጠው መፈራረማቸው የውጭ ጠላቶቻችንን አንገት የሚያስደፋ ሆኗል፡፡

በአንድ አገር ውስጥ ሁለት የታጠቀ ኃይል መኖር የለበትም በሚለው ፤ ከሀገር ሉዓላዊነት ጋር የተያያዘውን መርህ አምኖ፣ ከቀደመ ስህተቱ ተምሮ፣ ሕወሓት ትጥቅ ሊፈታ መስማማቱ ያስመሰግነዋል፡፡ እውነተኛ ሰላም ፈላጊ መሆን ማለት እንዲህ ነው!፡፡

አሁን ከፌዴራሉ መንግሥትም ሆነ ከሕወሓት የሚጠበቀው በደረሱበት የሰላም ስምምነት መሰረት ለስምምነቱ ፍጹም ተገዥ የመሆናቸው እውነታ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሀገሪቱ ታሪክ ወስጥ ስፍራ የሚያስገኝላቸው ሲሆን የአዲስ ታሪክ ጀማሪ በመሆንም እንዲዘከሩ እድል የሚሰጣቸው ነው።

ሀገርን ወደ እንደ ሀገር አስተማማኝ ወደ ሆነ ሰላም ከመውሰድ ባለፈ ፤ ለጀመርነው ልማት አቅም በመፍጠር ብልጽግና እውን እንዲሆን የሚያስችል እድል መፍጠር ይችላሉ። ኢትዮጵያን የብልጽግና ከፍታ ላይ ይሰቅላሉ፡፡ በጀመረቻቸው ትልልቅ ፕሮጀክቶች፣ አጀንዳዎች እና የከፍታ ጉዞዎች ታሪካዊ አሻራ ያስቀምጣሉ፡፡ ተፈፃሚ ሳያደርጉት ቢቀሩ ግን የታሪክ ተወቃሽ ይሆናሉ፡፡

የፌዴራሉ መንግሥት ሆነ ሕወሓት ቀደም ሲል የተስማሙባቸውን ጉዳዮች ተፈጻሚ ማድረግ ፤ በራሱ አልጋ በአልጋ ነው ተብሎ አይገመትም ፤ ጦርነቱ በሀገርና በሕዝብ ላይ ያስከተለው ሁለንተናዊ ጥፋት መረዳት የማይችሉ፤ ጦርነት ለችግሮች አልፋና ኦሜጋ ነው ብለው የሚያምኑ፤ ከዛም በላይ ከጦርነቱ አትራፊ የሆኑ ሃይሎች ለተፈጻሚነቱ ተግዳሮት መሆናቸው አይቀርም። ይህንን ተግዳሮት ሰብሮ/አሸንፎ ለመውጣት ቆራጥነት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ቆራጥነት የሚመነጨው ደግሞ የሰላም ድምጾችን ብቻ በመስማት ነው፡፡

ባለፈው ሰኞ ምሽት በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የተላለፈ ዜና ላይ አንዳንድ በውጭ አገራት የሚኖሩ የትግራይ ተወላጅ የዲያስፖራ አባላት ሰላምን የማይደግፍ ነገር ሲያስተላልፉ እንደነበር ለማየት ችያለሁ፡፡ በእነዚሁ የትግራይ ተወላጅ ዲያስፖራ የማህበራዊ ገጾችም ልክ ያልሆኑ ነገሮችን ስናይ ቆይተናል ፤ ዛሬም እያየን ነው፡፡

እነዚህ ወገኖቻችን እየሄዱበት ያለው የተሳሳተ የጥፋት መንገድ ከጦርነት የሚገኝ ትሩፋት ይኖራል ብሎ ከማመን ፤ የጦርነቱን ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ካለመረዳት የመነጨ ሳይሆን፤ ከጦርነቱ ሩቅ በሆኑ ሀገሮች ከመኖራቸው ጋር በተያያዘ የተፈጠረ ደንታ ቢስነት እንደሆነ ለማሰብ አይከብድም።

ሕወሓት ለእነዚህ ሃይሎች ሃላፊነት ለጎደለው ጮኸት ጆሮውን ሊሰጥ አይገባም። በጦርነቱ ግንባር ገፈት ቀማሽ ለሆነው የትግራይ ሕዝብ ሰላም ሲል የገባውን ቃል እና የተፈራረመውን ስምምነት ተፈጻሚ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በሕዝቡ ውስጥ የተፈጠረውን ስሜት በአግባቡ ሊያጤነው ይገባል።

ዶ ቸ ቬለ (DW) ሕዝቡ የሰላም ድርድር በመጀመሩ የተሰማውን ደስታ አስመልክቶ የሰራው ዘገባም የሕዝቡን ስሜት ምን እንደሚመስል አንዱ ማሳያ እንደሆነ ለመገንዘብ የሚከብድ አይደለም።

በተመሳሳይ የፌዴራሉ መንግሥትም የገባውን ቃል እና የተፈራረመውን ስምምነት ተፈፃሚ እንዲያደርግ ቆራጥነት ሊኖረው ይገባል፡፡ 120 ሚሊዮን ሕዝብ አንድ አይነት ድምጽ ይኖረዋል ተብሎ አይጠበቅም፤ መንግሥት ለአገር ይጠቅማል ብሎ ያሰበውን ነገር ያደርጋል፡፡ ሰላም ማስፈን የአንድ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባር ነውና የሰላም አማራጭ የማይፈልጉ ኃይሎች ካሉ ቁርጣቸውን ሊነገራቸው ይገባል፡፡

በፌዴራሉ መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ድርድር እና የተደረሰበት ስምምነት የምርም የኢትዮጵያን አሸናፊነት ያሳየ ነው፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን ማስፈን ፤ የሀገር ሉዓላዊነትን ማስከበር ያስቻለ ነው ። ኢትዮጵያ አሸንፋለች የሚባለውም ለዚህ ነው።

ከዚህም ባለፈ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ሕብረት መሥራችና መቀመጫ መሆኗ ፤ የአፍሪካ ሕብረት ደግሞ ‹‹ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ›› የሚል መሪ ሃሳብ ይዞ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ ስምምነቱ የሕብረቱን መሪ ሃሳብ ተግባራዊ በማድረግ አዲስ አህጉራዊ እውነታ መፍጠር ያስቻለ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የራሷን ችግር በራሷ መፍታት እንደምትችል በተጨባጭ ለዓለም ማሳየት የቻለ ፤ ያለማንም ጣልቃ ገብነትና ወሳኝነት ጦርነት አያስፈልገንም ብለው ሕገመንግሥታዊና ሉዓላዊነትን መሰረት ባደረገ መርህ መስማማት መቻላቸው፡ ፡ ኢትዮጵያ የራሷን ችግሮች በራሷ ትፈታለች ብሎ በሙሉ አፍ መናገር ያስቻለ አዲስ ክስተት ነው፡፡

ከዚህ በፊት በሰላም አስከባሪነት የምትታወቀው ኢትዮጵያ ‹‹ምነው ምን ነካት!›› ሲሉ የነበሩ የአፍሪካ አገራት ሁሉ ‹‹ዋው! ኢትዮጵያ እውነትም ትልቅ አገር ናት›› እንዲሉ አስቻሏል፡ ፡ በቀጣይ ሁለቱ አካላት ስምምነታቸውን አክብረው ተግባራዊ ካደረጉ የትልቅ አገር ታሪካዊ ተወዳሽ ይሆናሉ፡፡

አዎ! የምንመኘው ይህንኑ ነው፡፡ ከተፋላሚ ኃይልነት ወደ ተደጋጋፊ ኃይልነት መምጣት፣ በሁሉም መስክ የተጀመረውን የከፍታ ጉዞ አብሮ ማስቀጠል፣ ለዓለም የሚበቃውን የኢትዮጵያ እምቅ ሀብት በጋራ እና በፍቅር መጠቀም፣ ከአውዳሚነት ወደ አልሚነት መሸጋገር፣ ለጦርነት የሚሰማሩ ወጣቶችን ለልማት ማሰማራት፡፡

ለምሽግ ይውል የነበረውን ቦታ ለስንዴ እና ለመናፈሻ ማዋል፣ ለጥይት መግዣ ይውል የነበረውን ገንዘብ ለማዳበሪያ መግዣ ማድረግ፣ ይዘራረፍ የነበረ ተፋላሚ እንድጎራረስ ማድረግ፣ ታንክ የሄደባቸውን ሜዳዎች ትራክተርና ኮምባይነር እንድሄድባቸው ማድረግ... ይህ ነው የአንድ አገር ወዳድ መንግሥት ወይም ድርጅት መገለጫ፡፡

ከዚህ ውጪ ሀገርን ዳግም ወደ ጦርነት ለመውሰድ የሚደረግ የጥኛውም የእምቢተኝነት ተግባር ለሀገርና ለሕዝብ ተቆርቋሪ ነኝ የሚል አካል መገለጫ ሊሆን አይችልም ፤በየትበኛውም መመዘኛ ። በሕዝብ ዘንድ የሚጠላ እና ሲወቀስ የሚኖር ነው፡፡ በጎረቤት አገራትም ሆነ በውጭ አገራት ኢትዮጵያ የነበራትን ገናና ስም እና ሰላም አፍቃሪነት የሚያጎድፍ ነው።

ለምትወዷት አገራችሁ፣ ለምትመሩት ሕዝባችሁ ትክክለኛው መስመር አሁን የያዛችሁት ነው፡፡ የሰላምና እርቅ መንገድ። ፍቅር ካለ፣ መተሳሰብና ቅንነት ካለ የኢትዮጵያ ሀብት ለማንም እንደሚበቃ የአደባባይ ሀቅ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ የሰላም ድርድሩ ብሥራት በተሰማበት ማግስት በአርባ ምንጭ የተናገሩትም ይህንኑ ነበር፤ በሰላም የተገኘውን ድል በልማት ማስቀጠል፡፡ ያኔ ኢትዮጵያ ለሁላችንም ምቹ ትሆናለች፡፡

ለመሆኑ ልብ ብለን አስተውለነው እናውቃለን? እስኪ የብዙ ችግሮቻችንን ምክንያቶች ልብ እንበል! አብሮ ባለመሥራትና በመገፋፋት የተከሰቱ ናቸው፡፡ ፍቅር፣ አንድነትና ሰላም ቢኖር እነዚህ የሚታዩ ችግሮቻችን ሁሉ አይኖሩም፡፡

ለስምምነቱ ተፈጻሚነት ከፌዴራሉ መንግሥት እና ከሕወሓት አመራሮች ብቻ ሳይሆን ከእኛ ከተራ ዜጎችም ብዙ የሚጠበቅ ነገር አለ፡፡ ይሄውም የጀመሩትን የሰላም መንገድ ማጠናከርና ከጎናቸው መቆም፡፡ በጦርነቱ ወቅት ‹‹ሕዝብ ነው የሚጎዳ›› ስንል ቆይተናል፡፡ ስለዚህ አሁን ለሕዝብ ተብሎ የሰላም መንገድ ሲጀመር አመስጋኝና አበረታች መሆን አለብን፡፡

የትናንት ነገር ትናንት አልፏል፡፡ ዛሬ ሌላ ነው፤ ዛሬ የሚሰራው ለነገ ነው፡፡ አንድን ነገር እንደ አዲስ ስንጀምር ካለፈው ስህተት በመማር እንጂ ያለፈው ላይ ችክ ማለት ግትርነት ነው፡፡ ኢትዮጵያም ሆነች ሌላው ዓለም በየሥርዓቱ አንዳንድ መጥፎ ክስተቶች ያጋጥሟቸዋል፡፡ የሚያስመሰግናቸው ችግሩን የፈቱበት መንገድ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ዓውድ ብቻ እንኳን ካየነው፤ በዘመነ ኢህአዴግም፣ በደርግም፣ በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴም.... በየሥርዓቱ ችግሮች ነበሩ፡፡ ከአንዱ ሥርዓት ወደ አንዱ ሥርዓት ለውጥ የሚደረገው በኃይል ነበር፡፡ ከኢህአዴግ ወደ ብልጽግና የተደረገው የሥርዓት ለውጥ ግን ያለምንም ጦርነት በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ የዴሞክራሲ ጅማሮ ነበር፤ በመሃል የተፈጠረው ተፈጠረ፡፡

አሁን ወደ ሰላም እየተጓዝን ነው። እየሄድንበት ያለው የሰላም መንገድ በአገራችን ታሪክ አዲስ የዴሞክራሲ ምዕራፍ የሚከፍት ነው፡፡ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ ይጠፋፉሉ ሲባል ሁለት ተፋላሚ ኃይሎች አንድ ሆነው አገራቸውን ወደ ከፍታ ሲወስዱ ማየት የማንንም ቀልብ የሚስብ ነው፡፡

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ያሳለፈ ችግር

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

እሷ ከትውልድ አገሯ ርቃ ወደ ከተማ ስትዘልቅ መልካም ኑሮን ከጥሩ እንጀራ አስባ ነበር፡፡ በርከት ያሉ የአገሯ ልጆች ከቀያቸው ርቀው ስኬታማ ሆነዋል፡፡ ገንዘብ አግኝተው ጥሪት ይዘው ከብረዋል፡፡ ያሻቸውን መንዝረው፣ የፈለጉትን ገዝተው ሸጠዋል፡፡

ከእነሱ መሀል አብዛኞቹ ወደ መንደር ሲመለሱ ዓይን ያርፍባቸዋል፡፡ ተከታያቸው ይበዛል፡፡ አድናቂ አክባሪያቸው ያይላል፡፡ በእነሱ አነጋገርና አለባበስ ተገራሚው ብዙ ነው፡፡ እነሱ ከተማ ኖረው ከተሜ ሆነዋል፡፡ ገጠሩን ርቀው፣ አምረው፣ ዘምነዋል፡፡ ሁሌም ይህን ያዩ የገጠር ልጆች በከተሜዎቹ ዘመንኞች ይማረካሉ፡፡ ምኞታቸው እነሱን መሆን ነው፡፡ ሃሳባቸው ዘመነኞቹ በሄዱበት መንገድ መቀጠል ነው፡፡

ዘለቃሽ ተሰማ ከቀናት በአንዱ የጉራጌ ምድር ጉንችሬን ርቃ መሀል አዲስ አበባ ገባች ፡፡ ከተማውን ባየች ጊዜ ከልብ ወደደችው፡፡ እውነትም ያገሯ ልጆች ከቀየው ቢወጡ፣ ቢርቁ እንደማይፈረድ ገባት፡፡ ከተማው ከአገሯ ይበልጥ ያምራል፡፡ በዚህ ስፍራ ሁሉ የደመቀ የተዋበ ነው፡፡

ከዚህ የሚታይ ውበት ባሻገር ሰርቶ ስለመለወጥ አሰበች፡፡ አዎ! ከበረታች፣ ከጣረች እንደሌሎች የማትሆንበት አልታያት አለ፡፡ በእርግጥ የከተማ ሕይወት እንደገጠር አይደለም፡፡ እሸቱ ከጓሮ፣ ወተቱ ከጓዳ እንዳሻው አይገኝም ፡፡

ዘለቃሽ እግሮቿ ከከተማ መሀል ሲገኙ የኑሮውን ልዩነት አውቃለች፡፡ አሁን ራሷን ለማሸነፍ የመጀመሪያ ምርጫዋ ሰርቶ ማደር ብቻ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ላቧን ጠፍ አድርጋ ፣ በጉልበቷ ማደር አለባት ፡፡ አዲስ አበባ እህቷን ጨምሮ የቅርብ ዘመዶች አሏት፡፡ ሁሉም ለፍተው ያድራሉ፡፡ የከተሜ እንግድነቱን ማርዘም አላሻትም፡፡ መተዳደሪያ ካለችው ሥራ ተቀጥራ መስራት ያዘች፡፡

### ከሆቴሉ ኩሽና ...

ዘለቃሽና አዲስ አበባ ከተገናኙ ጊዜያት ተቆጥረዋል፡፡ ከአንድ ሆቴል ተቀጥራ የወጥቤት ሙያን ይዛለች፡፡ ስራው እረፍት ይሉት የለውም፡፡ በየቀኑ ለሚመጡ ደንበኞች በሰአት ምግብ ማድረስን ይጠይቃል፡፡ የእጅ ሙያዋን ያዩ አሰሪዎቿ ዘለቃሽን ወደዋታል፡፡ እሷ ጉልበት ሙያዋን አትሰስትም ፡፡ የታዘዘችውን አጣፍጣ ታዘጋጀለች ፡፡ ከጠዋት እስከ ማታ ከኩሽና የማትወጣው ሰራተኛ ሲመሽ ድካም ይጥላታል፡፡ ጥቂት ጎኗን አሳርፋ ለነገው ስራ ትዘጋጃለች፡፡

በየቀኑ ዘለቃሽና አድካሚው ስራ ይገናኛሉ፡፡ ሁሌም ከሽንኩርቱ ፣ ከበርበሬው፣ ከእሳት ከውሃው ስትል ትውላለች፡፡ የእጇን ሙያ የወጧን ጣዕም የለመዱ ደንበኞች ሆቴሉን አዘውትረዋል፡፡ አሰሪዎቿ ሙያዋን አይተው፣ ጉልበቷን ተጠቅመው ገበያቸውን አድርተዋል፡፡ ዘለቃሽ ባተሌነቷ ቀጥሏል፡፡ ቀን ስትሰራ ውላ ማታ ዕንቅልፍ ይጥላታል፡፡ ድካም ያሸንፋታል፡፡

ዘለቃሽ ሌት ነግቶ ወፍ ሲንጫጫ ከምዳጃዋ ቀጠሮ አላት፡፡ በዚህ ሰአት የእሷን እጅ የሚሹ ደንበኞች ቁርስ ይጠብቃሉ ፡፡ ይህን አዋቂዋ ሴት የጠዋት ግዴታዋን አጠናቃ ለምሳው ዝግጅት ትፈጥናለች፡፡ ከሰዓታት በኋላ የሆቴሉ ደንበኞች ምግብ ይሻሉ፡፡ ፍላጎታቸው ሞልቶ የሃሳባቸው እንዲደርሰ አሁንም የዘለቃሽ እጆች ይናፈቃሉ፡፡

ዘለቃሽ ለእሷ ተብሎ የተዘጋጀ የመኝታ ክፍል የላትም፡፡ ሁሉም በስራ ውሎ ወደቤቱ ሲገባ ከምድጃዋ ስር ፍራሽ አንጥፋ አረፍ ትላለች፡፡ ሁሌም ውሎ አዳሯ ኩሽናው መሆኑ አስከፍቷት አያውቅም፡፡ እሷ የዛሬ ጉዳቷ ለነገ ተስፋ መሆኑን ታውቃለች፡፡ የአሁኑ ልፋቷ ቆይቶ እንደሚከፍላት ሲገባት ድካሟን ትረሳለች፡፡ ይህን እያሰበች ዓይኖቿ በዕንቅልፍ ይከደናሉ፡፡ አካሏ በድካም ዝሎ ማንኮራፋት ፣ መቃዠት ትጀምራለች፡፡

### አንድ ቀን ምሽት

ዘለቃሽ በዚህ ቀን እንደተለመደው በድካም ስትባዝን ውላለች፡፡ ከጠዋት አስከማታ ለደንበኞች ወጥ ስትሰራ ፣ ምግብ ስታዘጋጅ ፣ የታዘዘችውን ስትከውን አምሽታለች ፡፡ የዛሬው ድካሟ ከወትሮው ቢለይ ጎኗን ልታሳርፍ ከኩሽናው ፍራሽ አረፍ ፣ ጋደም ብላለች ፡፡ አንዳንዴ ድካም ሲጠናባት የወደቀችበትን ትረሳለች፡፡ እንዲህ በሆነች ጊዜ ያለችበትን ሳታውቅ ሌቱ ይነጋል፡፡ ወፍ ይንጫጫል፡፡

### ዕንቅልፍ እንደ ሞት

ዘለቃሽና ዕንቅልፍ ከተገናኙ ቆይተዋል፡፡ ባተሌዋን ሴት የድካም ፈረስ ሸምጥ እየጋለበ ከተለመደው ቅዠትና ኩርፊያ አድርሷታል፡፡ ሌቱ ጭር ብሏል፡፡ አሁን የኩሽናው ግርግር አይሰማም፡፡ በዚህ ቦታ እንደቀኑ የሚነድ እሳት የሚዘጋጅ ወጥና እንጀራ የለም፡፡ ዝም ፣ ጭጭ እንዳለ ሌቱ ገስግሷል፡፡ ዘለቃሽ እንደወትሮዋ ትወራጫለች፣ ትቃዣለች፡፡

ከአንድ ጥግ ሆነው ሁኔታዋን የሚያስተውሉ ፈጣን ዓይኖች በድርጊቷ ተስበዋል፤ ይህች ሴት ፈጽሞ የምታይ፣ የምትሰማ ፣ አይደለችም፡፡ ድካም አቅሏን አስቶ ራሷን አስጥሏታል፡፡ አሁን ንቁዎቹ ዓይኖች ይበልጥ ፈጠዋል፡፡ የዚህች ሴት ሁኔታ ለሌላ እርምጃ የሚጋብዝ መሆኑ የገባው ጎልማሳው አስተዋይ ቀስ እያለ ወደውስጥ ዘለቋል፡፡

ሰውየው እርምጃውን አጥፍቶ፣ ትንፋሹን ውጦ አጠገቧ አስኪደርስ ማንም እንዳለየው አረጋግጧል፡፡ በዚህ ሰአት፣ በዚህ ስፍራ ሁሌም ከእሷና እሷ በቀር በኩሽናው ማንም አይገኝም፡፡ እሷም ብትሆን አሁን እንዳለች አይቆጠርም፡፡ ዕንቅለፍ አሸንፎ ረቷታል፡፡ ድካም አንገዳግዶ ጥሏታል፡፡ ይህን ያስተዋለው የሌሊቱ አድፋጭ በፈጣን ርምጃ ከጎኗ ደርሶ ልብሷን መገፈፍ ፣ አፏን ማፈን ጀምሯል፡፡ ሰውዬው ያቀደውን ፈጽሞ እስኪጨርስ ዘለቃሽ በከባድ ዕንቅልፍና በጠንካራ እጆች ስር ውላለች፡፡

ዘለቃሽ በውድቅት ለሊት ካለችበት ደርሶ የደፈራትን ሰው ለይታዋለች፡፡ በሆቴሉ ካሸር ሆኖ የሚሰራ የአሰሪዎቿ የቅርብ ዘመድ ነው፡፡ ይህን ብታውቅም እሱን መክሰስና መውቀስ አልቻለችም፡፡ ሀፍረትና ድንጋጤ ውስጧን ሰቅዞ ያዛት፣ ድርጊቱ ተስፋ አስቆርጦ አንገት አስደፋት፡፡

ባተሌዋ ሴት ከሆነባት ድርጊት በኋላ ቤቱን መልቀቅ ፣ እንጀራዋን መተው አልሆነላትም፡፡ ይህን ልሞክረው ብትል ጦሟን ታድራለች ፣ ማረፊያ መጠጊያ ታጣለች፡፡ ሰርቶ ከማደር ሌላ ምርጫ የሌላት ሴት በወጥ ቤት ስራዋ ገፋች፡፡ አሁንም ስለእሷ ኩሽና ማደር ደንታ የሰጠው የለም፡፡

ቀን በድካም የምትባዝነው ሴት ሌቱን እንደቀድሞው የሰላም ዕንቅልፍ አትተኛም፡፡ «ኮሽ» ባለ ቁጥር እየባነነች፣ ኮቴ ስትሰማ እየደነገጠች ከማለዳው ትደርሳለች፡፡ ውሎዋ ከወትሮው አይለይም፡፡ ከእሳት ከድስቱ ተጥዳ ለሌሎች ሆድ ትሮጣለች ፤ ለብዘዎች ፍላጎት ትደከማለች፡፡ ምሽት ድካምና ስጋት አይርቋትም፡፡ ሚስጥሯን ቋጥራ፣ ህመሟን ውጣ ስለ ነገ ታልማለች ፣ ለዚህ ሃሳብ አትሰንፍም ፣ ተስፋ አትቆርጥም ፡፡

### ከጊዚያት በኋላ

የዘለቃሽ ብርታት ዛሬም ከእሷ ጋር ነው፡፡ የዕለት ግዴታዋ አልተቋረጠም፡፡ ትዕዛዝ አክብራ ስራዋን ትከውናለች፡፡ ጉልበቷን ትገብራለች፡፡ ከሰሞኑ የሚሰማት ድካም ግን ከወትሮው የተለየ ሆኗል፡፡ የምትሰራው ምግብ ሽታ ይረብሻት ይዟል፡፡ የምትቀምሰው ከሆዷ አልረጋ እያለ አስጨንቋታል፡፡ የሆነችውን ባታውቅም ስለእሷ የጠረጠሩ ሁኔታውን ገምተዋል፡፡

ዘለቃሽ አሁን ማርገዟን አውቃለች፡፡ ይህ እውነት ገሀድ ከሆነ ጀምሮ የአሰሪዎቿ ዘመድ ቤቱን ትቶ ጠፍቷል፤ የልጅ አባት መሆን ያልፈለገው ገንዘብ ያዥ ስሙን ጠብቆ፣ ድርጊቱን ለመሸሸ መወሰኑ እሷን አስደንግጧል፡፡ ጉዳዩን የሰሙ ባለሆቴሎች የዘመዳቸውን ሃጢያት ማባባስ አልፈለጉም፡፡ ሁኔታውን እንደተለመደ ድርጊት ቆጥረው ችላ ብለውታል፡፡

ስራና መኖሪያን ያልተነፈገችው ዘለቃሽ የዕለት ስራዋን ቀጥላለች፡፡ ማርገዟን ካወቀች ወዲህ ህክምና የሄደችው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ አሰሪዎቿ ጉልበትና ሙያዋን ማጣት አልፈለጉም፡፡ እሷም እንደቀድሞው ከእሳት ከምድጃው ውላ የታዘዘችውን ትሰራለች ፡፡

ቀኑ መግፋት ይዟል፡፡ የዘለቃሽ እርግዝናም እንዲሁ፡፡ በድካም ስትናውዝ የምትውለው ሰራተኛ ግዴታዋን አጠናቃ ሲመሽ ከኩሽናዋ ታርፋለች፡፡ ማንም ስለእሷ መወደቅ መነሳት ደንታ የለውም፡፡ ማንም ስለእሷ ጤና አይጨነቅም፡፡ ውሎአድሮ ዘለቃሽ ድካሙን መቋቋም ተሳናት፡፡ ጎንበስ ቀና ማለቱ ደከማት፡፡ እናም ወሰነች ፡፡ ቤቱን ትታ፣ ስራውን ለቃ ልትወጣ ቆረጠች፡፡

ዘለቃሽ ጓዟን ሸክፋ ከሆቴሉ ስትርቅ እግሯ ያመራው ወደ እህቷ ቤት ሆነ፡፡ እህቷ ካገሯ ስትመጣ ተቀብላታለች ፡፡ ሰርታ እንድታድር ራሷን እንድትችል አግዛታለች፡፡ አሁን ግን ከራሷ አልፋ ሌላ ፍጥረት ይዛባት እየመጣች ነው፡፡ እህት እንዲህ መሆኑን ባትፈቅድም ፊት አልነሳቻትም «ይሁን» ብላ ተቀበለቻት፡፡

ዘለቃሽ በእህቷ ቤት አንድ ቀን እንዳደረች ሆስፒታል ልትሄድ ተነሳች፡፡ ያለፋትን ወራት በሀኪም እጅ ሳትታይ ቆይታለች፡፡ በሆስፒታሉ ደርሳ ህክምናዋን እንደጀመረች ወደቤት እንዳትመለስ ተነገራት፡፡ አጋጣሚ ሆኖ ልጇ ሊወለድ ተቃርቧል፡፡ በድንገት የመጣችው ዘለቃሽ ድንገቴ ምጥ አፋፋማት፡፡ ከቆይታ በኋላ ዘለቃሽ ሴት ልጇን ታቀፈች፡፡ ዓይኗን በዓይኗ አየች፡፡

አራስዋን ተቀብላ በቤቷ አቅም እንደወጉ ያደረገችው የዘለቃሽ እህት ያላትን አቃምሳ ፣ የቻለችውን ሞክራ ጥቂት ቀናት አገዘቻት፡፡ ቆይቶ ግን ዘለቃሽ በእህቷ ቤት መኖሩ ከበዳት ፡፡ በዚህ መቀጠሉ ለእሷም ለልጇም የሚመች አልሆነም፡፡ ጊዜ ወስዳ ደጋግማ አሰበች፣ ከራሷ መክራ ለውሳኔ ደረሰች፡፡

### ጉዞ ወደ ገጠር

ዘለቃሽ ከዓመታት በፊት በእንጀራ ፍለጋ ሰበብ የለቀቀችውን መንደር ዳግም ተመለሰችበት፡፡ እግሯ ወደትውልድ ቀዬዋ ሲያመራ ቀድሞ ታስበው የነበረው የመሻሻል ሕይወት በዓይነ ህሊናዋ ተመላለሰ ፡፡ አሁን የትናንቱ ህልም ቅዠት ሆኗል፡፡

እሷ ቀድሞ እንደምታውቃቸው ብርቱዎች አልሆነችም፡፡ እንደሌሎች ተለውጣ አምራ ደምቃ አልመጣችም፡፡ ፈጽሞ ከተሜ አትመስልም፣ ልብሷ አያምርም፣ ገንዘብና ጌጥ የላትም፡፡ ትናንት እሷን ብቻ ለሚያውቃት መንደር አንድ ሕይወት ጨምራ ፣ ልጅ በጀርባዋ አዝላ ታይታለች፡፡ አሻግረው ያዩዋት ሁሉ ርቆ እንደኖረ እንግዳ ሮጠው አልተቀበሏትም ፡፡ ከእሷ ያለው ተራ ጓዝና ጉስቁልና፣ ከአንዲት ጨቅላ ጋር ብቻ ነው፡፡

ዘለቃሽ ወደ እናቷ ቤት አልፋ ገባች፡፡ እናት ፊት አልነሷትም፡፡ ጓዟን ከነልጇ ተቀብለው ቤት «ለእንቦሳ» ሲሉ በፈገግታ ተቀበሏት፡፡ ኑሮና ችግር በእጅጉ ያጎሳቆላት ሴት መልሳ ከገጠር ሕይወት ተፋጠጠች፡፡ ልጇን በጀርባዋ አዝላ፣ ከእርሻ ከገበያው ዋለች፡፡ አሁንም ዘለቃሽ ኑሮ አልተመቻትም፡፡ ደስታ ራቃት፣ በየቀኑ ይከፋት፣ ሆድ ይብሳት ያዘ፡፡

ሶስት ዓመታትን የዘለቀው የገጠር ሕይወት በሚቆረቁር ኑሮ ታጅቦ እንደዋዛ ነጎደ፡፡ ምኞት ይሉትን እውነት ለአፍታ ያላየችው ዘለቃሽ ልቧ መልሶ ሩቅ መንገድ አሰበ፡፡ ከተማ ብትመለስ እንደሚበጅ ገምታ ጓዟን ሸካከፈች፡፡ ልጇን አዝላ አዲስ አበባ ስትገባ መገኛዋ ትታው የሄደችው የእህቷ ቤት ሆነ፡፡

ዘለቃሽ ከሶስት ዓመታት በኋላ ልጇን ይዛ የእህቷ እንግዳ ሆነች፡፡ አስራአምስት ቀናትን እንደቆየች ግን ሕይወት በእህት ቤት አልመች አላት፡፡ ከሞሰብ የማይቆርሱበት፣ ከድስት የማይጨልፉበት ቤት ሆኖ አሳቀቃት፡፡ እሷ ብትችልም ልጇ ለዚህ ይሉኝታ አልደረሰችም፡፡ ያየችውን አምጡ ትላለች፡፡ ሲከለክሏት ታለቅሳለች ፣ ትጮሃለች ፡፡

ይህ አጋጣሚ ዘለቃሽን አስመረራት፡፡ በድንገት ከእህቷ ቤት ወጥታ ልመና ጀመረች፡፡ ጥቂት ቆይታ ደግሞ በየቤቱ ልብስ ማጠብ ፣ መላላክ ያዘች፡፡ እንዲህ ማድረጓ ለእሷና ለልጇ ዳቦ መግዣ አላሳጣትም፡፡ የምታገኘው ገንዘብ ለወለል አዳር ተረፋት፡፡

ሲመሽ ከፍላ እያደረች ከመሳቀቅ «እፎይ» አለች፡፡ ለእህቷ ተከራይታ እንደምትኖር ተናገራለች፡፡ ጥቂት ቆይታ ደግሞ አሻሮ መቁላት ጀመረች፡፡ ገቢዋ ከቀድሞው የተሻለ ሆነ፡፡ የሚከፈላትን ይዛ የሚከራይ ቤት ፈላለገች፡፡ የአቅሟን አላጣችም፡፡ ከአንዲት ሴት ቤት መኖር ጀመረች፡፡

### ኑሮ በቤት

አሁን ዘለቃሽ ከዓመታት እንክርት በኋላ የራሴ ከምትላት ጎጆ ማደር ጀምራለች፡፡ ማለዳ ወጥታ ሲመሽ የምትመለስባት ትንሽዬ ቤት እግር አታዘረጋም፡፡ ብትጠባትም አልተከፋችም፡፡ በምስጋና ተኝታ ታድርባታለች፡፡ አሁን ላይ የሚያሳስባት ቢኖር የልጇ ባህርይ ነው፡፡ ያለ አንዳች ምክንያት ስታለቅስ ትውላለች፡፡ ውላ ስትገባም ለሊቱን ሙሉ ስታለቅስ ታድራለች፡፡

ይህ ጩኸትና ለቅሶ ለአከራይዋ አልተመቻቸም፡፡ ድምጽ በሰማች ቁጥር ትበሳጫለች፡፡ ዘለቃሽን እየጠራች፣ እየተቆጣች ታስጠነቅቃለች፡፡ የህጻኗ ችግር አልታወቀም፡፡ ጩኸቷ ፣ ለቅሶዋ ቀጥሏል፡፡ አንድቀን የዘለቃሽ አከራይ ትዕግስት ተሟጠጠ፡፡ በድንገት በሯን በርግዳ ገባች ፡፡ የዛሬው ሁኔታዋ ከወትሮው ይለያል፡፡ በእጇ ቢላዋ ይዛለች፡፡ ዓይኗ ፈጧል፣ ፊቷ ተለውጧል፡፡ ሴትዮዋ ሺሻ ከምታጨስበት ፍራሽ ተነስታ መምጣቷ ነው፡፡ ሁኔታዋን ያየችው ዘለቃሽ ቤቷን ለቃ ለመውጣት ፈጠነች፡፡

ዘለቃሽ ልጇን ለማሳደግ በሌሎች አማራጮች ሮጠች፡፡ አሁን ለእኔ የምትለው ማረፊያ የላትም፡፡ በድንገት የለቀቀችው ዳግም ቤት ለልመና ዳርጓታል፤ አጋጣሚ ሆነና ችግሯን ያዩ ልበ ቅኖች ከኩሽናቸው እንድታድር ፈቀዱላት፡፡ ትንሽዋን ልጅ ይዛ የጎን ማረፊያዋን ብታገኝ ስጦታውን በምስጋና ተቀበለች፡፡ ከማዕድቤቱ እያደረች የቀን ስራዋን ቀጠለች፡፡

አሁን ልጇ ነፍስ ማወቅ ጀምራለች፡፡ አራት ዓመት ሲሞላት ትምህርትቤት ገብታለች፡፡ ከትምህርት ውላ ስትመለስ ዘለቃሽ ተስፋዋ ለመለመ፡፡ ያለአባት የምታሳድጋት ልጅ ለቁምነገር መብቃቷ ስለነገ እንድታስብ ምክንያት ሆነ ፡፡ ቆይቶ ግን ልጇ የሚጥል በሽታ እንዳለባት አወቀች፡፡ ይህ እውነት እናትን በእጅጉ አሳዘናት አንድ ልጇን ያየባት ህመም በእሷ አቅም የሚድን አለመሆኑ አሳሰባት፡፡

አስር ዓመታትን የዘለቀችበት የኩሽና ሕይወት አደጋ ሊጋረጥበት ጊዜው ደረሰ፡፡ ትናንት በበጎነት ያስጠጓት ሰዎች ዛሬ ቦታውን እንደሚፈልጉት አሳወቋት፡፡ ዘለቃሽ ልጇን ይዛ ማደሪያዋን ከመልቀቅ ውጭ ምርጫ አጣች፡፡ ታዳጊ ልጇ በትምህርቷ የደረጃ ተማሪ ሆናለች፡፡ አልፎ አልፎ የሚጥላት ህመም ከእሷ ቢሆንም ስንፍናን አታውቅም፡፡

### የእናትና ልጅ እንክርት

አሁንም ዘለቃሽና ልጇ መኖሪያ ፍለጋ መንከራተት ይዘዋል፡፡ «አለናችሁ» የሚል ዘመድ በሌለበት «ግቡ» የሚል ወዳጅ ማግኘት ይከብዳል፡፡ አጋጣሚው ግን ብዙ አልዘለቀም ፡፡ አንድ ልበ ቀና ኩሽናቸውን ለመኖሪያ ፈቀዱላቸው፡፡ ዛሬ የዘለቃሽ ልጅ የአስራ አራት ዓመትና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡

ልጅቷ ከነገ ለመድረስ ብትሮጥም ለህመሟ መፍትሄ አልተገኘም፡፡ ዘለቃሽም ብትሆን አብሯት በኖረው የኪንታሮት ህመም እየተሰቃየች ነው፡፡ በዓይኗ ላይ የደረሰው ጉዳት ጭምር ለዛሬ ችግር ሆኗል፡፡ የኑሮ ውድነት በየስፍራው የሚያሮጣት ብርቱ ሴት በተደጋጋሚ ቤት ለማግኘት ያደረገችው ሙከራ አልተሳካም፡፡

ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት «መምጫዋ የማይታወቅ» በሚል ሰበብ ቤት እንዳታገኝ ፣ በሴፍቲኔት እንዳትታቀፍ ደጅ ያስጠኗታል ፡፡ ለብዙዎች የሚደርሰው የእርዳታ ፍጆታም ለእሷ የሰማይ ያህል እንደራቀ ዘልቋል፡፡ አሁን ዘለቃሽ በአካባቢዋ በተጀመረው የምገባ መርሀግብር በቀን አንዴ መጠቀም ችላለች፡፡

ሁሌም የሚሰጣትን ምግብ ቋጥራ ለልጇ ስታካፍል ዓይኖቿ ለምስጋና ወደ ላይ ያንጋጥጣሉ፡፡ ዛሬም ባላለፈው ችግር የምትዳክረው ዘለቃሽ የጠዋቷ ጀንበር ተስፋዋ ነች ፡፡ በእጇቿ ልፋትና በአንድ ልጇ ብርታት ስለ ነገ ብሩህነት ታስባለች ፡፡ ህይወትም ያለለውጥ በተለመደው መልኩ ቀጥላለች፡፡

# ስፖርት





## የባህርዳር ስቴድየም ሁለተኛ ዙር ግንባታን በአንድ ዓመት ለማጠናቀቅ ታስቧል

**ቦጋለ አበበ**

በኢትዮጵያ ትልልቅ ስቴድየሞችን መገንባት ከተጀመረ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ሐዋሳ፣ ባህርዳር፣ ነቀምት፣ ሐረር፣ አሶሳ፣ ሰመራ፣ ጋምቤላና ሌሎችም ከተሞች ትልልቅ ስቴድየሞች ግንባታቸው ከተጀመረ ዓመታት ቢቆጠሩም እስካሁን መጠናቀቅ አልቻሉም፡፡ የአብዛኞቹ ስቴድየሞች ግንባታም ኮንክሪት ከማቆም የዘለለ ዓለም አቀፍ ስቴድየሞች የሚጠይቁትን መስፈርት ማማላት ሳይችሉ በቁም ቀርተዋል፡፡ የሐዋሳና የባህርዳር ስቴድየሞች ከሌሎቹ በተሻለ ውስን መሰረተ ልማቶችን አማልተው ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ማስተናገድ ቢችሉም ግንባታቸው በተጀመረው ፍጥነት መጋዝ አልቻለም፡፡ እንዲያውም ከዓመታ በፊት የነበራቸው መሰረተ ልማት እየተዳከመ በመሄዱና ማሻሻያ ማድረግ ባለመቻሉ ያስተናግዱ ከነበረው ዓለም አቀፍ ጨዋታ ሊታገዱ በቅተዋል፡፡ የባህርዳር ስቴድየም ባለው የተሻለ ይዞታና መሰረተ ልማት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ ብቸኛው ዓለም አቀፍ ጨዋታ የሚካሄድበት ነበር፡፡ ይሁንእንጂ ይህ ስቴድየም በካፍና በፊፋ እንዲያሻሽል በተሰጠው ግብረመልስ መሰረት ስራዎችን ባለማከናወኑ ከዓመት በፊት ሊታገድ ችሏል፡፡ ይህም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን የሚያደርጋቸውን ዓለም አቀፍ ጨዋታዎች በሌሎች አገራት እንዲያካሂድ አስገድዶታል፡፡ በዚህም የስፖርት ቤተሰቡ የተጀመሩ ስቴድየሞች በተቻለ ፍጥነት እንዲጠናቀቁ ግፊት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ሆኖም እነዚህን በጅምር የቀሩ ስቴድየሞች ለማጠናቀቅ አብዛኞቹ ክልሎች እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አልተስተዋሉም፡፡

የባህርዳር ስታዲየም ሌሎች ክልሎች ካሉት በተለየ በክልሉ መንግሥት ተነሳሽነት የሁለተኛውን ዙር ቀሪ ሥራ ግንባታ ለማስጀመር ተወስኖ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ የዚህን ስቴድየም የሁለተኛ ዙር ቀሪ ግንባታ ማስጀመሪያ መርሃግብርም ከቀናት በፊት ተካሂዷል፡፡

የባህርዳር ስታዲየም ከጣራ ውጪ ያሉ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ እና የካፍን 16 መሠረታዊ መስፈርቶች ለማሟላት የግንባታ ሥራው በይፋ የተጀመረ ሲሆን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅም ታስቧል፡፡

ኅዳር 2002 ላይ በ780 ሚሊዮን ብር በጀት 52 ሺ ተመልካቾችን እንዲይዝ ታስቦ ወደ ግንባታ የገባው የባህርዳር ስታዲየም፣ ለግንባታው ማስጀመሪያ 389 ሚሊዮን ብር ተፈርሞ የነበር ሲሆን እስካሁንም 758 ሚሊዮን ብር ወጪ እንደተደረገበት ታውቋል፡፡

በ MH ኢንጀነሪንግ አማካሪነት እና በሚድሮክ ኮንስትራክሽን ለሚደረገው ግንባታ 1 ቢሊዮን 74 ሚሊዮን የተሰበሰበ ሲሆን ከጣራ ውጪ ያሉትን ሙሉ ሥራዎች የሚያጠቃልል እና በአንድ ዓመት የሚጠናቀቅ ይሆናል።

የኢፌዴሪ ባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ የባህርዳር ዓለም አቀፍ ስታዲየም ግንባታ ከሁሉ ስታዲየሞች በፊት ይጠናቀቃል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸው፣ በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ያላቸውን ፍላጎት በማሳየት ድምጻቸውን ለማሰማት ባህርዳር እንደተገኙ ተናግረዋል፡፡ ግንባታውን ለማጠናቀቅ የቻሉትን ሁሉ እንደሚያደርጉም ቃል ገብተዋል።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጀማል አህመድ በበኩላቸው፣ ብሔራዊ ቡድናችን በስታዲየም ዕጥረት ምክንያት ተሰዶ መጫወቱን ኮንነው ድርጅታቸው ስታዲየም ግንባታዎች በመሥራት እንደሚታወቅ በማስታወስ ለባህርዳር ስታዲየምም



**ሁለተኛውን የግንባታ ምዕራፍ ለማጠናቀቅ 1 ቢሊዮን 74 ሚሊዮን ብር እንደ ተሰበሰበ ታውቋል፤**

ከተበጀተው 740 ሚሊዮን ብር ላይ 300 ሚሊዮን ብር ጨምረው ግንባታውን እንደሚያሳልጡ አሳውቀዋል።

የክልሉ ርዕስ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ፣ ፕሮጀክቱ የሀገራችንን ስፖርት አንድ እርምጃ የሚያስኬድ መሆኑን ጠቁመው ግባቸው ግንባታውን ማስጀመር ሳይሆን ማጠናቀቅ እንደሆነ ገልጸዋል። ስታዲየሙን ብቻ ሳይሆን ከውጭ ያሉትን ታጥረው የተቀመጡ ቦታዎች አሻሽሎ በመሥራት ለወጣቶች ምቹ መዝናኛ ለማድረግ እንደሚሠሩም ተናግረዋል። ርዕሰ መስተዳድሩ በተለይም “ሀገራችን ውስጥ ግንባታ ይጀመራል እንጂ አይጨረስም” የሚሉ የሕዝብ አስተያየቶችን በማስተካከል ግንባታውን ለመጨረስ ያላቸውን ቁርጠኝነት አሳይተዋል።

ግንባታው 16 የካፍ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚደረግ ሲሆን በሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እና የአማራ ክልል ወጣት እና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዕርዚቅ ኢሳ መካከል የስምምነት ፊርማ ተደርጓል።

በግንባታ ማስጀመሪያ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ከአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በተጨማሪ፣ የኢፌዴሪ መረጃ እና መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጀኔራል ዳይሬክተር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ፤ የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር አብርሃም በላይ ፤ የኢፌዴሪ ባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ ፤ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክሲዮን ማኅበር የቦርድ ሰብሳቢ መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ ፤ አትሌት ሞስነት ገረመው፣ የክልሉ ባለሀብቶች እና ሌሎች በርካታ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።


## ኦሮሚያ ክልል

የባለቤትነት ስሙ በአቶ ሞላ ዋሴ የተመዘገበው የሰሌዳ ቁጥሩ 1-44591 ኦሮ፣ የሻንሲ ቁጥር 30694፣ ሞዴል RE-45 የሞተር ቁጥሩ 50355፣ የሊብሬ ቁጥሩ 0182826 የሆነው ባጃጅ ተሽከርካሪ የኋላ ሰሌዳ ጠፍቶብኛል ብለው በ23/02/2015 አሳውቀውናል፡፡ ስለሆነም ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ተይዟል የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ሪፖርት እንዲያደርግ እየጠየቅን፤ ይህ ባይሆን ግን ለባለንብረቱ ምትክ ሰሌዳ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር**
**የሰበታ ከተማ የትራንስፖርት ኤጀንሲ**

የባለንብረቱ ስም ሀይልዬ ወንድሙ የተሽከርካሪ ዓይነት ባጃጅ የሰሌዳ ቁጥር 03-50722 ኦሮ የሻንሲው ቁጥር MAKM2HJG3L42610 ሞዴል Algga የሞተር ቁጥር፡- R6K2833115 የሊብሬ ቁጥር 000348247 ከላይ የተጠቀሰው ባጃጅ የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብን ብለው በ30/01/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። ሰሌዳው ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን የትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## አማራ ክልል

የባለንብረቱ ስም እውነቴ አሰፋ መንግስቴ የሰሌዳ ቁጥር አማ- 01-58919 የተሽከርካሪው ዓይነት ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ የተሽከርካሪው የአገልግሎት ዓይነት ለከተማ ታክሲ ሞዴል RE-45 የሞተር ቁጥር AZZWLC07589 የሻንሲ ቁጥር MD2A25BY6LWD98828 የተሽከርካሪው የመጫን አቅም 3 ሰው ዓመታዊ ምርመራ ቀን 28/3/2014 ዓ.ም ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ሰሌዳ የጠፋ በመሆኑ ገልፀው በምትኩ እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በአብክመ ምሥራቅ ጎጃም ዞን ትራንስፖርት ቀ/ጽ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች ወ/ሮ ሰብለወንጌል ታደሰ ኢዶ ተጠሪ አቶ አባይ ዴሲሳ ጫላ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ስለሆነ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም ወ/ሮ ሰብለወንጌል ታደሰ ኢዶ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ22/03/2015 ዓ.ም 4፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አ/አ/ከተማ የ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ሙዘሚል መሀመድ አሊ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-45839 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALF-SR33L87000045 ሞዴል FSR የሞተር ቁጥር 6HH1-432674 የሊብሬ ቁጥር 242142 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 20/1/2015 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም እፀገነት ኪ/ማሪያም አለሙ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A02581 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JTD-BW23E610009619 ሞዴል NZE120-AEPDKV የሞተር ቁጥር 2NZ-2744963 የሊብሬ ቁጥር 327460 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 25/2/2015 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አቶ ተስፋዬ ተወልደ- የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-99450 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻሲ ቁጥር JTF-WS726100006668 ሞዴል KDN170L-CRMDYW የሞተር ቁጥር 2KD-0983531 የሊብሬ ቁጥር 598277 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 25/2/2015 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ ወ/ሮ ማህሌት እንዳለ እና በተከሳሾች ወ/ሮ ዘይነባ አብደላ መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች መከሰሳቸውን አውቀው ለ23/3/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቃችሁ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ ቀጥታ ፍ/ብሔር 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 1 ቀጥታ ክስ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ፍሬህይወት ግርማ ለማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B41005 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር MA3ZF6C1XMA733912 ሞዴል ZF6C1 የሞተር ቁጥር K12MN-4693553 የሊብሬ ቁጥር 336912 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 25/2/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ይደግ ዘውዴ እምሩ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-00262 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር 682-0091315 ሞዴል 682N3 የሞተር ቁጥር 0116998 የሊብሬ ቁጥር E068307 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 25/2/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም በላይ ደበበ ወልደየስ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-24985 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር LJRP12377D2009278 ሞዴል XXXXX የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0155317 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ24/2/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሰላም አፍወርቅ- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-62736 የተሽከርካሪው ፈሳሽ ጭነት የሻሲ ቁጥር LZFF25T44CD248634 ሞዴል 5254GYYYHBB የሞተር ቁጥር F2CE0681B*B052-12C00032290* የሊብሬ ቁጥር 0064968 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 17/2/2015 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አራዳ ቅ/ጽ/ቤት**